ምርጫ 2013

የምርጫ ቃልኪዳን ሠነድ

ኢዜማ

የመጨረሻ ረቂቅ

ይህ የምርጫ ቃል ኪዳን ሠነድ በኢዜማ የተዘጋጀ ሲሆን፤ ይህ ረቂቅ ሠነድ ለፓርቲው ኮንፈረንስ ቀርቦ ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

ማውጫ

መግቢያ 4
ክፍልአንድ 6
1.1. የኢትዮጵ ያዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ/ኢዜማ/ መለያዎች 6
1.1.1. መሰረታዊመርሆች 6
1.1.2. የፖለቲካፍልስፍና 6
1.1.3. ራዕይተልዕኮና ግብ 7
1.1.4. የኢዜማእሴቶቹ 7
1.1.5. ስትራቴጂያዊግቦቹ 8
1.1.6. የኢዜማ የአደረጃጀትና የአሰራር መርህ፣ 8
ክፍል ሁለት 9
2.1. የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታና መሰረታዊ ችግሮች 9
2.1.1. አጭር የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ 9
2.1.2. ሀገራዊ የደህንነት ሁኔታ 10
2.1.3. ከፖለቲካ 13
2.1.4. ከኢኮኖሚ 15
2.1.5. ማበራዊ 20
ክፍል ሦስት 22
3.1. የብሔራዊ ደህንነት መሰረታዊ ችግሮች መፍቻ መንገዶች ለቀጣይ አምስት ዓመት 22
3.1.1. የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት (ፓርላማ) የሰላምና ደህንነት ቋሚ ኮሚቴ 23
3.1.2. የብሄራዊ ደህንነት ካውንስል 23
3.1.3. የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሄራዊ ደህነት አማካሪ ፅ/ቤት 24
3.1.4. የደህንነት ማህበረሰብ 24
3.1.5. ፍ/ቤቶች 24
3.1.6. ዓቃቢ ሕግ 25
3.1.7. የፖሊስ ተቋማት 26
3.1.8. መከላከያ 26
3.2. ሲቪልሰርቪስ 28
ክፍል አራት 29
4.1. የፖለቲካ መሰረታዊ ችግሮች መፍቻ መንገዶች ለቀጣይ አምስት ዓመት 29
4.1.1. ሕገ መንግስታዊ ስርዓትን ማክበርና ማስከበር 29
4.1.2. የሕዝብ የስልጣን ባለቤትነት ጥያቄ 29

4.1.3. የመድበለ ፓርቲ ስርዓት ግንባታ 29
4.1.5. የመሬትባለቤትነት 31
4.1.6. የሊዝ ፖሊስ 31
4.1.7. ባንዲራ 31
4.1.8. የግልና የቡድን መብቶች 32
4.1.9. ሰብዓዊና ዲሞክራሲ መብቶች 32
4.1.10. የሠራተኛና የሙያ ማኅበራት 33
ክፍል አምስት 34
5.1. ግብርናገጠርልማት 34
5.2. ማዕድን 36
5.3. ኢንዱስትሪ 36
5.4. ንግድ 37
5.5. ቱሪዝም 38
5.6. መሠረተ ልማት 38
5.6.1. መንገድ 38
5.6.2. ባቡር 39
5.6.3. ኃይል አቅርቦት 39
5.6.4. የውሃ አቅርቦት 40
5.6.5. ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ 40
5.7. ፋይናንስ 41
5.8. ከተማ ልማት 41
5.9. ኢንቬስትመንት 43
ክፍል ስድስት 45
6.1.የማህበራዊመሰረታዊችግሮችመፍቻመንገዶችለቀጣይአምስትዓመት 45
6.1.1. ትምህርት 45
6.1.2. ጤና 45
6.1.3. ሰደት 46
6.1.4. ባህል 47
6.1.5. የስርዓተ-ፆታ 48
6.1.6. የወጣቶች 49
6.1.7. አካልጉዳተኝነት 49
6.1.8. በማህበራዊከለላ 50
ክፍል ሰባት 52
7.1. የውጭግንኙነት መሰረታዊ ችግሮች 52

7.2. የመፍትሔ አቅጣጫዎች 53
7.3. በአጠቃላይ 53
7.4. ጎረቤት ሃገሮችን በተመለከተ 54
7.5. በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን 54
ክፍል ስምንት 56
8.1. የቃልኪዳንሠነድመተግበሪያሥልቶች 56
8.1.1. ስትራቴጂ 56
8.1.2. ፋይናንስ 56
8.2. መራጩ ሕዝብ ኢዜማን ለምን ይመርጣል 56
8.2.1. የደህንነት ጉዳዮች 56
8.2.2. የፖለቲካ ጉዳዮች 57
8.2.3. የኤኮኖ ሚጉዳዮች 57
8.2.4. የማህበራዊ ጉዳዮች 57
8.2.5. የውጭ ግንኙነት ጉዳዮች 58

መግቢያ

አገራችን ኢትዮጵያ እጅግ በጣም ወሳኝ የሆነየታሪክምዕራፍላይቆማለች። ይህ የታሪክ ምዕራፍ ከዚህ ቀደም ገጥሞን የማያውቅ እጅግ በጣም ውስብስብና ፈታኝ የሆነ የታሪክምዕራፍ ነው። በ1966 እና በ1983 ዓ.ም. ኢትዮጵያን የፍትህ፣ የነጻነት፣ የዲሞክራሲና የእኩልነት አገር የማድረግ ሁለት መልካም አጋጣሚዎች በተከታታይ መክነዋል፣ ሆኖም ኢትዮጵያ እየተንገዳገደችም ቢሆን ዛሬ ላይ ደርሳለች። ዛሬ የምንገኝበትን ወቅት ወሳኝ ታሪካዊ ወቅት ነው የምንለው ዛሬም እንደገና ለሦስተኛ ግዜ የሀገራችንንየወደፊትእጣፈንታ የመወሰን ዕድል ስላገኘን እና ይህንን ዕድል እንዳለፉት ሁለት ዕድሎች ብናመክነው በኢትዮጵያ እንደ አገር ወደፊት የመቀጠል ዕድል ላይ ሊደርስ የሚችለው ታሪካዊ አደጋ ግዝፈት ከወዲሁ ስለሚታየን ነው።

ኢትዮጵያ በ2013 ዓም የምታደርገው አገራዊ ምርጫ ነጻና ፍትሃዊ ሆኖ መፈጸሙ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጅምራችን ዋስትና የሚሰጠን ከመሆኑ ባሻገር፣ በብዙ የተወሳሰቡ አገራዊና አለምአቀፋዊ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ የሚካሄድ ምርጫ በመሆኑ፣ ምርጫው የአገራችንን የወደፊት አቅጣጫ የሚወስን ታሪካዊ ምርጫ ነው። ይህ ምርጫ የሚካሄደው በሰሜናዊው የአገራችን ክፍል ህግና ሥርዓትን ለማስከበር የተካሄደው የመጀመሪያው ዙር ዘመቻ ተጠናቅቆ የመልሶ ማቋቋም ስራ በተጀመረበት፣ አንዳንድ ፀረ ሰላም ኃይሎች ህዝብን በሚያሸብሩበት፣ አንዳንድ አገሮችና አለም አቀፍ ድርጅቶች ሉዓላዊነታችንን በተመለከተ እኛ የምንላችሁን ካልሰማችሁ እያሉ ቃል የገቡትን እርዳታ ጭምር አንሰጣችሁም ባሉበትና ከፍተኛ ጫና ባሳደሩብን፣ ሱዳን በውጭ ኃይሎች አይዞሽ ባይነት የአገራችንን ድንበር በደፈረችበት፣ ግብፅ በህዳሴው ግድብ የተነሳ ከኢትዮጵያ ላይ አይኗን አላነሳም ባለችበት፣ በመሃል አገር የሚገኙ አንዳንድ አገራችን የምትገኝበት ውስብስብ ፖለቲካ ሁኔታ ያልገባቸው የፖለቲካ ኃይሎች ለእውነት የቆሙ እየመሰላቸው ማዕከላዊውን መንግስት በሚያዳክሙበትና አንዳንዶቹ ደግሞ በምርጫው ተሳትፈው የዲሞክራሲ ጅምራችንን ከማሳመር ይልቅ በምርጫው በራሱ ላይ ጥያቄ በሚያነሱበት ወቅትና ባጠቃላይ የአገራችን አንድነትና ሉዓላዊነት ከውጭም ከውስጥም በሚፈተንበት ታሪካዊ ወቅት ነው።

ኢዜማ ይህ ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ በሚፈልገው መንገድ ተጀምሮ የሚፈልገውን ውጤትም እንዲያገኝ እያንዳንዱ የፖለቲካ ባለድርሻ የሚጠበቅበትን ሁሉ ካደረገ፣ ከምርጫው በኋላ የሚፈጠረው መስተዳደር (Government) ህገ መንግስት ለማሻሻል፣ አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት ለመገንባት፣ የፌዴራል ሥርዓቱን በአዲስ መልክ እንደገና ለማዋቀር እና ሌሎችም የአገራችንን የረጂም ግዜ ህዝባዊ ጥያቄዎች ለመመለስና ችግሮች ለመፍታት ህጋዊነትና ቅቡልነት ይኖረዋል የሚል ከፍተኛ እምነት አለው። በኢዜማ አመለካከት የዚህ ምርጫ ትልቁ ፋይዳ በአንድ በኩል ነጻና ፍትሃዊ ሆኖ ተካሂዶ የዲሞክራሲ ጅምራችንን ተስፋ የሚያሰጥ መሆኑ ላይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አገራችን ኢትዮጵያን ከላይ ከተዘረዘሩት ችግሮች በድል ይዞ መውጣት የሚችልና በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደታችን የመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ ለብዙዎቹ ዘመን ላስቆጠሩ ትላልቅ ጥያቄዎቻችን ተቋማዊ ምላሽ መስጠት የሚችል አመራር መፍጠር መቻሉ ላይ ነው።

ይህ የምርጫ ማኒፌስቶ ኢዜማ ምርጫውን ካሸነፈ በአጭርና በረጂም ግዜ እሰራለሁ የሚላቸውን ዋና ዋና ፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ስራዎች ቢሆንም፣ ኢዜማ በአጭር ግዜም ሆነ በረጂም ግዜ በያዛቸው ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ውስጥ ምን ግዜም ቅድሚያ የሚሰጠው ለአገር አንድነት መከበር እና ለሰላምና መረጋጋት መሆኑ ለአንዲት ደቂቃም ቢሆን መረሳት የለበትም። በሥልጣን ላይ ያለውን መንግስት ጨምሮ፣ በዚህ ምርጫ ላይ የሚሳተፉ ኃይሎች ሁሉ እና ሌሎችም ባለድርሻዎች ከምርጫው በፊት፣ ለምርጫው በሚደረግው ዝግጅት፣ በምርጫ ዘመቻው ወቅትና ከምርጫው በኋላ በሚያደርጓቸውና በማያደርጓቸውን ነገሮች ሁሉ ለአገር አንድነት መቀጠልና ለሰላምና መረጋጋት ትልቅ ቅድሚያ መስጠት ይኖርባቸዋል።

ኢትዮጵያ ዉስጥ ከደርግ ውድቀት በኋላ አምስት ተከታታይ “ምርጫዎች” ተካሂደዋል፣ ሆኖም አንዳቸውም የኢትዮጵያን ህዝብ የስልጣን ባለቤት ማድረግ አልቻሉም። አንፃራዊ ፉክክር ከተያበት ከ1997ቱ ምርጫ ዉጭ ሌሎቹ ምርጫዎች የህዝብም የተፎካካሪዎችም ይሁንታ አልነበራቸውም። በ2013 ዓ. ም. በኢትዮጵያ የሚካሄደው ስድስተኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ በገዢው ፓርቲ በኩል ነጻ፣ ትክክለኛና ፍትሃዊ እንዲሆን ፍላጎት አለን የሚሉ መግለጫዎች እየተሰጡ ቢሆንም፤ ኢዜማ እንደ ፓርቲ የበኩሉን ለመወጣት ከምንግዜውም በተሻለ በተፎካካሪ ወገን ምርጫው የተሻለ እንዲሆ የበኩሉን ጥረት እያደረገ ነው::

ኢዜማ የዘንድሮው ምርጫ ከዚህ በፊት ከተፈፀሙት ኢ-ዴሞክራሲያዊ አሠራሮች በቂ ትምህርት የተቀሠመበትና ስህተቶች የማይደገሙበት ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲሆን ፍላጎት አለው፡፡ በ2013 ምርጫ ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመሸጋገር የሚያስችል ጽኑ መሠረት መጣል አለብን ብለን እናምናለን፤ ይህ ሳይሆን ቢቀር ሀገራችን እጅግ በጣም ፈታኝና ህልውናችንን አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ውስጥ ልንገባ እንችላለን። ዛሬ የምንገኝበት ሁኔታ በውስጥና በውጭ ሉዓላዊነታችንን እና አንድነታችንን የሚፈታተኑ ኃይሎች በቅርብ እየተናባቡ የሚሰሩበት ግዜ ስለሆነ፣ህዝባዊ አመኔታና ተቀባይነት የሌለው የይስሙላ ምርጫ አካሂደን ሉዓላዊነታችንን ለሚፈታተኑ ኃይሎች አመቺ ሁኔታ መፍጠር የለብንም ብሎ ኢዜማ ያምናል።

በሀገራችን ኢትዮጵያ ሊፈጠር የሚችለው ቀውስ ስፋትና ጥልቀት እጅግ በጣም ትልቅ ስለሚሆን ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ ማንም የፖለቲካ ኃይል በዚህ ቀውስ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ያለን ብቸኛ አማራጭ አገራችን ኢትዮጵያ በሃምሳ አመት ውስጥ ለሦስተኛ ግዜ ያገኘችውን ፍትህ፣ ነጻነት፣ዲሞክራሲና እኩልነት የሰፈነበት የፖለቲካ ማህበረሰብ የመገንባት ዕድል ከእጃችን እንዳይወጣ ማድረግ ነው።

የ2013ቱ ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ የስልጣን ምንጭ መሆኑን የሚያሳይበት እንደሚሆን እምነታችን ፅኑ ነው፡፡ የህዝብ የስልጣን ምንጭነት የሚረጋገጠው ደግሞ ለፖለቲካ ሥልጣን የሚወዳደሩ ድርጅቶች እኩል የመወዳደሪያ ሜዳ ሲያገኙ፣ ህዝብ ያለምንም መከልከል የተሊያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚነግሩትን መስማት ሲችልና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸው የምርጫ መርሆዎች ሥራ ላይ ሲውሉ ነው፡፡ ፊት ለፊታችን ላይ ያለው ምርጫ ገዢው ፓርቲ ከዚህ በፊት እንደነበሩት አምስት ምርጫዎች እራሱን መልሶ ወደ ሥልጣን ለማምጣት የሚጠቀምበት መሳሪያ እንዳይሆን እራሱን ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ ሁሉም የፖለቲካ ባለድርሻዎች በግልም በቡድንም የየራሳቸውን አዎንታዊ ሚና መጫወት አለባቸው። ኢትዮጵያ በታሪኳ የህዝብን ይሁንታ አግኝቶ ወይም በዲሞክራሲያዊ መንገድ ተመርጦ ሥልጣን የያዘ ፓርቲ ኖሯት አያውቅም። በመጪው ግንቦት ወር የሚካሄደው አገራዊ ምርጫ ህዝብ ብቸኛ የሥልጣን ምንጭ መሆኑን፣እኛ ኢትዮጵያዊያን እንደሌሎች ህዝቦች የራሳችንን መሪዎች መመረጥ የምንችልና ለዲሞክራሲ ዝግጁዎችን መሆናችንን ለራሳችንም ለአለም ህዝብም የምናሳይበት ታሪካዊ ምርጫማድረግ አለብን። ይህን ለማድረግ ብቸኛ ሃላፊነት የተሰጠው አካል ስለሌለ፣ ገዢው ፓርቲ፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ ሲቪክ ድርጅቶችና ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ ማድረግ አለባቸው።

ኢዜማ በዚህ ዓመት የሚደረገው ምርጫ ነፃ፣ ትክክለኛና ፍትሃዊ እንዲሆን በዋነኛነት እምነቱን የጣለው በመራጩ ህዝብ ላይ ቢሆንም በሥልጣን ላይ ያለው መንግስት፣ምርጫ ቦርድ፣ተፎካካሪ ፓርቲዎች፣የሜዲያ፣ የጸጥታና የፍትህ ተቋሞችም ምርጫውን ነፃና ፍትሃዊ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የሚጫወቱት ሚና በጣም ከፍተኛ ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎችን በእኩል አይን የሚመለከቱና ህዝብ በምርጫ የሰጠውን ድምፅ በገለልተኝነት ቆጥረው ትክክለኛውን አሸናፊ ፓርቲ ለህዝብ ያሳውቃሉ የሚባሉ የምርጫ ቦርድ ሃላፊዎች መኖራቸውና የምርጫ ቦርድን አቅም ለመገንባት ከፍተኛ የበጀት ድጋፍ ከመንግሥት፣ ከውጭ አገሮችና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች መኖሩ፤ ምርጫውን የተሻለ ያደርገዋል የሚል ተስፋ አለን፡፡ የምርጫው መሰናክል ሊሆኑ የሚችሉ ችግሮችን ለመፍታት እንዲቻል እንደ አንድ ሃላፊነት እንደሚሰማው የፖለቲካ ድርጅት ሚፈለግብንን ሁሉ የምናደርግ ሲሆን፤ የአገራችንን መሰረታዊ የፖለቲካ ችግሮች ለመፍታት የጀመርነውን ትግል ወድጎን ሳንተው በምርጫው ለመወዳደር የሚያስችለንን ሁለገብ ዝግጅት ቀጥለናል፡፡ ኢዜማ ይህን የቃልኪዳን ሠነድ እንዲዘጋጅና በምርጫ ንቁ ተሳታፊ ለመሆን ሲወስን የህዝብን ታሪክ ሰሪነት በመተማመን ነው፡፡

ይህ የቃልኪዳን ሠነድ የኢዜማ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ መርሆዎችና አሠራሮች፣ ኢዜማ በአጭር ጊዜ የምስረታ ታሪኩ ያደረጋቸውን ትግሎችና ልዩ የሚያደርጓቸውን ባህሪያት በአጭሩ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ የቃል ኪዳን ሰነዱ ኢዜማ ለኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች አለኝ የሚላቸው የመፍትሄ ሃሳቦችአሁን በሥልጣን ላይ ካለው መንግሥትና ከሌሎችም ተፎካካሪ ፓርቲዎች የተሻለ መሆኑን ያሳያል። ይህ የቃልኪዳን ሠነድ ትኩረት ያደረገው ኢዜማ ምርጫውን አሸንፎ ሥልጣን ቢቆጣጠር ቅድሚያ በሚሠጣቸው አበይት ፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊ እና የውጭ ግንኙነት ጉዳዮች ላይ ነው፡፡

ኢዜማ በነፃ ምርጫ፣ በሕዝብ ፈቃድና ሠላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ የመንግሥት ሥልጣን የሚያዝበትና የሚለቀቅበት አዲስ ምዕራፍ በኢትዮጵያ እንዲጀመር የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡ ወደፊት ይሽንኑ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ተሳትፎ ይገፋበታል፡፡ በመሆኑም መራጩ ሕዝብ የኢዜማን ተጨባጭ ጥረትና በዚህ የምርጫ የቃልኪዳን ሠነድ የቀረቡትን ሀገራዊ አጀንዳዎች መዝኖ ኢዜማን በመደገፍ ድምፁንና ውክልናውን እንዲሠጥ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

ክፍልአንድ

1.1. የኢትዮጵ ያዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ/ኢዜማ/ መለያዎች

1.1.1. መሰረታዊመርሆች

ኢዜማ የፖለቲካ ፍልስፍናውን፣ ርዕዩን፣ ተልዕኮውን፣ ስትራቴጂክ ግቦቹን እና የእሴቶችን ምንነት የወሰኑ፣ ለድርድር የማይቀርቡ፣ አሥር መሰረታዊ መርሆዎች አሉት።

- የኢትዮጵያና የሕዝቧ ጥቅም፣ ሰላምና ደህንነት፣ ምንግዜም ቅድሚያ ይኖረዋል።
- በብዝሀነት (Diversity) የተዋብንና የተገመድን አንድ ሕዝብ መሆናችንን እናምናለን።
- ማንኛውም ዜጋ፣ በዘር፣ በሀይማኖት፣በጾታ፣ወይም በዕድሜ፣ ሳይበላለጥ፣እኩል መብት፣ እኩል ፍትህ፣ እና በፖለቲካ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና ሌሎችም መስኮች የመሳተፍ እኩል ዕድል (Opportunity) ሊኖረው/ ሊኖራት ይገባል።
- ዕውነተኛ ዴሞክራሲ ለሀገራችን ህልውና እና ማንሰራራት ዋና መሠረት መሆኑን እንገነዘባለን።
- ያልተማከለ የመንግሥት አስተዳደር፣ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነትን ወደ ዜጎች በማቅረብ፣ የፖለቲካዊ ግልጽነትንና ተጠያቂነት ባህል በማጠናከር፣ የመልካም አስተዳደር መሠረት በመሆን፣ ለፈጣን የማኅበራዊና የኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት እናምናለን።
- ለማንነት ፖለቲካ መንስኤ ለሆኑት ችግሮች መፍትሄ የሰጠና፣ ዜግነት ላይ ብቻ ያተኮረ የፖለቲካ አመለካከት፣ ለእውነተኛና ዘላቂ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረት እንደሆነ እንገነዘባለን።
- ኢትዮጵያን የማዘመን ግዳጅ የሕዝቧን ልዩ ማንነትና ባህላዊ እሴቶች ለመጠበቅና ለመንከባከብ፣ የዜጎችን ሰብዓዊ ክብርና የሃገርን ህልውና ማረጋገጫ መጠበቂያ ዋስትና መሆኑን እናምናለን።
- ኢትዮጵያ ልንንከባከበዉ የሚገባን ባለ ብዙ፣ ባህል፣ ታሪክና ቅርስ ባለቤት የሆነች አገር መሆኗን ከልብ እናምናለን።
- የማኅበረሰባቸን የሞራል መሠረት፣ ማኅበራዊ ፍትህ (Social Justice) የማስፈን፣ ለድሆችና ለደካሞች ድጋፍና ጥበቃ (Welfare State) የማድረግ ኃላፊነት ላይ የተመሠረተ ሊሆን እንደሚገባው በጽኑ እናምናለን።
- ለተከታታይ ትውልዶች ሁለንተናዊ እድገትና ብልጽግና የተጎናጸፈች፤ የተፈጥሮ ሀብቷንና ውበቷን የተንከባከበች ኢትዮጵያን፣ ለትውልዶች የማስረከብ ሀላፊነት እንዳለባቸው ከምር እንገነዘባለን፣

በኢዜማ እይታ ድርጅታዊመርሖቹንበግልጽናበተሟላሁኔታማስቀመጥያልቻለየፖለቲካ ድርጅትበርግጥምየፖለቲካ ድርጅትነኝብሎራሱንቢጠራም፣አንድንየፖለቲካ ድርጅትዘመን ተሻጋሪነትን ዋስትና የሆነውን በመርሕላይየመመሥረትንቁልፍ መመዘኛስለማያሟላእንደፖለቲካ ድርጅትሊታይአይገባም።

1.1.2. የፖለቲካፍልስፍና

ኢዜማ የፖለቲካ ፍልስፍና ማህበራዊ ፍትህ ነው። ማህበራዊ ፍትህ፣ "ዜጎች ዕኩል የህይወት ዕድል ሊኖራቸው ይገባል" የሚል የፖለቲካ ፍልስፍና ነው። በአሁኑ ወቅት በሀገራችን የሚታየውን እኩል ያልሆነውን የዜጎች የህይወት እድል ከማስተካከል ሆነ የወደፊቱን ከማረጋገጥ አንጻር፣ ማህበራዊ ፍትህ የተሻለው የችግር አረዳድና የመፍትሄ ሀሳቦች አመላካች ፖለቲካ ፍልስፍና መሆኑን ኢዜማ ከልቡ ያምናል። በኢዜማ እይታ ሀገራችን ኢትዮጵያ የተረጋጋችና ከፍተኛ የእድገት ደረጃ የደረሰች ሀገር ለመሆን ማህበራዊ ፍትህ የሰፈነባት ሀገር መሆን ይኖርባታል። ኢዜማ በተለያዩ የሀገራችን ጉዳዮች ላይ የቀረፃቸው ፖሊሲዎች ሁሉ የማህበራዊ ፍትህ የፖለቲካ ፍልስፍና መሰረት ያደረጉ፣ እድገትን የሚያበረታቱና የብዙሃኑን ተጠቃሚነት በቀጥታ እንዲያረጋግጡ ሆነው የተቀረጹ ናቸው።

በኢዜማ እይታ፣ ማናቸውም በምርጫው የሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሀገራችን ችግሮች አማራጮች የመፍትሄ ሀሳቦቻቸውን መሰረት ያደረጉበትን የፖለቲካ ጉዳዮች ከፍተኛ የምክኒያት አረዳድ ሀሳቦችን (ፍልስፍናዎችን) ለመራጩ ሕዝብ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

1.1.3. ራዕይተልዕኮና ግብ

ራዕይ

“ኢትዮጵያ ሀገራችን፥ የእያንዳንዱ ዜጋዋ ፖለቲካዊ፣ ሰብአዊና ኢኮኖሚ መብቶች የተከበሩባት፣ ማኅበራዊ ፍትሕ የሰፈነባት፣ በዜጎቿ ጽኑ አንድነት ማሕቀፍ፥ የተለያዩ ባህሎች፣ቋንቋዎችና እምነቶች ሳይበላለጡ በነጻነት የሚስተናገዱባትና የውበቷ መገለጫ ብቻ የሆኑባት፣ ሰላምና መረጋጋት የተረጋገጠባት፣ በላቀየ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀት ላይ የተመሠረተ፥ ሁለንተናዊ ዕድገትና ብልጽግና የተጎናጸፈች፣ሁሉም ዜጎቿ የሚኰሩባት ታላቅና ገናና ሀገር ሆና ማየት ነው።”

ተልዕኮ

ኢዜማ በርእዩ ላይ እውን እንድትሆን ያስቀመጣትን ሀገር እውን የማድረግ ሐላፊነትን ለመወጣት፥ ምን ዐይነት ፓርቲ መሆን እንዳለበትና ማከናወን ያለበትን ሀገርን መለወጥ የሚችሉ ተግባራትን የሚመላክቱ ሐሳቦችን ያካተተ መልእክ ትበተልዕኮ ተከቷል።

“ሰፊ የሕዝብ መሠረት ያለው የመንግሥት ሥልጣን ባለቤት በመሆን እና የፓርቲውን መርሖች መሠረት ያደረጉ የዕድገት፣ የብልጽግና እና የሥልጣኔ ፖሊሲዎችን በመቅረጽና በማስፈጸም፣በርእዩ ላይ የተቀመጠችውን ዘመናዊትና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ነው።”

ግብ

የኢ-ዜማ ግብ በኢትዮጵያ አገራችን የመደበለ ፓርቲ የፖለቲካ ሥርዓት ተገንብቶ፣ የዜጎች ሉዓላዊነት የተረጋገጠበት፣ ዜጎች በቋንቋ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፆታ ወይም በማንኛውም የማንነት መገለጫ መድልዖ የሌለባት፤ ለዜጎችን ምቹ እና በሌሎችም የምትምረጥ አገር ማድረግ ነው፡፡

1.1.4. የኢዜማእሴቶቹ

ተጠያቂነት/Accountablity

- ✓ የኢ-ዜማ አሰራሮች ሁሉ ያልተማከሉና ግልፅነትና ተጠያቂነትን በሚያረጋጥ ሁኔታ ይሆናል፡፡ ኃላፊነትን በአግባቡ መወጣት፣ አጥርቶ መስራት የኢዜማ አባላት መገለጫ ይሆናል፡፡

ሠላማዊነት/Be peacfull

- ✓ ኢ-ዜማ ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴን ብቸኛው የሰልጣን መያዣ መንገድ ነው ብሎ ያምናል፡፡
- ✓ ኢ-ዜማ ማንኛውንም አመለካከት በኃይል በሌሎች ላይ ለመጫን የሚደረጉ አካሄዶችን ይቃወማል፤ ዜጎች የመሰላቸውን አቋም መደገፍና በሰላማዊ መንገድ መቃወም አይከለከልም፡፡

ትብብር/የቡድን ሥራ/Cooperation

- ✓ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፣ በፓርቲው ውስጥ የቡድን ሥራን ያበረታታል፡፡
- ✓ ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክ ያላት እንደመሆኗ መጠን፤ መጪው ትውልድ በሀገራችን ኢትዮጵያ የተፈጠሩ ማንኛቸውም ታሪካዊ ክስተቶች ለትምህርታዊ ግብዓት ከመጠቀም ውጭ፤ ለቂም በቀልና ህዝብን ከህዝብ ለማጋጨት እንዳይውል አስፈላጊውን ያደርጋል፣ የሲቪል ማህበራትና የትምህርት ተቋማት የውይይት መድረኮች እንዲያዘጋጁ ያበረታታል፤

ውይይት/ Dialogue

- ✓ ኢ-ዜማ በሀገራችን ከዚህ በፊት የተፈጠሩ የፖለቲካ ቁርቁሶች በሀገራዊ ዕርቅ መድረክ ሊፈቱ ይገባል የሚል ፅኑ እምነት አለው፡፡ ይህ የእርቅ መድረክ በአቋራጭ ስልጣን መያዣም ሆነ ሌሎች የፖለቲካ ጥቅሞች ማግኛ እንዳይሆን አብክሮ ይሰራል፡፡

- ✓ ኢ-ዜማ የሚወስዳቸውን የፖለቲካ አቋሞች በይፋ ለህዝቡ ያሳውቃል፡፡ የፖለቲካ ልዮነቶች ለቀጣይ ውይይት እንጂ ለግጭት መንስዔ እንዳይሆኑ አበክሮ ይሰራል፡፡

ልህቀት/Excellence

- ✓ ኢ-ዜማ በአስራር ልቀት ለሚያሳዩ አባላት እንዲሁም የፓርቲው ልዩ ልዩ አሃዶች እውቅናን ይስጣል፣ ይሸልማል፡፡

1.1.5. ስትራቴጂያዊግቦቹ

- ✓ ኢዜማተልዕኮውንማስፈፀምየሚችልዘመንተሻጋሪ፤ጠንካራተጠያቂነትያለበት የፖለቲካ ፓርቲማድርግ፤
- ✓ ኢዜማ ኢትዮጵያን በጠንካራ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እድገት ጎዳና መምራት የሚችልና የህብረተሰቡን አመኔታ ያገኘ የመንግሥት ቅርፅ እንዲኖረው ማድረግ፣
- ✓ በአገራችን ሠላምና መረጋጋትን ለማስፈን፣ የተጀመረውን አገራዊ ለውጥ ተቋማዊ ለማድረግ እንዲቻል ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባባር ጉልህ ሚና መጫወት፤
- ✓ በየደረጃውበሚገኙምክርቤቶችአብላጫወንበርበመያዝመንግሥትለመመስረትየሚያስችልመቀመጫዎችማሸነፍ፤

1.1.6. የኢዜማ የአደረጃጀትና የአሰራር መርህ፣

- በኢዜማ የአወቃቀር መርሕ መሠረት፥ የፓርቲው ከፍተኛ የሥልጣን አካል የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ነው።የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ከፓርቲው ዝቅተኛ አካል ከሆነ ከምርጫ ወረዳ አባላት የሚወከሉ ጉባኤተኞች ስብሰብ ነው። በዚህም አወቃቀር ከፍተኛው የፓርቲው ሥልጣን የተሰጠው፥ ለመሠረታዊው የፓርቲው መዋቅር አካል ነው።
- የኢዜማ መዋቅር፥ የመሠረታዊ ጉዳዮችንና ድርጅታዊ ጉዳዮችን የለየና ያደጋገፈ ነው። ይህ አወቃቀር የመንግሥትና የድርጅት ጉዳዮችን ለያይቶ የሚያስቀም ጥአሠራር፥ በድርጅት ውስጥ የሚነሡ ችግሮች ወደ መንግሥት ብሎም ወደ ህገር ችግርነት መሄድ የለባቸውም፤ የመንግሥትን ግብዓት ከድርጅት ጋር መደባለቅ ለከፍተኛ ብክነትና ዘረፋ ተጋልጦ መሰጠት የለበትም፥ ከሚሉ መጠበቂያዎች የተነሣ የአደረጃጀት መርሕ አቋም ነው።
- ኢዜማ፥ ይሄን ዐይነት አደረጃጀት የተከተለው ከፍ ብሎ ከጠቀሳቸው ምክንያቶች በተጨማሪ የህገራችን ገዥ ፓርቲዎች አደረጃጀትና አሠራር ያስከተለውን እጅግ አደገኛ ህገራዊ ሁኔታን ታሳቢ በማድረግ ነው። በገዥው ፓርቲና በመንግሥታዊ መዋቅር መኻል ይሄ ነው የሚባል ልዩነት ስለሌለ፥በግንባሩ ውስጥ ብጥብጥ ተነሥቶ የመፍረስ አደጋ ሲከሠት፥ ችግሩ ወደ ህገር የመዛመትና ህገር የማፍረስ አደጋ ያዘለ ነው። ማንኛውም ህገራዊ ሐላፊነት የሚሰማው ፓርቲ፥ እንዲህ ያለ አደጋ እንዳይከሠት፥ የመንግሥትና የድርጅት ጉዳዮችን፥በመዋቅርም ሆነ በአሠራር መለየት እንደ አንድ መሠረታዊ ግዴታው አድርጎ ማየት አለበት የሚል ጽኑ እምነት ኢዜማ አለው።
- ኢዜማ፥ መንግሥታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር መሪና ድርጅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ሊቀመንበር አለው። የኢዜማ አወቃቀሮች በሁለት የተከፈሉት የመንግሥታዊና የድርጅታዊ ጉዳዮች አካላት፥አንዱ ከሌላው ውጪ ምንም ዐይነት ትርጉም ስለሌለው ሁለቱ አካላት ተደጋግፈው የሚሠሩበትን ብሔራዊ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚባል በፓርቲው ሊቀመንበር የሚመራ የጋራ አካል መስርፈቷል።
- ይህ ዐይነት የፓርቲ መዋቅርና አሠራር በህገራችን የድርጅቶች ታሪክ ታስቦም ሆነ ተግባራዊ ሆኖ ስለማያውቅ፥ በብዙዎቻችን ላይ ግርታ መፍጠሩ የሚገርም አይደለም። ይህም በመሆኑ፥ "የህገርሰላም፣ ደኅንነትና ጥቅም ሁል ጊዜም ቅድሚያ አለው" የሚለው የመጀመሪያው የኢዜማ የመርሕ ላይ ያለውን ቁርጠኝነት ፓርቲው በተግባር ያሳየበት አንድ ተጨባጭ መረጃ ነው።

ክፍል ሁለት

2.1. የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታና መሰረታዊ ችግሮች

2.1.1. አጭር የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ላለፉት ሦስት አመታት በለውጥ ሂደት ውስጥ መገኘቷ የሚያጠያይቅ አይደለም። በኢዜማ አረዳድ ለውጡ ያስፈለገው ሀገራችንን ወደ ከፍተኛ አደገኛ ሁኔታ እየገፋት የነበረውን የዘረኛ አምባገነን የፖለቲካ ሥርዓትን ህጋዊ ቅቡልነት ወዳለው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመለወጥ ነው። ይህ የለውጥ ጉዞ ተጀመረ እንጂ አልተጠናቀቀም።

ባለፉት ሦስት የለውጥ አመታት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎች የዘር ማንነትን ምክንያት ባደረገ ጥቃት ህይወታቸውን አጥተዋል፣ ከመኖሪያቸው በመፈናቀል ለከፍተኛ ችግር ተዳርገዋል። በተለይ እንደ መተከል ባሉት ቦታዎች ይህ ችግር በተዳጋጋሚ በመከሰት ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል። በትግራይ የተከሰተው ሁኔታ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆኑ ዜጎች ለሞትና ለችግር እንዲጋለጡ አድርጓል። በሀገራችን በርካታ ቦታዎች ከአለው የደህንነት ሥጋት የተነሳ ዜጎች ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ማድረግ አልቻሉም። የዕለት ተዕለት የዜጎች ደህንነት በሚገባው ደረጃ ባለመጠበቁ ዜጎች በፍርሃትና በጭንቀት እንዲኖሩ ተገደዋል።

በፖለቲካው መስክ ሀገራችን በሁለት አደገኛ አጣብቂኝ ውስጥ ትገኛለች። በአንድ በኩል የዘር ማንነትን መሰረት ባደረገ ፍላጎትና ጥቅምን ለማስከበር ምንም ዓይነት ቀውስ ለመፍጠር ወደ ኋላ የማይሉ ጽንፈኛ ሃይሎች ሲሆኑ በሌላ በኩል ዘርን መሰረት ያደረጉ ሃይሎች ሀገራችን ለምትገኝበት አደገኛ ሁኔታና ለሀገራዊ አንድነት መዳከም ብቸኛ ተጠያቂ በማድረግ ብዝሃነትን ምንም ዓይነት ዋጋ መስጠት የለበትም የሚሉ ሀይሎች ናቸው። የዘር ማንነትን መሰረት ያደረጉና በማናቸውም ዋጋ ፍላጎታቸውን ለማስጠበቅ የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች በአንድ በኩል ግልጽ በሆኑ የጥቃት ተግባራት ላይ የተሰማሩ ሲሆኑ በሌላ በኩል በመንግስትና በፓርቲ መዋቅር ውስጥ ተሰግስገው በአንድ መልኩም ሆነ በሌላ ጽንፈኛ የዘር ቡድኖችን የሚረዱ ናቸው ።

ያልተረጋጋ ሀገራዊ ሁኔታ ለኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚመች አይደለም። ባለፉት ሶስት የለውጥ አመታት በነበረው አለመረጋጋትና ቀደም ሲል በአድሏዊ ተጠቃሚነት የአካባቢት ሀብት በኢኮኖሚው ላይ ክፍተኛ ሚና የነበራቸው አካላት ለለውጡ ባላቸው ቀና ያልሆነ አመለካከት የተነሳ በአንድ በኩል ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ሲዳከም በሌላ በኩል የመሰረታዊ ፍጆታ እቃዎች ዋጋ እየናረ ሄዷል። ይህ ሁኔታ የፈጠረው የኑሮ ውድነት በአብዛኛው ለጉዳት የዳረገው በዝቅተኝ ገቢ ደረጃ የሚገኙትን ዜጎችን ነው። በዚያው ልክ በየጊዜው ወደ ሥራ ፍለጋ ገብያ ውስጥ የሚገባውን በርካታ የሰው ሃይል የሚያስተናግድበት ደረጃ በጣም ዝቅተኛ ነው። በርግጥም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የደህንነትና የፖለቲካ መረጋጋትን የሚጠይቅ ቢሆንም የራሱ የአጭር፣ በአስቸኳይ መፍትሄ የሚፈልጉና የረጅም ጊዜ ጥረቶችን የሚጠይቁ ችግሮች አሉበት።

በማህበራዊ መስክ ያለው ሁኔታ በደህንነቱ በፖለቲካውና በኢኮኖሚው መስክ ካለው የተለየ አይደለም፣ እንደውም ማህበረሰባዊ ችግሮች መንሴአቸው ከደህንነት፣ ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ናቸው። በአሁኑ ወቅት በሀገራችን በርካታ ማህበራዊ ችግሮች አሉ። ከነዚህ በርካታ ማህበራዊ ችግሮች መሀል፣ የትምህርት ጥራትና ተደራሽነት፣ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት፣ ድህነት፣ ሥራአጥነት፣ ወንጀል፣ ስደት፣ የጎዳና ተዳዳሪነት፣ ቤት አልባነት፣ የብሔር ግጭት፣ የፖለቲካ ሙስና፣ መፈናቀል፣ የሰላምና መረጋጋት መጥፋት፣ የሞራል ውድቀትና የማኅበራዊ ወረት (Social Capital) መጥፋት፣ ሱሰኝነት፣ ግድየለሽነት ይገኙበታል።

በኢዜማ ከዚህ በላይ በአጭሩ የተገለጹትን መሰረታዊና ጊዜ የማይሰጡ ሀገራዊ፣ የደህንነት፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበረሰባዊ ሁኔታዎች አሁን ካሉበት ሁኔታ እይተባባሱ ሄደው ወደ አጠቃላይ ሀገራዊ ቀውስ ከመግባታችን በፊት፣ የ2013 ዓ.ም ምርጫ አስቸኳይ መፍትሄ ሊሰጣቸው ይገባል የሚል ዕምነት አለው። ይህም በመሆኑ የኢዜማ የ2013 ዓ.ም የምርጫ ቃል ኪዳን ሰነድ የመጭውን አምስት አመታት በምርጫ አሸንፎ ሀገርን የማስተዳደር እንድል ቢያገኝ ተግባራዊ ሊያደርጋቸው የተዘጋጀባቸውን የመፍትሄ ሀሳቦች እንዲያከታት ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

2.1.2. ሀገራዊ የደህንነት ሁኔታ

ብሄራዊ የውስጥ ደህንነት ስጋቶች

በብሄራዊ የውስጥ ደህንነት ስጋቶች የሚመደቡ በርካታ የስጋት አይነቶች ቢኖሩም በቅደም ተከተል እና በሃገሪቷ እና በዜጎች ላይ ከሚፈጥረው የህልውና ከፍተኛ አደጋ እንጻር ዋና ዋና የሚባሉት እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፦

- መንግስታዊ የፖለቲካ ስርአቱ የተዋቀረበት መንገድ ዘርን መሰረት በማድረጉና ኢትዮጵያ የምትከተለው ያልተማከለ አስተዳደር ዘውጌን መሰረት ባደረገ መመዘኛ የተካለለ በመሆኑ በሃገሪቷ ላይ ከፍተኛ የብሄራዊ ደህንነት ስጋት ሊደቅን ችሏል። ይህም በተለያዩ ዘውጌ ማህበረሰቦች መካከል መቃቃርና ግጭት እንዲቀሰቅ እንዲሁም ልዩነቶች እንዲሰፉ አድርጓል። ህገ መንግስቱም ዜጎችን እንደ ዜጋ የማይቀበል መሆኑ ተጨምሮበት በመንግስታዊ የፖለቲካ ስርአቱ ውስጥ ዜጎች ባይተዋር ሆነዋል። ዜጎች በዜግነታቸው ምክንያት ማግኘት የሚገባቸውን ማንኛውም ነገሮች እንዳያገኙና እንዲገለሉ አድርጓል።
- የዘውግ ጽንፈኝነት አንዱ የሃገራችን የብሄራዊ የደህንነት ስጋት ነው። በቅርቡ እያቆጠቆጠ ያለው የሃይማኖት ጽንፈኝነት በአሁኑ ሰአት ከምናልባታዊ የብሄራዊ የደህንነት ስጋት ወደ ተጨባጭ የደህንነት ስጋት እየተቀየረ ይገኛል። የዘውግ እና ሃይማኖት ማንነት ላይ የሚደረግ ጥቃቶች እየተበራከቱ መምጣታቸው ወደ የብሄራዊ የደህንነት ስጋት ደረጃ ላይ እንዲደርስ አድርጎታል።
- የክልልል ልዩ ሃይሎች የተደራጀ የጦር አቅም እየፈጠሩ መምጣት ሌላ ሊነሳ የምገባ የብሄራዊ የደህንነት ስጋት ነው።
- ድህነት አንዱና ለብዙ ችግሮች ምክንያት እየሆነ የመጣ የብሄራዊ የደህንነት ስጋት ነው። በተለይ ከፍተኛ የወጣት ስራ አጥነት እና የኑሮ ውድነት የብሄራዊ ደህንነት ስጋቶች ሆነዋል።
- ኢኮኖሚያዊ አሻጥሮች እና ከህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ጋር የተያያዙ ችግሮች የብሄራዊ ደህንነት ስጋቶች ደረጃ ደርሷል።
- የሳይበር ወንጀሎች አይነት እና ደረጃ እየተበራከቱና እያደጉ መምጣት ሌላው የብሄራዊ ደህንነት ስጋት እንዲሆን አድርጎታል።
- የብሄራዊ ደህንነት አስፈጻሚ አካላት ደካማ የስራ አፈጻጸም እና የአቅም ችግር ምክንያት ሃገሪቷ ለብሄራዊ የደህንነት ስጋቶች እያጋለጧት ይገኛሉ።
- የወደብ አለመኖርና በአንድ ወደብ ላይ ብቻ ጥገኛ መሆናችን የተጋላጭነት ደረጃችንን ከፍተኛ በማድረጉ የተነሳ የብሄራዊ የደህንነት ስጋት ውስጥ ሊካቱ የሚችሉ ያልተሻገርናቸው የደህንነት ስጋቶች ናቸው።

የውጭ የደህንነት ስጋቶች፤ ከውጭ የሚመጡ ስጋቶችን ቀጠናዊና አለማቀፋዊ ስጋቶች በማለት መክፈል ይቻላል። ቀጠናዊ ስጋቶች በተለይ ኢትዮጵያ በምትገኝበት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የሚከሰቱ ናቸው። በድንበር ከምንጋራቸዉ ሃገራት የሚመጡ ስጋቶች ለኢትዮጵያ በጣም ቅርብ ስጋቶች ይሆናሉ። ከዚያ በተጨማሪ ደግሞ በአለም ላይ ከሚኖረዉ የፖለቲካ ፍላጎት ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያን ስጋት ውስጥ የሚከቱ ጉዳዮች ከሩቅም ከቅርብም ሊመጡ ስለሚችሉ እነዚህን ስጋቶች አለምአቀፋዊ ብለን ልንጠራቸዉ እንችላለን። በመሆኑም ዋና የሚባሉ የውጪ የደህንነት ስጋቶች እንደሚከተሉት ተቀምጧል፦

- በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የሚገኙ ሃገራት ተለዋዋጭ አሰላለፍ የሚከተሉ መሆኑ፤
- ከሌሎች ሃገራት ጋር ከምንጋራቸው የተፈጥሮ ሃብቶች ጋር በተያያዘ ጠላት ሆነው ሊነሱ የሚችሉ ሃገራት መኖራቸው፤
- በአፍሪካ ቀንድ የወደቁ፣ የተጋላጭ ደረጃቸው ከፍተኛ የሆኑና ባህሪያቸው ሊገመት የማይችሉ ሃገራት መኖራቸው፤
- የተለያዩ ሃያላን ሃገራትና የመካከለኛው ምስራቅ ሃገራት በቀጠናው ላይ ግልፅ የሆነ ፍላጎት ያላቸው መሆኑ፤
- በቀጠናው ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታ መኖሩ፤

ከላይ ዋና ዋና የሚባሉ ብሄራዊ የውስጥ እና የውጪ የደህንነት ስጋቶች ተዘርዝረዋል። የብሄራዊ የውስጥ ደህንነት ስጋቶች ውስጥ አንዱ ከሆነው የብሄራዊ ደህንነት አስፈጻሚ አካላት ጋር ተያይዞ የሚነሱ በርካታ ችግሮች አሉ። የብሄራዊ ደህንነት አስፈጻሚ አካላት የሃገሪቷን ሉአላዊነት፣ የህዝቡን ደህንነትና ብሄራዊ ጥቅም በማስጠበቅ ረገድ የማይተካ ሚና አላቸው።

እነዚህ አካላት ህግ እና ስርአትን በማስፈን የተረጋጋ ሃገር እንዲኖረን የሚያስችሉ ናቸው። የብሄራዊ ደህንነት አስፈጻሚ አካላት ውስጥ የሚታዩ ችግሮች የብሄራዊ የደህንነት ስጋት በመሆናቸው ዋና ዋና የሚባሉትን የብሄራዊ ደህንነት አስፈጻሚ ተዋናዮች ላይ ያሉ ስትራቴጂያዊ ችግሮችን እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፦

የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት (ፓርላማ) የሰላምና ደህንነት ቋሚ ኮሚቴ፤ ፓርላማው ህግ የማውጣት ስልጣን ያለው አካል ነው። የሰላምና ደህንነት ቋሚ ኮሚቴ በፓርላማው ውስጥ ከብሄራዊ ደህንነት ጉዳዮችና ከህግ ማስከበር እንዲሁም ከውጪ ግንኙነት ስራዎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን እንዲከታተል በሕግ አውጪው አካል የተሰየመ ነው። የህግ ማስከበር እና የብሄራዊ ደህንነት አስፈጻሚ አካላት በአላቸው ሀላፊነት ልክ ስራዎችን እየሰሩ እንደሆነ ይከታተላል፤ ቁጥጥር ያደርጋል። እንዲሁም የብሄራዊ ደህንነት አስፈጻሚ አካላትን ተጠያቂነት ያረጋግጣል።
የፓርላማ የሰላምና ደህንነት ቋሚ ኮሚቴ ከላይ የተጠቀሱትን ሀላፊነቶች ቢኖሩትም በተግባር እነዚህን ሀላፊነቶች የሚመጥኑ ስራዎችን ሲሰራ አይታይም። ይህ ቋሚ ኮሚቴ ለስም ብቻ ያለ ነው ማለት ይቻላል። ተቋማዊ አደረጃጀትም የለውም። ሌላው ቀርቶ የብሄራዊ ደህንነት ጉዳዮችን ያሉባቸው ህጎች በአስፈጻሚው አካል ለፓርላማ በሚላክበትና ለዚህ ቋሚ ኮሜቴ በሚመራበት ጊዜ ያለው ሚና እንኳን በጣም አናሳ ነው። የቋሚ ኮሚቴው ጽ/ቤት በባለሙያዎች የተዋቀረ ባለመሆኑ የሚጠበቅባቸውን መሰረታዊ ስራዎች እንኳን በአግባቡ ማከናውን አይችሉም። የፓርላማ ቋሚ ኮሚቴዎች በአግባቡ የመከታተል እና የመቆጣጠር ሀላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው የአስፈጻሚ አካላትን ተጠያቂነት ማረጋገጥ አልቻሉም። ተቋማዊ ቅርጽ የላቸውም፤ በብቁ ባለሙያዎች ተዋቅረው ስራዎቻቸውን በአግባቡ አይሰሩም።

የብሄራዊ ደህንነት ካውንስል፤ የብሄራዊ ደህንነት ፖሊሲ አተገባበር በርካታ የመንግሥት ተቋማት ቅንጅታዊ ስራ የሚጠይቅ ነው። የብሄራዊ ደህንነት ካውንስል በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ ሲሆን የመንግስት ሥራ አስፈጻሚና የሚመለከታቸው አካላት አሉበት። የብሄራዊ ደህንነት ካውንስል ከብሄራዊ ደህንነት ፖሊሲ አተገባበር ጋር ተያይዞ የሚከናወኑ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች እና ስትራቴጂያዊ ኦፐሬሽኖችን እየተከታተለ የአፈጻጸም ውሳኔዎችን የሚወስን አካል ነው። ካውንስሉ በተለያየ ጊዜ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ከመምከር ውጪ በተቋም ደረጃ ተደራጅቶ የሚጠበቅበትን ሚና እየተወጣ አይደለም። የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሄራዊ ደህንነት ጉዳዮች አማካሪ በዚህ ካውንስ ላይ ሊኖረው የሚገባው ሚና እየተወጣ አይደለም። ይህ ካውንስል የራሱ ጽ/ቤት እንኳን የሌለው በመሆኑ በቋሚነት ስራዎችን ማከናወን እንዳይችል ሆኗል። የብሄራዊ ደህንነት ጉዳዮችን በዘፈቀደ ሚመሩበት ሁኔታ ተፈጠሯል።
የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሄራዊ ደህነት አማካሪ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሄራዊ ደህንነት ፖሊሲ አተገባበር ጋር ተያይዞ ከፍተኛ የመወሰን ስልጣን በህግ ተሰጥቷቸዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚወስኑት ውሳኔ የአገሪቷን ደህንነት እና ብሄራዊ ጥቅም ከማስጠበቅ ጋር የተቆራኘ ነው። አሁን ያለው የጠቅላይ ሚኒስትሩ የደህንነት አማካሪ ጽ/ቤት የተወሰኑ ባለሙያዎች (በቂ አይደለም) ቢኖሩበትም የሚፈለገውን ያህል ስራዎች እየሰራ አይደለም። ውጤታማም አይደለም። በጽ/ቤቱ ያሉት የተወሰኑ ባለሙያዎች የብቃት ደረጃቸው አናሳ ነው። የጠቅላይ ሚኒስትሩ የደህንነት አማካሪዎች በተለያየ ጊዜና በፍጠነት ነው የሚቀያየሩት። ይህን የጠቅላይ ሚኒስትሩ የደህንነት አማካሪ ጽ/ቤትን ያልተረጋጋ እና አትኩሮት የሌለው እንዲሆን አድርጎታል።
ደህንነት ማህበረሰብ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የደህንነት ማህበረሰብ የሚል ምልከታ (concept) የለም። በመሆኑም የትኛው ተቋም የደህንነት ማህበረሰቡ አባል እንደሆነ መለየት አልተቻለም። የደህንነት ማህበረሰብ ምልከታ ባለመኖሩ ምክንያት የመረጃ እና ደህንነት ተቋማት ስትራቴጂያዊ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራርን ሊተገብሩ አልቻሉ። እንዲሁም የተቀናጀ ስትራቴጂያዊ አቅጣጫ ለደህንነት ማህበረሰቡ እንዳይኖር አድርጎታል። የመረጃና ደህንነት ተቋማት እራሳቸው በመሰላቸው መንገድ እንቅስቃሴዎችን የሚያደርጉት።

የሰላም ሚኒስተር መቋቋምን ተከትሎ ሲቪል የመረጃና ደህንነት ተቋማት እንዲሁም የፌደራል ፖሊስን ጨምሮ ለሚኒስተር መስሪያ ቤቱ ተጠሪ እንዲሆኑ ተደርጓል። እነዚህ ተቋማት በተጠያቂነት መንፈስና በህግ አግባብ ስራቸውን እያከናወኑ እንደሆነ የመቆጣጠር እና የመከታተል ሀላፊነት አለበት። የሰላም ሚኒስተር ይህን ሃላፊነት በአግባቡ እየተወጣ አይደለም። ሰላም ሚኒስተር በስሩ ካሉ ዘርፎች ውስጥ የብሄራዊ ደህንነት አስፈጻሚ አካላትን በበላይነት የሚቆጣጠረው አካል የህግ ማስከበር ዘርፍ ነው። ይህ ዘርፍ በብሄራዊ ደህንነት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ልምድ ባላቸዉ ባለሙያዎች የተዋቀረ አይደለም። ይህን ዘርፍ በሚኒስተር ዴኤታ የሚመሩት እራሱ የህግ ማስከበር እና ከብሄራዊ ደህንነት ጉዳዮች ጋር ምንም ትውውቅ የሌላቸው ናቸው። የሰላም ሚኒስተር ካለው የመደበኛ እና የፐሮጀክት በጀት ማለትም 2.4 ቢሊዮን ብር በላይ ከሆነ በጀት ውስጥ ለህግ ማስከበር ዘርፍ የተመደበው 16 ሚሊዮን ብር ብቻ ነው። ይህም የደህንነት ተቋማት እና የፌደራል ፖሊስ

ስራዎችን ለሚከታተል አካል የተመደበውን በጀት ስናየው ከህግ ማስከበር ጋር ተያይዞ ሚኒስተር መስሪያ ቤቱ አነስተኛ አትኩሮት እንዳለው የሚያሳይ ነው።
በሰላም ሚኒስተር ስር ካሉ የህግ ማስከበር እና የብሄራዊ ደህንነት አስፈጻሚ አካላት ስንመለከት፡-

የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት መስሪያ ቤት፤ የደህንነቱ ዋና መስሪያ ቤት በተለያዩ ዘርፎች የተዋቀረ ነው። የደህንነቱ ዋና መስሪያ ቤት ባለፉት ሁለት አመታት ሶስት ሀላፊዎች ተፈራርቀውበታል። ይሄም መስሪያ ቤቱ እንዳይረጋጋ አድርጎታል። መስሪያ ቤቱ በፊት ከነበረው አደረጃጀት እና አሰራር አንጻር ከፍተኛ ችግር ውስጥ ያለ ተቋም ነው። ይህ ተቋም በተለያየ ጊዜ የተመደቡ ሀላፊዎች ሪፎርም ሊያደርጉ ቢሞክሩም የሚፈለገውን ውጤት ሊያመጡ አላስቻላቸውም። ተቋሙ መሰረታዊ የሆኑ የመዋቅር ችግሮች ያሉበት ተቋም ነው። የደህንነቱ መስሪያ ቤት የሙያ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ አጠያያቂ የሆነበት ነው። ከምልመላ ጀምሮ ከአሰራር ጋር የተያያዙ እና መዋቅራዊ በሆኑ ችግሮች ተተብትቦ ይገኛል። ተቋሙ የተጨባጭና ምናልባታዊ የስትራቴጂዊ እና ስልታዊ የስጋት ትንተናዎች ላይ ከፍተኛ ችግር እንዳለበት እስከ አሁን እየተፈጠሩ ካሉ ችግሮች በደንብ መረዳት ይቻላል። ባለፉት 27 አመታት ባለን የመረጃ እና ደህንነት ልምድ በተለይ ከለውጡ በኋላ በዚህ መስክ ላይ ያለን የአቅም ደረጃ በጣም የሚያሳሳብ አገርንም ፈተና ላይ ሊጥል እንደሚችል ይታመናል።

ፌደራል ፖሊስ፤ ፌደራል ፖሊስ በዋናነት ከህግ ማስከበር ጋር ተያይዞ የወንጀል መከላከል እና የወንጀል ምርመራ ዘርፎች ከፍተኛ ሚና አላቸው። በሃገራችን ከህግ ማስከበር ጋር ተያይዞ የሚነሱ ዘርፈ ብዙ ችግሮች አንዱ የዚህ ተቋም ወንጀል የማስቀረት ወይም የመከላከል ተግባራት ጋር በተያያዘ ያለበት ድክመት ነው። በተለይ የፖሊስ መረጃ አካሉ ደካማ መሆን የብሄራዊ ደህንነት ስጋት የሆኑ ከፍተኛ ችግሮች ሲከሰቱ ነበር። የፌደራል ፖሊስ ሙያዊ ብቃቱን ለማዘመን በቅርቡ ባወጣው የፖሊስ ዶክትሪን በርካታ አዎንታዊ የሆኑ ጉዳዮችን በዶክትሪኑ እንዲሰፍር ተደርጓል። የፖሊስ ዶክትሪኑ ሙያዊ የሆነ የፖሊስ ኃይል ለማፍራት ከፍተኛ አጋዥነት አለው። ይህ እውነታ እንዳለ ሆኖ የፖሊስ ዶክትሪኑ የፌደራል ፖሊስን የህግ ማስከበር አካል ብቻ አድርጎ ለማየት መሞከሩ አንዱ ችግር ነው። የፌደራል ፖሊስ ህግ የማስከበር ሀላፊነቱን የሚወጣው ከብሄራዊ ደህንነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችንም ጭምር ያካተተ ቢሆንም ፌደራል ፖሊስ እንደ የደህንነት ማህበረሰብ አካል አለመቆጠሩ ዋነኛው የችግሩ ምንጭ ነው። በመሆኑም የፌደራል ፖሊስን ከደህንነት ማህበረሰብ ስራዎች አንጻር ያሉበትንም ሀላፊነቶች በሚገባ እየተወጣ አይደለም። እስካሁን ፌደራል ፖሊስ፤ የሚመለከት የብሄራዊ ደህንነት ጉዳዮች በምን መልኩ እንደሚያስተናግድ ግልጽ ባለመሆኑ ብዙ ክፍተቶች ሲፈጥሩ እየተስተዋለ ነው።

መከላከያ፤ የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል በአዋጅ ዝ00/2019 አማካኝነት የምድር ኃይል፤ የአየር ኃይል እና የባህር ኃይል እንደሚኖረው ይደነግጋል። እንዲሁም የሳይበር ኮማንድ ሊያቋቁም እንደሚችል ይገልጻል። ይህን አዋጅ መሰረት አድርጎ በወጣው የመከላከያ ስትራቴጂ የምድር ኃይል፤ የአየር ኃይል፤ የባህር ኃይል፤ የሳይበር ኮማንድ እና የተጠባባቂ ጦር መከላከያ እንደሚኖረው ያስቀምጣል። የመከላከያ ሚኒስተር የመከላከያ ኃይልን (defense force) በበላይነት የመቆጣጠር (oversee power) እና በህግ አግባብ ስራውን እያከናውነ እንደሆነ የመከታተል ሀላፊነት ተሰጥቷል። የመከላከያ ኃይል በጀት አቅርቦ የማጸደቅና በተቀመጠው በጀት ልክ ስራዎችን እያከናወነ እንደሆነ የመከታተል ሀላፊነቱ ለመከላከያ ሚኒስተር መስሪያ ቤት የተሰጠ ነው።

የመከላከያ ሚኒስተር መስሪያ ቤት የመከላከያ ኃይልን በበላይነት የመቆጣጠር ስልጣን ያለውን ያህል በአግባቡ የክትትል ስራውን ሲያከናውን አይታይም። በህግ የተሰጣቸው የስራ ክፍፍል ቢኖርም በትግበራ ሂደት ላይ ማን ምን አይነት ሚና መጫወት አለው በሚለው ላይ የእርስ በርስ መጠራረስ ይታያል። መከላከያ ሚኒስተር የመከላከያ ኃይል የሚተገብራቸውን የመከላከያ ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችን በተግባር ላይ እየዋሉ እንደሆነ የመከታተል ሀላፊነት ቢኖርበትም፤ ብዙን ጊዜ የመከላከያ ኃይል የመከላከያ ሚኒስተር መስሪያ ቤትን ሀላፊነት በመተላለፍ በእራሱ ሲንቀሳቀስ ይታያል። ይህም የመከላከያ ሀይሉ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ሀላፊነቱ ባልሆነ ጉዳይ ላይ ሚኒስተር መስሪያ ቤቱን ሲሸፍን (over shadow) ይታያል።

የመከላከያ ሚኒስተር የመከላከያ ኃይልን የመቆጣጠር (inspection) ሀላፊነቱን በሚገባ እየተወጣ አይደለም። በመከላከያ ሚኒስተር ስር የቁጥጥር (inspection) ዳይሮክቶሬት ያለ ቢሆንም ስራውን በሚገባው ደረጃ እየሰራ እንዳልሆነ ከመከላከያ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን ላስተዋል በቀላሉ የሚረዳው ጉዳይ ነው። በመከላከያ ሚኒስተር ስር የሕዝብ ግንኙነት ዳይሮክቶሬት ቢኖርም በተለያዩ ጊዜ ከሕዝብ ግንኙነት ስራዎች ጋር ተያይዞ በርካታ ያለመናበብ እና ሌሎች ችግሮች የሚስተዋሉበት ነው። የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ብዙ አዎንታዊ የሆኑ ስራዎችን እያከናወነ የሚገኝ ቢሆንም

የሚጠበቅበትን ሀላፊነት በሚገባ እየተወጣ ነው ማለት አይቻለም። ይህ አካል ሀላፊነቱን በተጠና እና ሙያዊ በሆነ መንገድ እየተገበረ አይደለም። ባጠቃላይ መከላከያ ከሙያዊነትን ጋር ተያይዞ በርካታ ችግሮች እንዳሉበት ይታወቃል።

ከመከላከያ ሃይላት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ዋና ዋና ችግሮችን በተወሰነ መልኩ እንደሚከተለው ይቀርባል፦

- ከብሄራዊ ደህንነት ካውንስል የሚመጡ የብሄራዊ ደህንነት እና የስትራቴጂያዊ መረጃ ቅደም ተከተሎች የሚመነጭ እና የመከላከያ ኃይል ካውንስል የሚያጸድቀው የመከላከያ ስትራቴጂያዊ የመረጃ ቅደም ተከተሎች በመከላከያ አሰራር ውስጥ እስካሁን የለም። እንደዚህ አይነት ጉዳዮች በመከላከያ ውስጥ በዘፈቀደ የሚከናወን ነው። ይህም መከላከያ ተቋማዊ በሆነ መንገድ ስራዎችን እንዳያከናውን እንቅፋት ሆነውበታል።
- በጠቅላይ መምሪያ ስራ ካሉ በርካታ ዋና መምሪያዎች ውስጥ የመከላከያ መረጃ ዋና መምሪያ አንዱ ነው። ይህ ተቋም ከፍተኛ ችግር ያለበት ነው። ከፍተኛ ሙያዊነት የሚጠየቅበት ዋና መምሪያ ቢሆንም የሚጠበቅበትን ያክል እየሰራ እንዳልሆነ ይታወቃል። በተለይ የተጨባጭ እና ምናልባታዊ ስትራቴጂያዊ ስጋቶችን በመተንተን ሃገርን እና የወገን ኃይልን ከማንኛውን አይነት አደጋ የማስቀረትና የመከላከል ሀላፊነት ያለበት ቢሆንም ይህን ስራውን ግን በአግባቡ መወጣት የሚችልበት ደረጃ ላይ አይደለም ያለው። እስካሁን እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮችን በደንብ ብንመረምራቸው አብዛኛዎቹ የመረጃ ውድቀት (Intelligence failure) ናቸው። ይህ ተቋም እንደተቋም እየሰራ አይደለም። ከስትራቴጂያዊ መረጃ ማሰባሰብ ጀምሮ እስከ የትንተና ውጤት አቅርቦቱ ድረስ በውድቀት የተሞላ ነው። የመከላከያ መረጃ ዋና መምሪያ መዋቅራዊ በሆኑ ችግሮች የተተበተበ ነው።
- የመከላከያ ኃይል የተለያዩ ሃይሎቹን የሚያሰፍርበት (deployment)፣ መዋቅሩን ማዕከል የሚያደርግባቸውን ቦታዎች እና የኃይል ስምሪት አካባቢዎች በተጨባጭ እና ምናልባታዊ የስትራቴጂያዊ አደጋ እና ስጋት ትንተና ላይ ተመስርቶ የመፈጸም ችግሮች አሉበት።
- ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የውጪ ምንዛሪ የመሳሪያ ግዢ ታወጣለች። አሁን ድረስ የነፍስ ወከፍ መሳሪያዎችን እየገዛን እንገኛለን። ከነፍስ ወከፍ እስከ ቀላል ተተኳሽ መሳሪያዎች ድረስ በሃገራቸን ሊመረት ሚችልበትን እና እራሳችንን ከመቻል አልፈን ለአካባቢ ሃገራት መሳሪያዎችን መሸጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ተነድፎ መንቀሳቀስ አልተቻለም። ከዚህ በፊት በርካታ ሙከራ የተደረገ ቢሆንም በኢትዮጵያ ብራንድ የሚጠራ መሳሪያዎችን ማምረትና እራሳችንን መቻል አልቻልንም። በቅርቡ እንኳን የሪፐብሊካን ጋርድ ወታደሮች የታጠቋቸውን መሳሪያዎች ከውጪ ያስመጣናቸው ናቸው። በመሳሪያ አቅርቦት እራሳችንን እንድንችል የሚያደርግ የመሳሪያ ቴክኖሎጂ (weapon technology) ምርምር የሚደረግበት የመሳሪያ የምርምር ማዕከለ መገንባት አልተቻለም።

2.1.3. ከፖለቲካ

ባለፉት ሰላሳ አመታት በተለይም ባለፉት ሁለትና ሶስት አመታት አገራችን ውስጥ የታየው የፖለቲካ ቀውስ ህዝብን ከህዝብ ጋር ያጋደለ፣ሚሊዮኖችን ያፈናቀለና በአገራችን አንድነት ላይና በኢትዮጵያ ህዝብ የረጂም ግዜ የአብሮ መኖር ታሪክ ላይ ከፍተኛ አደጋ ያጠላ አደገኛ ቀውስ ነው። ይህ ቀውስ የአንድ ሥርዓት ቀውስ አይደለም፣ ባለፉት ሃምሳ አመታት ከሥርዓት ወደ ሥርዓት እየተንከባለለም እየባሰበትም የመጣ ቀውስ ነው። የዛሬዋ ኢትዮጵያ የሦስት እጅግ በጣም የተለያዩ መንግስታት የፖለቲካ ምስቅልቅል ውጤት ናት። የኢትዮጵያ ችግሮች በአይነትም በመጠንም ብዙ ናቸው፣ ሆኖም ከችግሮቻችን ሁሉየከፋውና የሌሎች ችግሮች ሁሉ ምንጭ የሆነው የፖለቲካ ሥርዓታችን የተዋቀረበት መንገድ ወይም ፖለቲካችን የነባበት ቀውስ ነው። አገራችንከዚህየፖለቲካቀውስነጻመሆንእስካልቻለችድረስ ወይም የአገራችንን ፖለቲካ አከመን ከዚህ ውስብስብ ቀውስ ውስጥ ጎትተን ካላወጣነው ለኤኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮቻችንመፍትሄማግኘትአለመቻላችን ብቻ ሳይሆን የአገራችን ህልውና እራሱ አደጋ ላይ የወደቀ ይሆናል።

ህገ መንግስት- ብዙዎቹ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግሮች የተቀዱት አሁን በስራ ላይ ካለው ህገ መንግስት ነው። ከግለሰብ መብት ይልቅ ለቡድን መብት የተሰጠው ትኩረት፣ መሬትን ያክል ትልቅ የኤኮኖሚ መሳሪያ በህግ የታሰረ እንዲሆን ማድረጉ፣ ቋንቋን እና ብሔርን መሰረት ያደረገ የፌዴራል ሥርዓት መፍጠሩ፣ ለብሔር ብሔረሰቦች ከግዴታ ጋር ያልተያያዘ እስከመገንጠል የሚደርስ ልቅ መብት መስጠቱ እና ባጠቃላይ የአገርን ሉዓላዊነት ከዜጎች ቀምቶ ለብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች መስጠቱ የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ዛሬ አገራችን ውስጥ ለሚታዩ ትልልቅ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮች ዋና ምንጭ መሆኑን ያሳያል። ስለዚህ ይህ ህገ መንግስት እስካልተሻሻለ ድረስ መሰረታዊ የሆኑ የፖለቲካ ችግሮቻችንን ማስወገድ ሊሳነን ይችላል።

ባንዲራ፤ባንዲራ በዘመናዊ አገረ-መንግስት ግንባታ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት፣ በአንድ አገር ውስጥ የሚኖር በቋንቋ፣ በባህልና በሃይማኖት የሚለያይ ህዝብ የአንድ የጋራ የፖለቲካ ማህበረሰብ አባል መሆኑን የሚገልጽ የአንድነት፣ የአብሮነት፣ የመስዋዕትነትና የአገር ቀጣይነት ምልክት ነው። የኢትዮጵያ ባንዲራም ይህንን በተመለከተ እያንዳንዱ ቀለም የሚናገረው የራሱ ታሪክ አለው። ሆኖም የህወሓት/ኢህአዴግ መንግስት የኢትዮጵያ ባንዲራ አራንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ መሆኑን በህገ መንግስት ድንጋጌ ውስጥ እንዲገባ ቢያደርግም፣ ባንዲራው ላይ የአብሮነታችን መገለጫ የሚሆን አርማ የህዝን ፍላጎት በተከተለ መንገድ ማድረግ ሲገባው፣ ይህንን ባለማድረጉና ብሔራዊ ባንድራችንን በተመለከተ ወጥ የሆነ አገራዊ ፖሊሲ ባለመኖሩ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ህዝብ "ባንድራዬ" ብሎ አደባባይ ተሸክሞ የሚወጣው አርማ እንደየአካባቢው ይለያያል። ይህ መለያየት አገራዊ አንድነትን እና የህዝብ ለህዝብ መቀራረብን የሚያዳክም በመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ብሔራዊ ባንድራችንን በተመለከተ አፋጣኝ ውሳኔ መወሰን አለበት ብሎ ኢዜማ ያምናል።

የሕዝብ የስልጣን ባለቤትነት ጥያቄ- የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪኩ የሱን ፈቃድ ጠይቀው ወደ ሥልጣን የመጡና መብትና ነጻነቱን አክብረው መሰረታዊ የኤኮኖሚና ማህበራዊ ፍላጎቱን ያሟሉት መሪዎች ኖረውት አያውቅም። ዛሬም ዴሞክራሲና ፌዴራሊዝም አለህ ተብሎ ከተነገረው ከ30 አመት በኋላም የኢትዮጵያ ህዝብ በማዕከለም በአካባቢም ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የመረጣቸውና ለሱ ተጠያቂ የሆኑ መሪዎች የሉትም። የኢትዮጵያ ህዝብ ሰብዓዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ መብቶቹ ተከብረዉ የተሟላ ቁሳዊና መንፈሳዊ ህይወት መኖር እንዲችል ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት ያስፈልገዋል፣ ጠንካራ መንግስት ሲባል ጡንቻውን አፈርጥሞ ህዝብን የሚረግጥ መንግስት ማለት አይደለም። ይልቁንም ጠንካራ መንግስት ሲባል በህዝብ ተመርጦ የህዝብን ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶች ለማስከበርና የህዝብን የደህንነት፣ የኤኮኖሚና ማህበራዊ ፍላጎቶች ለማሟላት አቅም ያለው መንግስት ማለት ነው።

እንደ ሀገር መድረስ ወደምንፈልግበት ከፍታ ለመድረስ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ብቻ ሳይሆን በሁሉም ያስተዳደር ደረጃ ያሉ የመንግሥት አካላት በሚኖሩበት አካባቢ ህዝብ የተመረጡ መሆን አለባቸው። የአካባቢ መሪዎች በህዝብ ሲመረጡ የስልጣን መሰረታቸው የመረጣቸው ህዝብ ስለሆነ ተጠያቂነታቸውም ለመረጣቸው አካባቢ ህዝብ ይሆናል። እንዲህ አይነት የቅርብ ተጠያቂነት ሲኖር በአንድ በኩል መሪዎች የመረጣቸውን ህዝብ ላለመበደል ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ህዝብ ከመንግሥት ጋር ያለው ቁርኝት የጠበቀ ይሆናል። ህዝብና መንግስት በቅርበት ተገናኝተው በቅንጅት ሲሰሩ ደግሞ መንግሥት መስራት ያለበትን የአገር ሉአላዊነትን ማስጠበቅ፤ ሰላም ማስፈን፤ማህበራዊ ደህንነትን ማስከበር፣ የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት...ወዘተ ስራዎች ካለብዙ ውጣውረድ በሙሉ አቅሙ መስራት ይችላል። ይህም ሁሉ ሆኖ መንግሥት ስራውን ሲሰራ ሊሳሳትና አንዳንዴ አላስፈላጊ የሆኑ ባህሪያት ሊታዩበት ይችላል። ይህ በሚሆንበት ግዜ እንዲህ አይነት አዝማሚያዎችን የመቆጣጠርና የማስተካከል መብትና ሥልጣን የኔ ነው የሚል የባለቤትነት ስሜት የሚሰማው ሕዝብ መኖሩ እጅግ በጣም ወሳኝ ስለሆነ፣ ካሁን በኋላ አገራችን ኢትዮጵያ ሊኖራት የሚገባ መንግስታዊ የፖለቲካ ሥርዓት፣ በየደረጃው የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት ያረጋገጠ መሆን ይገባዋል።

ሰላምና መረጋጋት- አገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ ከምንም ነገር በላይ የሚያስፈልጋት ሰላምና መረጋጋት ነው፣ሰላምና መረጋጋት በችግሮቻችን ላይ ቁጭ ብለን ተወያይተን መፍትሄ ለማግኘትም ሆነ ለዕድገትና ልማት ፍላጎታችን አማራጭ የሌላቸው እሴቶች ናቸው። ሆኖም ለሰላምና መረጋጋት ዋስትና የሚሰጥ የፖለቲካ ሥርዓት መፍጠር ባለመቻላችን እጅግ በጣም የሚያስፈልገን የውስጥ ሰላማችንን ማስጠበቅ አልቻልንም። እኛ ኢትዮጵያዊያን ሀገራዊ ሰላምና መረጋጋት በግለሰብ ደረጃ እራሳችንን፣ ቤተሰባችንን እና ባጠቃላይ የምንኖርበትን ማህበረሰብ በህይወት ለማስቀጥል ከምናደረገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጀምሮ ለወደፊቱ እንደ እንደ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ መቀጠል የምንችለው በየትኛውም የሀገራችን ክፍል ሰላምና መረጋጋት ሲኖር ብቻ ነው። ስለዚህም ኢትዮጵያ ውስጥ ሊኖረን የሚገባው መንግስታዊ የፖለቲካ ሥርዓት ለአገራዊ ሰላምና መረጋጋት ቅዲሚያ የሚሰጥ፣ሰላምና መረጋጋትን ለማረጋገጥ ፍላጎቱም ችሎታውም ያለው መሆን መሆን ይኖርበታል።

ፍትህ፤ የዜጎች ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶች-

ዛሬ በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነጻነት የሰው ልጆች ትርጉም ያለው ኑሮ ለመኖር ከሚያስፈልጋቸው መሰረታዊ ፍላጎቶች ውስጥ ቀዳሚው ነው፣ እንዲያውም ነጻነቱን የተቀማ ሰው ሌሎቹን ፍላጎቶቹን ማሟላት አይችልም። የሰው ልጅ ከምንም አይነት ውጫዊ ኃይል ቁጥጥር ነጻ ሲሆን ብቻ ነው መጠየቅ፣ መመራመርና አዳድስ ሃሳቦችን እና ግኝቶችን ማመንጨት የሚችለው። ነጻ ሰው በመንግሥት ወይንም በባህል ተጽእኖ ተተብትቦ በፍርሀት ቆፈን ውስጥ አይኖርም። የአንድ አገር የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት፣ የኤኮኖሚ ግንባታ ሂደትና ዘመናዊነት ከዜጎች መብትና ነጻነት መከበር ጋር

በቀጥታ የተገናኘ ነውና፣ ኢዜማ እንደ ሀገር ያሉብንን የኢኮኖሚ፣የፖለቲካም ሆነ የባህል ችግሮች ለመፍታት ባጠቃላይ ከኋላ ቀርነት ለመላቀቅ የዜጎች በነጻነት መረጋገጥ አለበት የሚል የማያወላውል አቋም አለው።ይህ እንዲሆን አገራችን ኢትዮጵያ የዜጎችን ሰብዓዊ፣ፖለቲካዊና ሲቪክ መብቶች የሚያከብርና የሚያስከበር የፖለቲካ ሥርዓት ያስፈልጋታል።

በነጻነት ማሰብና ያሰቡትን በነጻነት መግለጽ የማይችሉ፣ በነጻነት መሰብሰብና መደራጀት የማይችሉና በፈለጉበት ቦታና ግዜ መንቀሳቀስ የማይችሉ ዜጎች የራሳቸውን ከእጅ ወደአፍ ኑሮ ለማሳካት ከመሯሯጥ አልፈው ትውልድ ተሻጋሪ የሆነ አገራዊ ኤኮኖሚ በመገንባት አይችሉም። አገራዊና ኤኮኖሚያዊ ሉዓላዊነታችንን ለማስከበር፣ ጠንካራ ብሔራዊ ኤኮኖሚ ለመገንባትና የህዝብን መሰረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ግዴታቸውንም የሚያውቁና የሀገር ባለቤትነትና የሀገር ፍቅር ስሜት ያላቸው ዜጎች መፍጠር መቻል አለብን። እንዲህ አይነት ዜጎችን ፍትህ፣ መብትና ነጻነትን ከመሳሰሉ መሰረታዊ የሰው ልጆች እሴቶች ውጭ ማሰብ አይቻልም።

ፌዴራሊዝም- ኢትዮጵያ በመዋቅር ደረጃ ከፌዴራሊዝም ጋር የተዋወቀችው በህወሓት የተመራው የብሔር ድርጅቶች ጥምረት አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ ከ1983 ዓም በኋላ ነው። በአዋጅ ከተመሰረተበት ከ1987 ዓም ጀምሮ አሁንም ድረስ የኢትዮጵያን ህዝብ ለሁለት ከፍሎ ያወዛገበውን እና ዛሬ በስራ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ፌዴራል ሥርዓት ህገ መንግስት ጽፎና ዘጠኝ ክልሎችን ሸንሽኖ ያዋቀረው በህወሓት የበላይነት የተመረውና በ1983 ዓም የተቋቋመው የሽግግር መንግስት ነው። የህወሓት/ኢህአዴግ መንግስት የአካባቢ አስተዳደሮችን (ክልሎች) ለመሸንሸን የተጠቀመው ብቸኛ መመዘኛ ብሔር ወይም ቋንቋ ነበር። ብሔር ብቸኛው መመዘኛ ሆኖ መቅረቡ ግዛትንና ማንነትን አቆራኝቷል፣ ለዘመናት አንድ ላይ በኖረ ህዝብ መካከል የልዩነት አጥር ሰርቷል፣ አገራዊ የዜግነት ስሜትን አዳክሞ አከራሪ ብሔረተኝነትን ፈጥሯል፣ ፌዴራሊዝም ከመመስረቱ በፊት ኢትዮጵያ ዉስጥ ያልነበረ የግዛት ባለቤትነትና ይገባኛል ጥያቄ ፈጥሯል። የእነዚህ ህዝብን ከህዝብ ጋር የሚያጋጩ አዳዲስ ሁኔታዎች መፈጠር ኢትዮጵያ ዉስጥ ህዝብ በብሔር እራሱን እየለየ ግጭትና ጦርነት ዉስጥ እንዲገባ ተደርጓል።

ኢዜማ እንደ አንድ የፖለቲካ ባለድርሻ፣ ፌዴራሊዝም ለኢትዮጵያ አስፈላጊ የመንግስት መዋቅር ነው ብሎ ያምናል። ሆኖም ኢትዮጵያ በፌዴራሊዝም ተጠቃሚ ትሆናለች ብሎ የሚያምነው መሰረታዊ የሆኑት የፌዴራሊዝም መርሆዎች ሲከበሩና ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለው የፌዴራል ሥርዓት አወቃቀር ክልሎችን፣ ማዕከላዊውን መንግስትና ባጠቃላይ ኢትዮጵያን እንደ አገር በሚጠቅም መልኩ እንደገና በአዲስ መልክ ቢዋቀር ነው የሚል ጠንካራ እምነት አለው። ፌዴራሊዝም ህዝብ በአካባቢው እራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ሥርዓት ነው ሲባል፣ ይህ እራስን በራስ የማስተዳደር መብት በክልል ደረጃ ብቻ ተወስኖ የሚቆም መብት አይደለም። እራስን በራስ የማስተዳደር መብት የሰው ልጆች ሁሉ ሊኖራቸው የሚገባ መብት ነው እንጂ፣አንድን ክልል ለአንድ ብሔር ብቻ በባለቤትነት በመስጠት ዜጎችን በገዛ አገራቸው ሁለተኛ ዜጋ ማድረግ አይደለም።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በዕድገት ወደኋላ የቀሩና በብሄርና በቋንቋ በተከፋፈሉ አገሮች ዉስጥ የኃብት ስርጭትና ክፍፍል ልዩነት፥ በኤኮኖሚ ዕድገት አለመመጣጠንና የግዛት ይገባኛል ጥያቄ፣ በክልሎች መካከል ግጭቶችን ከሚፈጥሩ ብዙ ምክንያቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ ኢዜማ ይገነዘባል። እንደዚህ አይነቶቹን በግልጽ የሚታዩ ችግሮች ለመቆጣጠር ኢትዮጵያ ውስጥ የፌዴራል ክልሎች ሲመሰረቱ ቋንቋ አንዱ እንጂ ብቸኛው መመዘኛ መሆን የለበትም ብሎ ያምናል። የህዝብ ብዛት፥ የቆዳ ስፋት፥ የመልማት አቅም፥ የተፈጥሮሀብት ብዛት፥ የሀብት ስርጭት፥ የአስተዳደር አመቺነት፥ የአብሮ መኖር ታሪክ፥ የታሪክ ትስስርና ኩታ ገጠምነት የተለያዩ የፌዴራል ክልሎችን ለመከለል እንደ መመዘኛ መታየት አለባቸው በሚል መነሻ ግልፅ የሆነ አማራጭ ያቀርባል።

2.1.4. ከኢኮኖሚ

ግብርናና ገጠር ልማት፤ የሀገራችን ኢትዮጵያ አብዛኛው ሕዝብ በገጠር የሚኖርና ኑሮውም በግብርና ሥራ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በግብርና ሥራ የተሰማራው አብዛኛው ገበሬ ኋላ ቀር በሆነ በዝናብ ላይ የተመሠረተ ግብርና የሚያካሂድና የተሻሻሉ የግብርና ግብዓቶችን በስፋትና በአግባቡ የማይጠቀም ስለሆነ ከሰብልና እንሰሳት ልማቱ የሚገኘው ምርትና ምርታማነት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በየዓመቱ ከ10% (እጅ) በላይ የሚሆነው ሕዝብ በዕለት የእህል እርዳታ ላይ ጥገኛ ሆኖ ይገኛል፡፡

የእንስሳት ሀብት ልማት ንዑስ ዘርፍም ያልተሻሻሉ ዝርያዎችን የሚጠቀም፣ በቂና በጥራት የሚቀርብ መኖ የሌለበትና የእንስሳት ጤና አገልግሎቱም የተዳከመ በመሆኑ ከዘርፉ ሊገኝ የሚገባው ምርትና ገቢ በበቂ እየተገኘ አይደለም፡፡ የሰውና

የእንስሳት ቁጥሩም በየጊዜው እየጨመረ በመሄዱ የግብርና ምርት ፍላጐቱን ለማሟላት ገበሬው የደንና የግጦሽ መሬቶችን በመመንጠር ለእርሻ አውሏቸዋል፡፡ የደን ምንጣሮውና የአፈር በዝናብ መታጠብ የአፈር ክለትና የተፈጥሮ ሀብቶችን መመናመን በማስከተሉ የአፈር ለምነት እየቀነሰ፣ የዝናብ ስርጭትና ብዛት እየተዛባ መጥቶ በርካታ የሀገራችን አካባቢዎች በድርቅ ተመትተዋል፡፡

የተፈጥሮ ሀብቱን ተንከባክቦ ለዘላቂ ልማት ለማዋል አግባብነት ያላቸው የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲና እስትራቴጅዎች ሕዝቡንና የተማረውን ሰው ባሳተፈ ሁኔታ ተቀርጸው ሥራ ላይ ባለመዋላቸው፣ አልፎ አልፎ ጥሩ የተባሉ የፖሊሲ ሰነዶች ቢወጡም በአግባቡ በየደረጃው ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ወደ ተግባር ባለመግባታቸው የግብርናው ዘርፍ ችግርን አልፈታም፡፡

የግብርና ሥራ ከመሬት የባለቤትና የመጠቀም መብት ጋር የተቆራኜ በመሆኑ ገበሬው በመሬቱ ላይ ለረጅም ጊዜ ሀብቱን አፍስሶ ውጤት ከሚያመጡ ሥራዎች ይልቅ ጊዜአዊና ዘለቄታዊነት በሌላቸው የግብርና ሥራዎች ላይ እንዲያተኩር በመደረጉ ለምርት አለማደግና ለተፈጥሮ ሀብቱ መመናመን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በእነዚህና ሌሎች የፖሊሲ ችግሮች የተተበተበው ግብርና እያደገ የመጣው ሕዝብ ተፈላጊውን የሥነ ምግብና የገቢ ፍላጐት ማሟላት አቅቶት ከውጭ ሀገር በሚመጣ የምግብ እርዳታ ላይ ጥገኛ ሆኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሀገራችን ሊመረቱ በሚችሉ ምርቶች ማለትም ስንዴ፣ ጥጥ፣ ዘይት፣ ወተትና የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶችን ከውጭ ሀገር በማስገባት በውጭ ሀገር ገንዘብ ጥሪት ላይ ጫና ተፈጥሯል፡፡

ግብርና ለአጠቃላይ ሀገራዊ ኢኮኖሚም 34.9% አስተዋጽኦ ያበረክታል ለ85% ሕዝብ የገቢ እና የምግብ ምንጭ፣ 80% የማያንስ ከውጭ ንግድ የሚገኘውን ገቢ የሚሸፈንና 70% የሀገር ሀብት የኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ ግብዓቶችን እንደሚሸፍን ይታወቃል፡፡ ግብርና ሀገራችን ኢትዮጵያ ለምታስበው የኢኮኖሚ እድገትና ሽግግር (Economic growth & Transformation) ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት ይታመናል፡፡ እንዲሁም ሀገሪቱ ባላት የተፈጥሮ ሀብት ተነጻጻሪ ጥቅም (Comparative advantage) ያላት በመሆኑ ግብርናን ለማዘመን በአግባቡ የተፈጥሮ ሀብቶቿን መጠቀም ከቻለች ዘላቂነት ያለው ልማት ለማካሄድ የተመቻቸ ሁኔታ ላይ ትገኛለች፡ዘርፉ ለኢኮኖሚ እድገትና ሽግግር የጀርባ አጥንት የመሆኑን ያክል በተገቢው የእድገት ደረጃ ላይ የማይገኝና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ዘርፍ ነው፡፡ ይህም በብዙ መለኪያዎች ሲታይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ ግብርና በአብዛኛው በዝናብ ላይ ጥገኛ የሆነ፣ የተሻሻሉ (ዘመናዊ) ግብዓቶችን የማይጠቀም፣ ኋላቀር የእርሻ ዘዴዎች የሚጠቀም፣ በከፍተኛ ደረጃ የተፈጥሮ ሀብቶቹን ያመናመነና ለከፍተኛ የተፈጥሮ አየር መዛባት የተጋለጠ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም በዘርፉ ላይ የሚደረገው ኢንቨስትመንት በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

የዘርፍ መገለጫ ከሆኑት ተግዳሮቶች መካከል አንዱ አነስተኛና የተበጣጠሰ የመሬት ይዞታ ለተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም አመቺ ካለመሆኑም ባሻገር ዝቅተኛ የሰው ኃይል ምርታማነት እንዲኖረው አድርጓል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ትክክለኛ የመሬት ፖሊሲ ተግባራዊ ባለመሆኑ የተነሳ የግብርናውን ዘርፍ ማዘመን አልተቻለም፡፡ እንድሁም ለዘርፉ የወጡ ፖሊሲዎች በተግባር ገበያ ተኮረ ያለመሆናቸውና በአብዛኛው በመንግሥት ቁጥጥር ስር የዋሉና የግል ሴክተሩን ያገለሉ በመሆናቸው ዘርፉ በተፈለገው ፍጥነት ማደግ እንዳይችል አድርገውታል፡፡ ዘርፉ እስካሁን ባለው ሁኔታ በከፍተኛ መሠረተ ልማትና በገበያ ትስስር እጦት የሚሠቃይ ከመሆኑም ባሻገር በደካማ ተቋማት አደረጃጀትና የሰው ኃይል ምደባ፣ ሙያን ያላማከለ የፓርቲ ጣልቃ ገብነት የተነሳ የሚፈለገውን እገዛ ሊያገኝ አልቻለም፡፡

በሌላ በኩል ዘርፉን ለማዘመን ቁልፍ ግብዓት የሆኑት እንደ ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና የትምህርት ሥርዓት በአግባቡ ተቀናጅተው የዘርፉን ችግር ሊፈቱ አልቻሉም፡፡ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እየታየ ያለው የሕዝብ ቁጥር ምጣኔ ከኢኮኖሚ እድገቱ ጋር ሲነጻጸር በከፍተኛ ደረጃ እያደገ በመምጣቱ የተነሳ በተለይ 73% የሆነው ወጣቱ ትውልድ በሥራ አጥነትና መሬት አልባ በመሆን እየተቸገረ ይገኛል፡፡ በዚህም የተነሳ ወጣቱ በቤተሰቡ ጥገኛና ለስደትና ለአጉል ሱሶች ተጋላጭ ሆኗል፡፡ ኢትዮጵያ ባላት እንስሳት ሀብት ብዛት “ከዓለም እስረኛና በአፍሪካ ነኛ” ብትሆንም ንፁስ ዘርፉ በችግር የተተበተበ ስለሆነና ከፍተኛ የከብት ቁጥር መኖሩ ለተፈጥሮ ሀብታችን መመናመን የራሱን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይዘርፉያለበትሁኔታሲታይመንግሥትግብርናንእንደወሳኝናትኩረትአቅጣጫአድርጐመውሰዱበጠንካራጐኑየሚታይቢ ሆንምበአተገባበር፣በበጀት፣በተቋምአደረጃጀትእናጥራትያለውየሰውኃይልአመዳደብደካማአፈጻጸምነበረው፡፡**በዚህ መነሻ የዜጎችን በምግብ ዋስትና እና ሥርአተ-መብል ዋስትና**፤ ማረጋገጥ ያልቻለች አገር ልትሆን ችላለች፡፡

ማዕድን፤ በኢትዮጵያ ባልፉት 2000 ዓመታት በባህላዊ መንገድ የደለል ወርቅ የማውጣት ሥራ ተግባራዊ ሲደረግ የቆየ ቢሆንም ከፍተኛ የማዕድን ልማት እስካሁን የለም፡፡ ልማዳዊ የወርቅ ማውጣት ሥራ ባብዛኛው በደላላማ በሆኑ የደቡብ፤ የምዕራብ እና የሰሜን የሀገሪቱ አካባቢዎች ሲሆን የሚከናወነውም ቁጥራቸው በርካታ በሆኑ በባህላዊ መንገድ በሚያመርቱ እና አነስተኛ አምራቾች ነው፡፡ በከፍተኛ ደረጃ የሚያመርተው ሚድሮክ ለገደምቢ የተባለው ኩባንያ ብቻ ነው፡፡ ጌጣጌጥ ደንጋዮች በስፋት የሚመርቱ ሲሆን ከዚህም 90 በመቶ ያህሉ የሚገኘው ከኦፓል ማዕድን ሲሆን የሚገኘውም በሰሜን ወሎ ዞን ነው፡፡ በቱሉ ካፒ እንዲሁም የወርቅ ምርት በኢንዲስትሪ ደረጃ ለማምረት እንቅስቃሴ አለ ነገርግን በካፒታል ዕጥረትና በደህንነት ችግር የተነሳ እስካሁን ሥራው አልተጀመረም፡፡

ከወርቅ በተጨማሪ ኢትዮጵያ በተለያዩ የኢንዱስትሪ ማእድኖች የበለጸገች አገር ናት፡፡ ነገር ግን በአብዛኛው በጥቃቅንና አነስትኛ ድርጅቶች ልማዳዊ በሆን አሠራር የሚመረት ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በኢንዱስትሪ ደረጃ ማመረት የሚቻል የፖታሽ ክምችት በአፋር ክልል ዳሎል አካባቢ የተገኘ ሲሆን አላና ፖታሽ የተባለ ድርጅት ሥራው ተጀምሮ ነበር ሆኖም እስካሁን የተገኘ ውጤት የለም፡፡ የማዕድን ዘርፉ ውጭ ምንዛሪ ከማምጣት አኳያ ብዙ የሚያግዝ ቢሆኑም ዘርፉ በዙ ትኩረት ስላልተሰጠው የሀገሪቷን ኢኮኖሚ ሊያግዝ አልቻለም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በአነስተኛ አምራቾች የሚወጣው ወርቅም ሆነ ጌጣጌጥ ድንጋዮች በኮንትሮባንድ ከ ሃገር ስለሚወጣ ሀገሪቱ ማኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ ልታገኝ አልቻለችም፡፡የጸጥታና የደህንነት ችግሮች፤ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር፤ የህግ ማቅፉ ኋላ ቅርነት፤ የመንገድና የኃይል አቅርቦት ደካማ መሆን ከሚጠቅሱት ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

ኢንዱስትሪ፤ አገራችን ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ መስክ ይህ ነው የሚባል መዋቅራዊ ሽግግር ማምጣት ባለመቻላችን በአገር ውስጥ ሊመረቱ የሚችሉ ከፍተኛ የፍጆታ እቃዎች ከውጭ እየገቡ ይገኛሉ፡፡ ይህ ማለት እጅግ ከፍተኛ የሥራ አጥ ያለባት አገር ኢትዮጵያ ለሌሎች አገራት የሥራ እድል እየፈጠረች መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ከፍተኛ እጥረት ያለብንን የውጭ ምንዛሪ እየተጠቀመ መንግሥት ለሌላ ሀገር ሥራ እየፈጠረ ይገኛል፡፡ ኢንዱስትሪዎች እንዳይስፋፉ፤ የተቋቋሙ ኢንዱስትሪዎችም በሙሉ ዐቅም እንዳይሰሩ ብዙ ማነቆዎች ያሉ ሲሆን፤ የጥሬ እቃ እና የሀይል አቅርቦት ዋንኞቹ ናቸው፡፡ እጅግ ብዙ ከዩኒቨርሲቲ የሚመረቁ ተማሪዎች ቢኖሩም ይህን ሊሸከም የሚችል የኢንዱስትሪ ልማት ደረጃ ላይ መድረስ አልቻልንም፡፡

ንግድ፤ በአገራችን ያለው ከፍተኛ የአቅርቦት ችግር፤ አማራቹ ከሸማቹ ጋር በቀላሉ እንዳይገናኝ በመሃል የሚኖሩ የተንዛዛ የንግድ ሥርዓቶች በከፍተኛ ሁኔታ ሸማቾችን አየጎዱ እንደሆነ ይታመናል፡፡ አገር ውስጥ ሊመረቱ የሚችሉ እጅግ ብዙ የሸቀጥ ዓይነቶች በውጭ ምንዛሬ ወደ አገር ውስጥ መግባታቸው፤ የኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋት፤ በቂ የኤክስፖርት እቃዎች ያለመኖር መሰረታዊ ችግሮች ናቸው፡፡

ቱሪዝም፤ ኢትዮጵያ በዓለም የቱሪዝም ሀብት አላቸው ከሚባሉ አገሮች ውስጥ ቀደምት ሥፍራ ያላት ሀገር ነች፡፡ የሚዳሰሱና የማይደሰሱ ቅርሶችን በዓለም ያስመዘገበች ሲሆን፤ እነዚህን ሀብቶች በተገቢው ለዜጎች ጥቅም በማዋል ረገድ እጅግ በጣም ወደኋላ ቀርታለች፡፡ እነዚህን ሀብቶች ለማልማት ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ባለመሆኑ፤ በቱሪዝም ሀብቶች አካባቢ የሚኖሩ ዜጎች ቦታውን ለልመና በማዋል የቱሪስት መስብዕነቱን እየጎዱትይገኛሉ፡፡ ለቱሪስቶች የቆይታ ጊዜ ማራዘሚያ የሚሆኑ ተጨማሪ መሰረተ ልማቶችና መዝናኛዎች እየተዘጋጁ አይደለም፡፡

መሠረተ ልማት፤

መንገድ፤ ኢትዮጵያ ወደብ የሌላት አገር ሰትሆን በአብዛኛው የንግድ እንቅስቃሴዎች በውጤታማ የመንገድ ዘርፍ የተመሰረተ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ባወጣው የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በአገሪቱ ከነበረው የ10 ሺ ኪሎሜትር መንገድ በእጠፍ በማሳደግ ወደ 220 ሺ ኪ፣ሜ እንደሚያሳድገው እቅድ ይዞ የነበረ ቢሆንም፤ አሁን ያለው የመንገድ ሽፋን 138 ሺ ኪሜ የማይበልጥ ነው፡፡ ይህ በእቅድ ተይዞ ከነበረው 35 ከመቶ ብቻ የተሰራ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ በገጠር መንገድ ሥራ ተይዞ የነበረው እቅድ ከዚህ በባሰ ደረጃ መፈፀም ያልተቻለ ሲሆን፤ ይህን ተከትሎ ዜጎች ወደ ክረምት ከበጋ አገልግሎት ወደሚሰጡ የሚደረግ ጉዞ አሁን ካለው የአንድ ሰዓት ተኩል ከአንድ ሰዓት ለመቀነስ የነበረው እቅድ ሊሳካ አልቻለም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በወጪ ንግድ የኤክስፖርት ዋጋ ሲያንር፤ በተመሳሳይ ከውጭ የምናስገባቸው እቃዎች ከፍተኛ የትራንስፖርት ክፍያ እንዲያስከፍሉ በማድረግ በምርቶችና አገልግሎቶች ላይ የዋጋ ጫና

እያሳደረ ይገኛል፡፡ መሰረታዊ አገልግሎቶችን ማለትም ጤናና ትምህርትን ወደ ዜጎች ለማቅረብ የሚደረገውን ጥረትም እጅግ በከፍተኛ ደረጃ ጎድቶታል፡፡

የመንገድ ሴክተሩ ከፍተኛ የአገር ውስጥና የውጭ መዋለ ንዋይ እየፈሰሰበት ያለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በዘርፉ ባለው ብልሹ አሰራር የተነሳ ኮንትራቶች በጊዜ ስለማያጠናቀቁ፤ ኮንትራቶች የሚሰጥበት አግባብ ግልፅነት የጎደለው እና በጥቅም ትስስር ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ዘርፉን በጣም ጎድቶታል፡፡ ግንባታዎች በአመዛኙ ከውጭ ኮንትራክተሮች ጋር የሚደረግ ሲሆን፤ ይህ በምንም ሁኔታ የቴክኖሎጂ ሽግግር ወደ አገር ውስጥ ለማምጣት በሚያስችል ሥርዓት እየተሰራ አይደለም፡፡

ባቡር፤ ኢትዮጵያ እንደሚታወቀው ባቡር በዓለም ላይ ሲመሰረት በቀደምትነት ተጠቃሚ ከሆኑ ሀገሮች አንዷ ነበረች፡፡ ይህ ከ700 ኪሎ ሜትር በላይ መንገድ ተገቢውን ጥገና እና አስተዳደር እንዳይኖረው በመደረጉ ሚኒሊክ ቢመጡ እስከሚያውቁት ድረስ አሮጌ እንዲሆን ተፈርዶበት ከቆየ በኋላ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ መጀመሪያ ሰሞን ምንም የባቡር መስመር እንደሌለ ተቆጥሮ ከዜሮ እንድንነሳ ተበየነብን፡፡ መንግሥት ባለፉት አሰር ዓመታት 2395 ኪሎ ሜትር አዲስ የባቡር መስመር እንደሚገነባ ለሕዝብ ተስፋ የሰጠ ቢሆንም ፤ከዚህ ውስጥ በአሁኑ ሰዓት ተጠናቆ በተገቢ ሁኔታ ግልጋሎት ከማይሰጠው የአዲስ አበባ ጅቡቲ እንዲሁም በከተማው ከፍተኛ ጭንቅንቅ በመፍጠር የሚታወቀው የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ውጪ በተግባር የዋለ ነገር አይታይም፡፡ በጅምር ላይ ያሉትም ቢሆኑ በከፍተኛ ችግር ላይ እንደሚገኙ የዕለት ከዕለት ዜና ማሞቂያ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ዕቅዱ ለመጀመር ነው እንጂ ስራ ላይ ለማዋል አይደለም ብለው ክርክር ካልጀመሩ በስተቀር የእውሸት ዕቅድ እንደነበር በግልፅ የሚታይ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ዕቅድ ሲታቀድ የመፈፀም፣ የፋይናንስ አቅም ታይቶ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አንፃር ገንዘብ ስለአላገኘን ወይም ባለሞያ አጥትን የሚለው በሙሉ ሰበብ ውሃ የሚቋጥር አይደለም፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖም አሁን በመገንባት ላይ ያሉት የባቡር መስመሮች ገንዘብ ያቀረበው የቻና መንግስት ኮንትራቱን ለራሱ ወስዶ በውድ ዋጋ የሚሰራው ሲሆን ይህ ገንዘብ በጥናት ላይ ተመርኩዞ ለመስራት ቢቻል ከዚህ ይበልጥ መስመር ሊገነባ እንደሚችል እሙን ነው፡፡

ኃይል አቅርቦት፤ እንደሚታውቀው ገዢው ፓርቲ ምርጫ ሲወዳደር የኤሌትሪክ ኃይል አቅርቦት አሳድጋለሁ በማለት ቃል ይገባል፤ ሆኖም ከምርጫው በኋላ ግን ህዝቡን በመናቅ ያለን የሀይል አቅርቦት ዝቅተኛ በመሆኑ በፈረቃ ኑሩ ለማለት ምንም ዓይነት ይሉኝታ የሌለው መንግሥት ነው፡፡ ሴክተሩ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ነው በማለት በጀት ተመድቦለት የሚንቀሳቀስ ቢሆንም በሙስና ተጨማልቆ ወደፊት ለመሄድ ያልቻል ዘርፍ ነው፡፡ ገዢው ፓርቲ በ2007 የሀይል አቅርቦትን 8000 ሜጋ ዋት እንደሚያሳድግ በዕቅድ አስቀመጠ ቢሆንም እስከ ዛሬ ግማሹን እንኳን ለማቅረብ የሚያስችል ደረጃ ላይ አይገኝም፡፡ የአባይ ወንዝ ላይ በመሰራት ላይ የሚገኘው ታላቁ የህዳሴ ግድብ በፍፁም ይህን ተግባር የሚፈፅሙት ዜጎች ናቸው ለማለት በማያስደፍር ሁኔታ የምስኪን እናቶች መቀነት ተፈቶ የተዋጣ ገንዘብ እንዲባክን ሆኖ በአሁኑ ሠዓት ለከፍተኛ የውጭ ጣልቃ ገብነት በር የሚከፍት የዲፕሎማሲ ኪሳራ ውስጥ ከቶን ይገኛል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ 8000 ሜጋ ዋት ሀይል አምርተን 75 ከመቶ የሚሆነው ዜጋ የሙብራት ተጠቃሚ ይሆናል ተብለን የነበረው ተስፋ በተስፋ ብቻ ከአስር ዓመት በላይ አስቆጥረናል፡፡ ኢትዮጵያ አሁንም ለዜጎቿ ሀይል ማቅረብ ያልቻለች አገር ሆና ቀጥላለች፡፡ የኢንዱስትሪ ልማታችን ጭምር ከዚህ ዘርፍ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ለኢንዱስትሪ ዘርፉ አለማድግና በሙሉ አቅም ያለመስራት ዋንኛው ምክንያት ነው፡፡

ውሃ አቅርቦት፤ ኢትዮጵያ ለግዙፍ አገራዊ እርሻዎች እና ለትንንሾቹ የገበሬ መሬቶቿ ማጠጫ ሊሆን የሚችል የተትረፈረፈ የውሃ ሃብቷን በመጠቀም፤ አሁን ያለውን አመታዊ የግብርና ምርቷን፤ በሺዎች እጥፍ ማብዛት፤ ስለዚህም ራሷን ችላ ህዝቧን መመገብ፤ ከራሷ አልፋም፤ የቀጥታ-ከማሳ እና በኢንዱስትሪ ያለፉ ኦርጋኒክ የግብርና ምርቶችን ለአለም በመሸጥ፣ ሀብት ማጋበስ የሚያስችል ሀብቷን አልተጠቀመችም፤

ይህንን የውሃ ሀብት ለማጓጓዝ፣ ታላላቅ እርሻዎችን ለማጠጣት፣ የገበሬ መሬቶችን በአመት እስከ ሶስት፣ አራት ግዜ የተለያዩ የግብርና ምርቶች ለማምረት፣ የመጠጥ ውሃ ለማቅረብ፣ እንዲሁም ከግብርናው ቀጣይ የሚሆነውን የኢንዱስትሪዎች መመስረት መጋቢ ሃይል መሆን የሚችል፤ እጅግ ብዙ የኢነርጂ ሀይል ለማምረት የሚያስችል አቅም ያላት፣ በውሃና ኢነርጂ እንዲሁም ተያያዥ በሆነው የእርሻ ዘርፍ ትልቅ እምቅ ሀብት ያላት አገር ብትሆንም ይህን ፀጋ መጠቀም አልቻልንም፡፡

ኢትዮጵያ ታላላቅ ወንዞቿን በመጠቀም የውሃ የኤሌክትሪክ ሀይል ማምረት ፣የትናንሽ እና መካከለኛ ሃይድሮ-ኤሌክትሪክ ሃይል እንዲሁም የመሳሰሉ የኢነርጂ ምንጮችን በመጠቀም ኢነርጂ ማምረት፤ አሁን ካላት የኢነርጂ ማመንጨት ደረጃ ብዙ እጥፍ አይላም፣ የራሷን የዶመስቲክ የሀይል ፍላጎት መሙላትና ለቀጣይ የኢንዱስትሪያል እድገቷም የኢነርጂ-መሰረት መጣል፣ እንዲሁም ለአካባቢው እና ዘልቀው ላሉ የአፍሪካ አገራትም ሃይል በመሸጥ ሃብት መሰብሰብ የሚያስችል እምቅ አቅም ያላት አገር ናት - ኢትዮጵያ ይህን ማድረግ አልቻለችም፡፡

ኢትዮጵያ የዉሃ ሀብቶች ቢኖራትም እንኳን፣ አገሪቱ ይህንን ሀብት የተጠቀሙት ባለመሆኑ፣ ዘዐ ሚሊዮን ህዝቧ በከፋ ድህነት፣ እንዲሁም በዋነኝነት ከዚህ የከፋ ድህነት በሚመነጭ እና ዜጎች፣በተለይም ወጣቶች፣ ከሀገራቸው ምንም አይነት ህይወታቸውን የሚለውጥ አገልግሎት ባለማግኘታቸው በሚነሳ *(የኢትዮጵያ ወጣቶች ከአገራቸው-ለህይወታቸው-መፍትሄ የሚሰጥ አገልግሎት በማጣታቸው የተነሳ፣ ምናልባት ይህንን ኢትዮጵያ ያላቀረበችውን አገልግሎት ከብሄራቸን እናገኘው ይሆን ብለው፣ አገራቸውን ትተው ብሄራቸውን በመጠጋታቸው፣ የመሰሪ ብሄርተኞች የስልጣን-መያዝ ተልእኮ ማሰፈጸሚያዎች ሆነው እንዳሉ ይታወቃል)*፤ የፖለቲካኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ቀውስ ላይ እንገኛለን፡፡

ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፤ በአገራችን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑ በታወቅም፤ መንግሥት መሰረተ ልማቱን ማሳደግና ኤኮኖሚው በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ከማረግ ይልቅ፤ የድምፅ መልዕክት ተደራሽነት በማስፋት ዘረፉን “የሚታለብ ላም” በሚል፤ የጥቂት ግለሰቦች መጠቀሚያ የተደረገ ዘርፍ ነው፡፡ ዘርፉን ከአጠቃላይ ኤኮኖሚ ጋር በማቆራኘት፤ ዓለም የደረሰበትን ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ብቻ ሳይሆን፤ በቴክኖሎጂ ፈጠራ ጭምር ተወዳዳሪ የሚሆንበትን እድል ዘግቶት ይገኛል፡፡ በአገልግሎት ጥራት ይሁን ፍጥነት በዓለም ዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝ ዘርፍ ሲሆን በቀጣይ ያለው እድል መመልከት የሚችልም አደረጃጀት ያልነበረው ተቋም ነው፡፡

የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት በአንድ አቅራቢ እንዲሆን ብቻ በማድረግም፤ ከውድድር የሚገኘውን ጥቅም ዜጎች ያለማግኘታቸው ብቻ ሳይሆን፤ በሌሎች ምርቶችም ላይ ተገቢ ያልሆነ ዋጋ እንዲከፈል ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ የትምህርት እና ከጤና ጋር በሚደረገው ቁርኝት ለትምህርትና ለጤና አገልግሎት ጥራት የሚጠበቅበትን ሚና ሊጫወት አልቻለም፡፡

ፋይናንስ፤ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ እንደ ማዕከላዊ ባንክ ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነፃ ባለመኖኑ የዋጋ ንረት ሊያስከትሉ የሚችል፤ በሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ላይ ጭምር ጫና የሚያሳድር እርምጃ ሲወሰድ መቆየቱ ይታወሳል፡፡ የማዕከላዊ ባንኩ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ያልተላቀቀ እና የባለሞያ እጥረት ያለበት ተቋም ነው፡፡ ያለፉት ዘመናት የመንግስት ገደብ የሌለው ብድርና ብድሩንም በአግባቡ ተጠቅሞ መክፈል አለመቻል ሃገራችንን ከፍተኛ እዳ ከተጫናቸው ሃገራት ውስጥ አንዷ አድርጓታል፡፡ የእዳችን መጠን ከሁለት ትሪሊዮን ብር በላይ ሆኗል፡፡ በዚህ መንገድ ከተጓዝን በአባቶቻችን ደምና አጥንት የወረስነውን ነፃነት በእዳ እንዳናጣው ያሰጋል፡፡

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የባንኮቻችን አሰራር ለሚያበድሩት ብድር ዋስትና ንብረትን በመያዝ ብቻ በመሆኑ፤ የሚያገለግሉት ሃብታምን የበለጠ ሃብታም ለማድረግ የታለመ ነው ማለት ይቻላል፡፡ አዋጭና ስኬታማ ሊያደርግ የሚችል የስራ ሃሳብ ያለው ሰው ለባንክ የሚያሲይዘው ንብረት ከሌለው ሃሳቡን ወደተግባር የሚቀይርበት ብድር የሚያገኝበት አሰራር የለንም፡፡ በሌላው ዓለም አዳዲስ ሃሳቦችና ፈጠራዎች የባንኮች ትኩረት በመሆኑ በርካታ ስራ ፈጠራዎች በየዓመቱ ወደ ገበያ ይገባሉ፡፡ ይህ ሥርዓት እንዲኖር ባለመደረጉ ብዙ የሥራ ፈጠራዎች እንዲመክኑ ሆነዋል፡፡

የሃገራችን ኢኮኖሚ በቂ ቁጠባ እያፈራ አይደለም፡፡ የተገኘውንም ቁጠባ በተገቢው መንገድ እየተጠቀምንበት አይደለም፡፡ ባንኮቻችን የብድር አቅርቦታቸውን ከኢኮኖሚ ፋይዳ አንፃር መዝነው ማቅረብ ካልቻሉ የምናልመውን የኢኮኖሚ እድገት ልናሳካ አንችልም፡፡ የሃገራችን ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆነው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ያገኘውን ከ 5% ያነሰ የብድር አቅርቦት ስንመለከት መንገዳችንንና መድረሻችንን እንድንጠይቅ የሚያደርግ ነው፡፡

የአነስተኛ ብድር ተቋሞቻችን በበርካታ ችግሮች የተተበተቡ በመሆናቸው ለማህበረሰቡ እያቀረቡ ያሉት አገልግሎት ውስን ነው፡፡ ለብድር የሚያቀርቡት ገንዘብ ማነስ፣ የሰለጠነ የሰው ሀይል ማነስ፣ የፋይናንስ መሰረተ ልማት በበቂ አለመኖር፣ ለአብነት የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው፡፡

ከተማ ልማት፤ ከተሞች የአለማችንን 80% ያህሉን ጂ.ዲ.ፒ. እንደማመንጨታቸው፣ የከተማ ልማት በአግባቡ ከተቀረጸ ለዘላቂ እድገት የሚኖረው አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ ነው። በተጨማሪም ከተሞች መሰረተ ልማትን በቁጠባ ለማዳረስ፣

ዜጎች ገቢ የሚፈጥሩባቸውን ዘርፎች ለማብዛት እንዲሁም የሃገሪቱን የወጪ ምርቶች ለመጨመር የከተሞች መስፋፋት አይነተኛ ሚና ይጫወታል።

በሀገራችን እየታየ ያለው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር እድገት፣ በተለይ በየአመቱ በ2.5 ሚለየን የሚጨምረው ስራ ለመስራት የደረሰ ወጣት፣ በገጠር ለመፍታት ያልተቻለውን የመሰረተ ልማት አቅርቦት እና እየጠበበ እየመጣ ባለው የእርሻ መሬት ጥበት ምክንያት እያደገ የመጣውን የአማራጭ የስራ መስክ ፍላጎት ስንመለከት፤ እንዲሁም በነዚህ ምክንያቶች የተነሳ ወደ ከተማ እየፈለሰ ያለውን ህዝብ ማስተናገድ ያቃተውን የከተማ ልማት ተቋማት፣ዜጎች በራሳቸው እየሄዱበት ያለውን ኢመደበኛ የከተሞች መስፋፋት ስናስተውል፣ በአግባቡ የሚመራ እና የታቀደ የከተማ ልማት አንገብጋቢነቱ ፍንትው ብሎይወጣል።

ከተማን አስቦ መገንባትና ከተሜነትን መስበክ በገዢው ፓርቲና መንግስት በኩል የሚታሰቡ ጉዳይ አይደለም። ይልቁንም ዜጎችን በደሳሳ የቀበሌ ቤት ወይም በቁጥጥር ውስጥ በሆነ የኮንዶሚኒየም ቤት ማኖር ለከተሜው የተፈቀደ ሲሆን፤ ማህበራዊ መሰረታችን የሚሉት የገጠር ነዋሪው እዚያው ከመሬቱ ጋር ተቆራኝቶ እንዲኖር፤ ንቅንቅ ቢል መሬቱ የሚወረስበት መሆኑን በመስጋት፤ በእጅ አዙር ባርነት ውስጥ ማኖር፤ በዚሁ መነሻ በሥልጣን መቆያ መሳሪያ ማድረግ ዋንኛ ስትራቴጂያቸው ነው።

ኢንቬስትመንት፤ በአገራችን ያለው የፀጥታ ሁኔታ በቅርብ ጊዜ ኢንቨስትመንት ከዓለም የካፒታል ገበያ ለማግኘት እጅግ አስቸጋሪ አድርጎታል። አገራችን በተፈጥሮ ሀብት ምቹ፤ በቂ ገበያ ያላትና ለአፍሪካ የንግድ ማዕከል የምትሆንበት እድል ያለ ቢሆንም ይህን ማድረግ የሚያስችል ደረጃ ላይ አትገኝም። ሀገራችን በዓለም ለኢንቨስትመንት ምቹ ካልሆኑ አገራት ተርታ መመደቡ አሳዛኝ እውነት ነው። በአገራችን በተዘረጋው የብሔር ፌዴሬሽን መነሻም ባለሀብቶች ወደ ፈለጉት አካባቢ ተጉዘው ሀብታቸውን ለማፍሰስ የሚችሉበት እድል ጠባብ ነው።

2.1.5. ማበራዊ

ትምህርት፤ በትምህርት ሽፋን ደረጃ በአገራችን ከፍተኛ ለውጦች መመዝገባቸው የሚከዳድ ሳይሆን በመስረታዊነት የሚታየው ችግር የጥራት ችግር መሆኑ ሁሉም የሚረዳው ጉዳይ ነው። የትምህርት ዘርፍን አመራርና አደረጃጀት፤ የሃላፊዎች ምደባ፤ የባለሞያዎች እና የወላጆች ተሳትፎ አናሳ እንዲሆን እና ፖለቲካዊ ግብ ብቻ የነበረው ነው። በትምህርት ቤቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ይሰጣል ቢባልም፤ ልጆች በአገራቸው ከሌሎች ጋር በመግባባት ሊያዳብሩት የሚገባውን የተጨማሪ ቋንቋ እውቀት የሚገድብ፤ ሲከፋም በጥላቻ እንዲመለከቱ የሚያደርግ ነው። በዩኒቨርስቲ ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች የውጭ አገር ቋንቋዎች መሰረታዊ እውቀት እንዲኖራቸው ሆነው ባለመማራቸው በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ሳይሆን ለአገር ውስጥ ስራ ለመቀጠር ብቃት እንዳይኖራቸው ተደርገው እንዲያድጉ ሆነዋል። ከሴቶች ተሳትፎ አንፃርም የሚታየው ጭማሪ የትምህርት ደረጃዎች ሲጨምሩ በሚያሳዝን ሁኔታ ተሳትፏቸው የሚቀነስበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን።

በግል ትምህርት ቤቶች እና በመንግሥት ትምህርት ቤቶች መካከል የሚታየው የጥራት ልዩነት አስደንጋጭ ሲሆን፤ የሚወሰድት እርምጃዎችም የመንግሥት ትምህርት ቤቶችን ጥራት ከማሻሻል ይልቅ የግሎቹን ወደ ዝቅተኛ ደረጃ በማውረድ የማመሳሰል አሳዛኝ ድርጊት ነው። አገራችን በአንድ ወቅት አስመዝግባው የነበረውን የተሻለ የጎልማሶች ትምህርት ማስቀጠልና ዘላቂ በማድረግ መሃይምነትን ማጥፋት አልተቻለም። አካል ጉዳተኞች እና ልዩ ፍላጎት ያላቸው ዜጎች በተገቢው መንገድ ትምህርት የሚያገኙበት ሥርዓት ማበጀት አልቻለም።

ጤና፤ በጤና ዘርፍ የሚታየው የሽፋን ሁኔታ መልካም ቢመስልም፤ የጤና ተቋሞች በመድሃኒት አቅርቦት ይሁን በጤና ባለሞያዎች በብቃት የተደራጁ ያለመሆኑ፤ በተለይ ደግሞ ለፈውስ እክምና ተገቢው ትኩረት እንዲያገኝ ባለመደረጉ፤ ዜጎች ጤናቸውን ለመጠበቅ ያላቸው የኤኮኖሚ ደረጃ ወሳኝ እንዲሆን አድርጎታል። የገንዘብ አቅም የሌላቸው ዜጎች ምርጫቻው ሞት ብቻ እንዲሆን ተደርጓል። አሳዛኙ ደግሞ የመንግሥት ሹማምንት ለቀላል ህክምና ሁሉ በውጭ አገር፤ በውጭ ምንዛሪ የሚታከሙበት እድል ተፈጥሮላቸው፤ በውጭ ምንዛሪ እጥረት የመንግሥት ተቋማት ከመሰረታዊ የህክምና ቁሳቁስና መድሃኒት እጥረት ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት ያለመቻላቸው ነው።

ሰደት፤ ወጣቱ ትውልድ በአገር ስርዶ መኖርን አማራጭ አድርጎ እንዳይመለከት፤ ከሥራ አጥነት በተጨማሪ በየመኖሪያው አካባቢው የሚደርስበት ፖለቲካዊ ግፊትና ጫና፤ ሥራ አጥነት፤ የምግብ ዋስትና ያለመረጋገጥና ረሃብ አገሩን ጥሎ በማንኛውም መንገድ እንዲሰደድ ምክንያት እየሆነው ይገኛል። ይህም ዜጎች በሚሰደዱበት የዓለም ክፍል ክብራቸውን በሚያዋርድ ሁኔታ ኑሮ እንዲገፉ የሚያደርግ ሲሆን፤ ወደ ስደት የሚያደርጉትም እንቅስቃሴ የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር የሚያስፈከፍል እንደሆን የእለት ከእለት ዜና መሆኑ ይታወቃል። ዜጎች በመላው ዓለም ተንቀሳቅሰው መስራት መብታቸው ሲሆን፤ ይህን ማድረግ የማይችሉበት የዕውቀትና ክዕሎት ጉድለት ምንጩ ግን የትምህርት ፖሊሲው ነው። በቋንቋ እና መሰረታዊ ክዕሎት ለማዳበር የማይረዳ የትምህርት ዝግጅት ዜጎችን በሚሄዱበት አገር ከባርነት ባልተናነሰ ሁኔታ ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋቸዋል።

በአሁኑ ወቅት በአደገኛ ሁኔታ ወደ ምዕራቡ ዓለም የሚደረገው ስድት በተቀባይ አገሮች ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ ቁጥጥር የሚደረግበት ቢሆንም ለተማሩና በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ለሚያገኙ ተማሪዎችና ባለሞያዎች ምቹ ሁኔታ እየተፈጠረ ስደት መቀጠሉን መዘንጋት የለብንም። ዲቪን ጨምሮ በዚህ ሁኔታ የሚደረጉ ሰደቶች አገራቸንን ለሰው ሀይል ልማት የሚወጣውን ኢንቨስትምን በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ መሆኑ ይታወቃል። ይህን ጉዳት ሊቀንስ፤ ብሎም ትርፋማ በሆነ ሁኔታ ለአገር እንዲጠቅም ማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ማበጀት ካለመቻሉም በላይ ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ኢትዮጵያዊያን በፖለቲካ ምልከታቸው ብቻ የሚገፉበት አስራር መኖሩ ግልፅ ነው።

ባህል፤

ሥርዓተ ጾታ፤በገራችን የሥርዓት ፆታ ግንዛቤ ብዙ የሚቀረው ሲሆን፤ አሁን ባለው ደረጃ በፖለቲካው መስክ በመቶ ሳላሳ እጅ ለማሳተፍ ከማይቻልበት ደረጃ ላይ እንገኛለን። የልጃገረዶች የትምህርት ተሳትፎ በመጀመሪያ ደረጃ አበረታች ምልክቶች ያሉት ሲሆን፤ በተለያዩ ማህበራዊ ምክንያቶች ወደ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና ኮሌጂ ማሳደግ አልተቻለም። ይህም ሴቶችን ወደ ከፍተኛ የሃላፊነት ደረጃ ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት ሰንካላ እያደረገው ይገኛል። ወንዶችን ያሳተፈ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ያለመስፋፋት፤ ሴቶችን የሚያበረታታ የተለየ የትምህርት እድሎች አለመኖራቸው፤ በተለያየ ጊዜ የሚታዩት ፆታ መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች መበራከት፤ ወዘተ.. በሥርዓተ ፆታ ዙሪያ ገዢው መንግሥትና ፓርቲ ተገቢውን ትኩረት እንዳልሰጡት ማሳያ ነው።

ወጣቶች፤የነገው ትውል ተራካቢ እየተባለ ከአሁናዊ ሁኔታው እንዲርቅ የሚደረገው ወጣት በቁጥርም ሆነ ለአገር ልማት ማበርከት ካለበት ድርሻ አንፃር ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል። ወጣቱን በተለያየ መንገድ ለፖለቲካ ግብ ማሳኪያ በመጠቀም ውድ የሆነ ሕይወቱን እንዲከፍል የተደረገ ቢሆንም፤ በማንኛውም ሚዛን ቢለካ የእኩል ተጠቃሚነት እድል ማግኘት አልቻለም። ይልቁንም አፍላ እድሜውን በሥራ አጥነት ከማሳለፍ በተጨማሪ ለአጉል ሱሶች ተገዢ በመሆን ተገቢ ባልሆኑ ሥፍራዎች የሚገኝ የሕብረተሰብ ክፍል ነው። ወጣቱ በተሳሳተ የትምህርት ሥርዓት መንሥዔ በቴክኖሎጂ ተደግፉ፤ በሥራው ዓለም ተፈላጊ በሆኑ ክዕሎቶች እራሱን አዳብሮ እንዲገኝ አልተደረገም። የአገር ፍቅሩን በሚሸረሽሩ፤ ግቡን ሰደትና የውጭ አገራት እንዲሆን ተደርጎ በተሳሳተ መንገድ እየተቀረፀ ነው። ወጣቱ ብሔረተኞች በሚረጩት ፕሮፓጋንዳ ዋንኛ ተጠቂ እየሆነ፤ የማህበራዊ ሚዲያ ለልማትና ጥቅሙን ለማስጠበቅ ሳይሆን ለመለያየት እና ለግጭት እንዲውል ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮለታል። በገጠር የሚገኘውም ወጣት በተሳሳተ የመሬት ፖሊሰ አና የመሬት ባለቤትነት መንሥዔ በገጠር ውሰጥ ያለ ሥራ የቤተሰቦቹን መሬት ተሰፋ አድርጎ መጠበቅ ብቸኛ አማራጩ ተደርጎበታል። ባለፉት 30 ዓመታት

የተወለዱ ወጣቶች መሬት የሚያገኙበት እድል እጅግ ጠባብ ከመሆኑ የተነሳ ከፍተኛ ማህበራዊ ቀውስ በቤተሰብ ውስጥ እየፈጠረ የሚገኝ እውነት ነው፡፡

አካል ጉዳተኞች፤ በአገራችን በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች የተነሳ በሰዎች ላይ የደረሱ የአካል ጉዳቶች መኖራቸው አሌ የማይባል ጉዳይ ነው። በዚህም ሳቢያ አካል ጉዳተኞች ለተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ተጋልጠው ይገኛሉ። ይህም መንግስታት የተከተሉት ፖሊሲና ማህበረሰቡ ስለአካል ጉዳተኞች የነበረው የተዛባ አመለካከት እንደፈጠረው ሊታወቅ ይገባል። የአካል ጉዳት አይነቶች በዋነኝነት በሰባት ተከፍለው የሚታዩ ናቸው፡፡ እነኝህም የወገብ ችግር ፣ ዓይነስውርነት፣ የተሽከርካሪ ወንበር ተጠቃሚዎች እና የመራመጃ እግር ተጠቃሚዎች፣ መናገር የተሳናቸው፣ መስማት የተሳናቸው፣ የአእምሮ ውስንነት ያለባቸው እና ጥምር ጉዳት ያለባቸው ናቸው፡፡ ከእነዚህ የአካል ጉዳቶች ጋር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ከ17 ሚሊየን የሚልቅ እንደሚሆን የሚገመት ነው፤ እነዚህ የአካል ጉዳተኞች ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸው በአገር ልማት ላይ እንዲሳተፉ እየተደረጋ ካለመሆኑ በተጨማሪ በተለያዩ ሁኔታ መገለልና መድልዎ ይደርስባቸዋል፡፡ የሚገኙትንም ማንኛውም ዓይነት ድጋፍ በምፅዋት መልክ እስኪመስል ድረስ የግንዛቤ ችግር ያለ ሲሆን፤ አገራዊ ጠቀሚታቸውን የተረዳ የፖለቲካ አመራርም ሆነ ማህበረሰብ መፍጠር አልተቻለም፡፡

ማህበራዊ ከለላ፤ማኅበራዊ ከለላ ስንል የፖሊሲዎች እና የመርህግብሮች ጥቅል የሆነ በቁጥር ላቅ ያለውን ማህበረሰብ ከድህነት እና ከተጋላጭነት የማውጣት ውጥን ነው፤ ይህንንም ለማድረግ በፖሊሲዎች እና መርህግብሮች ጥምረት ህዝብን ከአደጋ ተጋላጭነት መቀነስ፣ እራሳቸውን የሚከላከሉበትን የስራ ገበያ በማመቻቸት አቅማቸውን ማሳደግ እና በቂ ገቢ እንዲያገኙ ማስቻል እና መሰረታዊ የማህበራዊ አገልግሎትን ማድረስ ነው፡፡ ገዢው ፓርቲና መንግሥት የማህበራዊ ከለላን ፅንሰ ሃሣብ በቅጡ ካለመረዳታቸው በተጨማሪ ለዚሁ አገልግሎት መዋል የሚገባውን ሀብት በብዙ ዕጥፍ በተለያዩ ምክንያቶች ሲያባክኑት ይስተዋላል፡፡

ክፍል ሦስት

ኢዜማ የአገራችን ሰላምና ደህንነት በዋነኝነት ስጋት ላይ የሚወድቀው በአገር ውስጥ ባሉ ችግሮች ነው ብሎ ያምናል!

ችግሮቻችን በውይይትና በሕዝብ ይሁንታ ብቻ እንዲፈታ ያደርጋል!

ለማንኛውም የሀይል ትንኩሣ ዝግጁነቱን ያረጋገጠ ሀይል ይኖረዋል!

የመከላከያ፤ ፖሊስና ደህንነት ሀይሎች ሥራቸውን ሲከውኑ፤ የፖለቲካ ወገንተኝነት ሊይዙ አይችሉም!

3.1. የብሔራዊ ደህንነት መሰረታዊ ችግሮች መፍቻ መንገዶች ለቀጣይ አምስት ዓመት

ኢዜማ መሰረታዊ የደህንነት ችግሮች ሊወገዱ የሚችሉት፤ የመንግሥት አደረጃጀትን ገለልተኛ እና ተልዕኮዎን ለመፈፀም በሚያስችለው ሁኔታ ሲደራጅ መሆኑን ያምናል፡፡ በዚህ መሰረት ፍርድ ቤቶች፤ ዓቃቢ ሕግ፣ ፖሊስ ደህንነትና መከላከያ ከፖለቲካ ገለልተኛ ሆነው እንዲደራጁ የሚያደርግ ሲሆን፡፡ የመንግሥት ተቋማት ተገቢውን አገልግሎት በመስጠቅ የመልካም አስተዳደር እንዲያስፍኑ ከፖለቲካ ገለልተኛ እንዲሆኑ በማድረግ መሆኑን በማመን የሚከተሉትን የማሻሻያ እርምጃዎች በዋና ዋና ተቋማት ላይ ይወሰዳል፡፡

ኢዜማ በቀጣይ 5 አመታት ስልጣን የሚይዝ ከሆነ ከላይ የተዘረዘሩት የብሄራዊ ደህንነት ስጋቶችን በመቅረፍና የደህንነት ስጋት ደረጃዎችን እንዲቀንሱ የሚያደርግባቸውን የመፍትሄ ሃሳቦች እንደሚከተለው በዝርዝር ይቀርባሉ፡-

- ህገ መንግስቱን በማሻሻል መንግስታዊ የፖለቲካ ስርአቱን ዘግነትን መስረት ወደ አደረገ የፖለቲካ ስርአት እንዲቀየር ያደርጋል። በአጭሩ የሀገርና የሕዝብን ደህንነት ያረጋገጠ፤ አሁን ላሉት በሀገርና በሕዝብ ላይ ላንጣበበው የደህንነት አደጋ ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች ከግምት የወሰደ፤ መንግስታዊ የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ ያደርጋል።

- በዘውግ ማንነት ላይ ብቻ ተመስርቶ የተዋቀረውን ያልተማከለ የፌደራል ስርአት ከሕዝብ ጋር በሚደረግ ምክክር ሌሎች መመዘኛዎችን በመጨመር ያልተማከለ የአስተዳደር አይነቱ በዘውግ ብቻ እንዳይሆን አድርጎና ሁሉንም ዜጎች በእኩልነት ሊያስተናግድ በሚችልበት አኳሃን ከእንደገና እንዲዋቀር ያደርጋል።
- የደህንነት ተቋማት የዘውግ እና የሃይማኖት ጸንፈኝነትን ለማጥፋትና ለመቆጣጠር በሚያስችል የጸር ጽንፈኝነት ስታራቴጂዎችን አውጥተው በተግባር ሊፈጽሙና አደጋውን ሊያስቀሩ በሚችሉ ሁኔታ ይደራጃሉ። ጽንፈኝነትን ከመከላከል አንጻር የጽንፈኝነትን አይነት እና ባህሪያት ግምት ውስጥ የከተተ የተለየ የመከላከል ስትራቴጂና ስልቶችን ይቀየሳሉ።
- በክልሎች ውስጥ የተደራጁ ልዩ ሃይሎች በሙሉ ፈርሰው በክልሎች ውስጥ ባሉ የክልል ፖሊስ አካላት ሥር እንዲጠቃለሉና ፖሊስ በሚመራበት መመሪያ አማካኝነት እንዲተዳደሩ ይደረጋል።
- ድህነትን አስቀርቶ የማህበራዊ ፍትህ ከማስፈን አንጻር የሚወሰዱ የኢኮኖሚ ማነቃቂያ እና የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች ይተገበራሉ። በተለይ አላግባብ የሚባክኑ ገንዘቦች ከፍተኛ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል። በሙስና፣ ህገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር እና በመልካም አስተዳደር እጦት የሚባክነውን በቢሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ በማስቀረት ከዚህ በሚገኘው ገንዘብ ለድህነት ቅነሳ ስራዎች እና ለወጣት የስራ እድል ፈጠራ እንቅስቃሴዎች እንዲውል ይደረጋል። እንዲሁም መጠነ ሰፊ የኑሮ ውድነትን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ተግባራት ይፈጸማሉ።
- የኢኮኖሚ አሻጥሮችን እና ህገ ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመቆጠጠር የሚያስችል ጠንካራ፣ በሙያተኞች የተገነባ የኢኮኖሚ እና የፋይናንስ መረጃ ኤጀንሲ በማቋቋም ጥብቅ ቁጥጥር ያደርጋል።
- የሳይበር ወንጀሎችን ሙያዊ በሆነ መንገድ በሚገባ ለመቆጣጠር በሚያስችል ሁኔታ የሳይበር ደህንነት ተቋምን ዘመኑን በሚመጥን መልኩ እንዲ ደራጅ ይደረጋል።
- አማራጭ የወደብ አገልግሎትን ማግኘት በሚያስችል ሁኔታ እና የሃገሪቷን ብሄራዊ ደህንነት እና ጥቅም በሚያስጠብቅ ሁኔታ ከጎረቤት ሃገራት ጋር ግንኙነት ይመሰረታል። ከኤርትራ ጋር በሚኖረን ግንኙነት የኢትዮጵያን ብሄራዊ ደህንነት እና ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ ግንኙነቱ እንዲሆን ይደረጋል። ለቀጠናው ሰላም እና የጋራ ደህንነትን ማስጠበቅ በሚያስችል ሁኔታ ላይ ከቀጠናው ሃገሮች ጋር በትብብር ይሰራል።
- ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብቶቿን ካለ ማንም ጠልቃ ገብነት የመጠቀም ሙሉ መብቷን ባረጋገጠ መንገድ የልማት እንቅስቃሴዎቿን እንድታከናውን ይደረጋል።

ከብሄራዊ የደህንነት አስፈጻሚ አካላት ጋር ተያይዞ ያሉ ተግባራት እንደሚከተለው ነው፦

3.1.1. የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት (ፓርላማ) የሰላምና ደህንነት ቋሚ ኮሚቴ

ፓርላማው ህግ የማውጣት ስልጣን ያለው አካል ነው። የሰላምና ደህንነት ቋሚ ኮሚቴ በፓርላማው ውስጥ ከብሄራዊ ደህንነት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የብሄራዊ ደህንነት አስፈጻሚ አካላት በአላቸው ሀላፊነት ልክ ስራዎችን እየሰሩ እንደሆነ እንዲከታተል ይደረጋል። ፓርላማውን ከብሄራዊ ደህንነት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ያማክራል። ከብሄራዊ ደህንነት ጋር የተያያዙ የተለያዩ አማራጭ ሐሳቦችን በጥልቅ ጥናትና ትንታኔ በመደገፍ የውሳኔ ሐሳቦችን ለፓርላማው ያቀርባል። ውሳኔ ከተሰጠበት በኋላም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ሂደቱንና ውጤቱ አስፈጻሚዎች ስራን በአግባቡ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል። የብሄራዊ ደህንነት አስፈጻሚ አካላት የተለዩ (special) በጀት ምደባ ላይ ቋሚ ኮሜቴው የእራሱ ሚና እንዲኖረው ይደረጋል።

3.1.2. የብሄራዊ ደህንነት ካውንስል

የብሄራዊ ደህንነት ፖሊሲ አተገባበር በርካታ የመንግሥት ተቋማት ቅንጅታዊ ስራ የሚጠይቅ ነው። የብሄራዊ ደህንነት ካውንስል በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ ሲሆን የመንግስት ሥራ አስፈጻሚና የሚመለከታቸው አካላት አሉበት። ይህ ካውንስል ስትራቴጂያዊ የሆኑ የብሄራዊ ደህንነት ጉዳዮችን የሚከታተል ነው። የብሄራዊ ደህንነት ካውንስል ከብሄራዊ ደህንነት ፖሊሲ አተገባበር ጋር ተያይዞ የሚከናወኑ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች እና ስትራቴጂያዊ ኦፐሬሽኖችን እየተከታተለ የአፈጻጸም ውሳኔዎችን ይወስናል። ፖሊሲውን ከመተግበር አንጻር ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል። የስራ ድርሻቸውን ለሚመለከታቸው አካላትን በመስጠት ቅንጅታዊ አሰራራቸውን በተሳለጠ መንገድ እንዲያከናውኑ አቅጣጫዎችን አስቀምጣል። ካውንስሉ ከተለያዩ አካላት የሚያገኘውን የመረጃና ትንተና ውጤቶች እንዲሁም የሥራ ሪፖርት መነሻ በማድረግ ከብሄራዊ ደህንነት አንፃር ጥልቅ ስትራቴጃዊ ጥናትና ትንተና በማድረግ የተለያዩ አማራጭ የውሳኔ

ሐሳቦችን እንዲያቀርብ ይደረጋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከካውንስሉ አባላት ጋር በተለያዩ የውሳኔ ሃሳቦች ይመክራሉ፤ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣሉ።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሄራዊ ደህንነት ጉዳዮች አማካሪ በዚህ ካውንስ ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ሚና እንዲወጣ ይደረጋል። ይህ ካውንስል በባለሙያዎች የተዋቀረ የራሱ ጽ/ቤት ኖሮት እንደ ተቋም እንዲደራጅ ይደረጋል። የብሄራዊ ደህንነት ካውንስል ዋነኛ ስራው የብሄራዊ ደህንነት ቅደም ተከተሎችን መለየትና መወሰን ይሆናል።

3.1.3. የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሄራዊ ደህንነት አማካሪ ፅ/ቤት

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሄራዊ ደህንነት ፖሊሲ አተገባበር ጋር ተያይዞ ከፍተኛ የመወሰን ስልጣን በህግ ተሰጥቷቸዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚወስኑት ውሳኔ የአገሪቷን ደህንነት እና ብሄራዊ ጥቅም ከማስጠበቅ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ከብሄራዊ ደህንነት ጋር የተያያዙ ውሳኔዎች በትልቅ ጥናትና ትንተና ላይ ተመርኩዘው በሚቀርቡ ምክረ ሃሳቦች ሆናል። በዚህ ረገድ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የደህንነት አማካሪ ጽ/ቤት በጥናት እና ትንተና ላይ ተመርኩዘው የሚቀርቡ የመረጃ ትንተና ውጤቶችን እውነተኛ፣ ጠቃሚ፣ ወቅታዊ እና ታእማኒነት ያላቸው መሆናቸውን ከብሄራዊ ደህንነት አስፈጻሚ አካላት ጋር ተቀናጅተው በመስራት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሚወስናቸው የተለያዩ የውሳኔ ሃሳቦች ግብአት እንዲሆኑ ይደረጋል። በዚህ የስራ ሂደት የጠቅላይ ሚኒስተር የደህንነት አማካሪ ወሳኝ ሚና አለው። በአጠቃላይ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሄራዊ ደህንነት አማካሪ ጽ/ቤት በብቁ ባለሙያዎች የተዋቀረና አትኩሮት ያለው ሆኖ ይደራጃል፤ የሚጠበቅበትን የስራ ድርሻም በከፍተኛ የብቃት ደረጃ እንዲወጣ ይደረጋል።

3.1.4. የደህንነት ማህበረሰብ

በኢትዮጵያ ውስጥ የደህንነት ማህበረሰብ እሳቤ (concept) ተግባራዊ ይደረጋል። የሃገር ውስጥ ደህንነት፣ የውጪ መረጃ፣ የፌደራል ፖሊስ፣ የመከላከያ መረጃ ተቋም፣ የሳይበር ደህንነት ተቋም እና ሌሎች የመረጃ እና የደህንነት ተቋማት የደህንነት ማህበረሰቡ አባል ይሆናሉ። የደህንነት ማህበረሰቡ ስትራቴጂያዊ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራርን እንዲተገብሩ ይደረጋል። ይህንንም ስትራቴጂያዊ የመረጃ እና ደህንነት አቅጣጫ የመስጠት ሃላፊነት እና የመረጃና ደህንነት ማእከላዊነት ሚናን እንዲወጣ አሁን ያለው የሰላም ሚኒስተር፤ የሰላም እና ደህንነት ሚኒስተር መስሪያ ቤት ሆኖ እንደገና እንዲደራጅ ይደረጋል። የሰላምና ደህንነት ሚኒስተር የደህንነት ማህበረሰብ ማእከላዊነት እና ያለመማከልን (centralization and compartmentation) የመረጃ እና ደህንነት ባህሪያትን ግምት በወሰደ መንገድ ስትራቴጂያዊ የመረጃ እና ደህንነት አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል። እንዲሁም ስትራቴጂያዊ በሆኑ የመረጃ እና ደህንነት ጉዳዮች ላይ የደህንነት ማህበረሰቡን እንዲያስተባብር ይደረጋል።

አሁን ያለው የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት መስሪያ ቤት እራሳቸውን ችለው እንደ ተቋም በተቋቋሙና የደህንነት ማህበረሰቡ አባል በሆኑ ሁለት ተቋማት እንዲከፈሉ ይደረጋል። የሃገር ውስጥ ደህንነት ኤጀንሲ እና የውጪ መረጃ ኤጀንሲ ተብለው እንዲቋቋሙ ይደረጋል።

የእነዚህ ተቋማት ስትራቴጂያዊ እይታ፣ ርዕይ፣ ተልዕኮ እና ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎቹ ሙያዊነትን ሊያሰፍን በሚችል፤ የሃገርን ደህንነት እና ጥቅም በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲቃኝ ይደረጋል። እነዚህ ተቋማት የሃገሪቷ ብቁ ዜጎች ሙያዊነትን ባሰፈነ መንገድ ስራዎቻቸውን እንዲያከናውኑ የሚያደርጉ ተቋማት ይሆናሉ። በምልመላ ሂደትም በእውቀታቸው እንቱታን ያተረፉ እና በእምቅ እውቀታቸው የልህቀት ጫፍ መድረስ የሚችሉ ተማሪዎችን ማእከል አድርጎ ነው የምልመላ እንቅስቃሴዎችን የሚያደርጉት።

እነዚህ ተቋማት የተጨባጭና ምናልባታዊ የስትራቴጂዊ እና ስልታዊ የስጋት ትንተናዎች የማድረግ አቅም ያዳበሩ ተቋማት እንዲሆኑ ተደርገው ነው የሚዋቀሩት። በአጠቃላይ ጠንካራ የሃገር ውስጥ ደህንነት የሚያስከብር እና ታላቅ ሃገር ለመሆን ያለንን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ ጠንካራ የውጪ መረጃ ተቋማት ይሆናሉ። በተለይ ስውር ጥቃቶች ወይም ኦፕሬሽኖችን (covert actions or operations) የመፈጸም አቅምን (capabilities) በማያወላዳ መንገድ መፈጸም የሚችሉ ተቋማት ሆነው ይደራጃሉ።

3.1.5. ፍ/ቤቶች

ፍ/ቤቶች ጥራት ያለው የፍትህ አገልግሎት የመስጠት ችግር ያለባቸው ፣ የተደራሽነት ችግር ያለባቸው ፣ ከፖለቲካ ተጽእኖ ያልተላቀቁ ፣ የዜጎችን መብቶች ለማስከበር ያላቸው አቅም ውስን የሆነና ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ያላቸው አስተዋጽአ በጣም አነስተኛ የሆኑ ተቋማት ናቸው ፣ ስለሆነም ኢዜማ

- ፍ/ቤቶች ተቋማዊ ነጻነታቸው የተጠበቀና ከማንኛውም ተጽእኖ ነጻ የሆነ የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል
- የዳኝነት ሹመት በከፍተኛ የሙያ ብቃትንና የስነምግባር ምስጉንነት ላይ የተመሰረት እንዲሆን ያደርጋል
- ዳኞች በከፍተኛ የሙያ እውቀት የተካኑ እንዲሆኑ በየጊዜው ደረጃውን የጠበቀና በጥናት ላይ የተመሰረት ተከታታይ ስልጠና እንዲወስዱ ይደረጋል
- የፍ/ቤቶች አሰራር ቀልጠፋና ወጪ ቆጣቢ ለማድረግ በቴክኖሎጂ የታገዘና በአዳዲስ የአሰራር ስርአቶች የታገዘ በየጊዜው እየዘመነ የሚሄድ አሰራርን የተከተለ እንዲሆን ያደርጋል
- ፍ/ቤቶች የፍትህ አገልግሎትን በጥራትና በፍጥነት መስጠት የሚችሉበትን አስፈላጊ ቁሳዊና የሰው ሀብት አቅርቦት ያሟላል
- ፍ/ቤቶች የሚያጋጥማቸውን ችግር ከስር ከስር ለመፍታት በቋሚነት ክትትልና የሚደርግበትንና ችግሮች ስር ሳይሰዱ የሚፈቱበት ስርአት እዲዘረጋ ያደርጋል
- ከፍተኛ ልምድና በተወሰነ የሕግ መስክ ከፍተኛ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው የሕግ ባለሙዎች በከፊል ጊዜ አገልግሎት የዳኝነት ስራ መስራት የሚችሉበትን ስርአት ይዘረጋል
- ከዩኒቨርስዎችና ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ለዳኝነት ጥራት ማደግ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማሰራት ተግባራዊ ያደርጋል
- ዜጎች የሚተማመኑበት ፣ የሰብአዊና ህገመንግስታዊ መብቶችን በአግባቡ ማስከበር የሚችልና ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ጽኑ መሰረት የሚሆን የዳኝነት ስርአት ይገነባል

3.1.6. ዓቃቢ ሕግ

የሕግ የበላይነት የመከበር ጉዳይ ያለ ጠንካራ ፣ ገለልተኛና ብቃታ ባለው ባለሙያ ያልተደራጀ ዐ/ሕግ መ/ቤት የማይታሰብ ቢሆንም ዐ/ሕግ መ/ቤት በተለያየ ተቋማዊ የአደረጃጀትና የስልጣንና ሀላፊነት ለውጥ የተነሳ ጠንካራ መሰረት የሌለው ተቋም ሆኖ ቆይቷል ። በተጨማሪም በፖለቲካ ተጽእኖ ምክንት ብዙ ተጎድቶና ጠንካራ ከሆነ ሙያዊ አስተዳደር ርቆ ስለቆየ የሚጠበቅበትን አገልግሎት ሳያበረክት ቆይቷል ፤ ስለሆነም ኢዜማ

- የዐ/ቤ ሕግ መ/ቤት ገለልተኛ እና ነጻ የሆነ ተቋም ሆኖ እንዲደራጅ ያደርጋል
- የሕግ የበላይነት በጠነከረና ስር በሰደደ ሁኔታ እንዲከበር ተገቢውን ጥረት ሁሉ የሚያደርግ ተቋም እንዲሆን ያደርጋል
- የሚመደቡ ዐቃቤ ሕጎች ከፍተኛ የሙያ ብቃትና የስነምግባር ደረጃ ያላቸው እንዲሆኑ ያደርጋል ፣ ይህንኑ የሚያረጋግጥበት ስርአትንም ይዘረጋል
- ጥራት ያለውና ከማንኛውም ፖለቲካዊ ተጽእኖ ነጻ የሆነ የወንጀል መዝገብ ምርመራ ፣ የወንጀል ክስ ምስረታና የክርክር ስራዎች እንዲከናወኑ ያደርጋል
- በየጊዜው የሚወጡ የወንጀል ሕጎች አላማና ግብን በሚገባ የተረዱ እንዲሆኑ ለዐ/ሕጎች በቂና ደረጃውን የጠበቀ ተከታታይ ስልጠና እንዲወስዱ ያደርጋል
- ዜጎች ያለአግባብ እንዳይከሰሱና ሊከሰሱ የሚገባቸውም ያለአግባብ ሳይከሰሱ እንዳይቀሩ ጥብቅ ፣ ግልጽና ቀልጣፋ የአሰራር ስርአት ፣ የአቤቱታ አቀራረብና አወሳሰን ስርአት እንዲዘረጋ ደርጋል
- በተለያዩ ምክንያቶች የወንጀል ተጎጂ የሆኑ ዜጎችን በፍትህብሄር ክስ ወክሎ በመከራከር ተገቢውን ፍትህ እንዲያገኙ ያደርጋል
- በዜጎች ሰብአዊና ሕገመንግስታዊ መብቶች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያላቸውን ሕጎች ፣ አሰራሮችና ልማዶች በቅርበት በመከታተል በተገቢ ጥናት ላይ የተመሰረት እርምት እንዲወሰድባቸው ያደርጋል
- የፖሊስና የማረሚያ ቤቶች ተቋማት ተግባራቸውን በአግባቡ እያከናወኑ ስለመሆኑ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል
- የታራሚዎች አያያዝ ሰብአዊ መብታቸውን ያከበረና ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ ያረጋግጣል ።

- ታራሚዎች የማረሚያ ቤት ቆይታቸውን ጨርሰው ወደህብረተሰቡ ሲቀላቀሉ በስነምግባር ተለውጠው ፤ የወንጀልን አስከፊነት ተረድተውና የተለያዩ ክህሎቶችና ስልጠናዎች አግኝተው ለራሳቸው ፣ ለቤተሰባቸውና ለማህበረሰቡ ሰላምና ደህንነት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ እንዲሆኑ ያደርጋል
- ብቃት ያለው የመንግስት የሕግ አማካሪ ተቋም እንዲሆን አድርጎ ያደራጃል
- በጥናት ላይ በመመስረት የተወሰኑ የፀ/ሕግ መ/ቤት አገልግሎቶች በፍትህ ሚኒስቴር የሚሰጡ እንዲሆኑ የፍትህ ሚኒስቴር መ/ቤትን ሊያደራጅ ይችላል

3.1.7. የፖሊስ ተቋማት

ከህግ ማስከበር ጋር ተያይዞ ፌዴራል ፖሊስ ወንጀል የማስቀረት ወይም የመከላከል ተጋባራት በሚገባ ለመፈጸም በሚያስች መልኩ መዋቅራዊ ማሻሻያ ያደርጋል። የፌዴራል ፖሊስ ሙያዊ ብቃቱን በሚያረጋግጥ መልኩ በስልጠናዎች፤ በፖሊስ ትምህርቶች እና በተሞክሮዎች ውስጥ አባላቱ እንዲያልፉ በማድረግ ሙያዊነትን ማእከል ያደረግ የፖሊስ የስራ ሂደት እንዲፈጠር ይደረጋል። የፖሊስ ሃይልን ለማዘመን በቅርቡ ባወጣው የፖሊስ ዶክትሪን በርካታ አዎንታዊ የሆኑ ጉዳዮችን በዶክትሪኑ እንዲሰፍር ተደርጓል። የፖሊስ ዶክትሪኑ ሙያዊ የሆነ የፖሊስ ኃይል ለማፍራት ከፍተኛ አጋዥነት አለው። ይህ እውነታ እንዳለ ሆኖ የፖሊስ ዶክትሪኑ የፌዴራል ፖሊስን የህግ ማስከበር አካል ብቻ አድርጎ ለማየት መሞከሩ አንዱ ችግር ነው። የፌዴራል ፖሊስ ህግ የማስከበር ሀላፊነቱን የሚወጣው ከብሄራዊ ደህንነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችንም ጭምር ያካተተ በመሆኑ ፌዴራል ፖሊስ የደህንነቱ ማህበረሰብ አባል ይሆናል። ስለዚህ የፌዴራል ፖሊስን ከደህንነት ማህበረሰብ ስራዎች አንጻር ያሉበትንም ሀላፊነት በሚገባ ባገናዘበ መልኩ እንዲዋቀር ይደረጋል። የፌዴራል ፖሊስ የደህንነት ማህበረሰብ አባል ሆኖ ከብሄራዊ ደህንነት ጋር በተያያዘ ያለበትን ሀላፊነት በሚገባ ሊወጣ በሚችል መልኩ መዋቅራዊ ማሻሻያ ያደርጋል።

የፖሊስ ተቋማት ብቃት ያለው የወንጀል መከላከል ስራ ለመስራት የሚያስችል ከፍተኛ የቁሳዊ አቅርቦትና የሰለጠነ የሰው ሀይል ችግር አለባቸው ። እንደፎረንሲክ አገልግሎት የመሳሰሉ በዘመናዊ የፖሊስ ሳይንስ እና ቁሶች የታገዙ የወንጀል ምርመራ ለማድረግና ብቃት ያለው የወንጀል ምርመራ ለማድረግ ፣ ደረጃውን የጠበቀ የተጠርጣሪዎች አያያዝ ለማድረግ ከፍተኛ ችግሮች ይታያሉ ፣ ስለሆነም ኢዜማ

- በዘመናዊ ቁሳዊ አቅርቦትና በሚገባ በሰለጠነ የሰው ሀይል በሚገባ የተደራጀና ብቃት ያለው የፖሊስ ተቋም ይገነባል
- ዘመናዊ የፖሊስ ሳይንስን የተካነ የወንጀል መከላከል ላይ ትኩረት ያደረገ ተቋም ይገነባል
- የወንጀል ምርመራ ስራዎች ዘመኑ ባፈራቸው ሳይንሳዊ የምርመራ ዘዴዎች ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ያደርጋል
- የወንጀል መከላከልና ምርመራ ስራዎች የዜጎችንና የወንጀል ተጠርጣሪዎችን ሰብአዊና ሕገመንግስታዊ መብቶች ባከበረ ሁኔታ እንዲከናወኑ ያደርጋል
- ህዝባዊ አመኔታ ያለው የፖሊስ ተቋም በመገንባት ዜጎች ያለፍርሀትና መሸማቀቅ ሰላማዊ ኖሮአቸውን የሚመሩባት አገር እንድትሆን ያደርጋል

ጥራት ያላቸው የፖሊስ የስልጠና ተቋሞችን ያደራጃል ፣ ያሉትንም ብቃታቸውን ያሳድጋል

3.1.8. መከላከያ

የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል በአዋጅ ዝ00/2019 አማካኝነት የምድር ኃይል፤ የአየር ኃይል እና የባህር ኃይል እንደሚኖረው ይደነግጋል። እንዲሁም የሳይበር ኮማንድ ሊያቋቁም እንደሚችል ይገልጻል። ይህን አዋጅ መሰረት አድርጎ በወጣው የመከላከያ ስትራቴጂ የምድር ኃይል፤ የአየር ኃይል፤ የባህር ኃይል፤ የሳይበር ኮማንድ እና የተጠባባቂ ጦር መከላከያ እንደሚኖረው ያስቀምጣል።

የመከላከያ ሚኒስተር የመከላከያ ኃይልን (defense force) በበላይነት የመቆጣጠር (oversee power) እና በህግ አግባብ ስራውን እያከናውነ እንደሆነ የመከታተል ሀላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ ይደረጋል። መከላከያ ሚኒስተር የመከላከያ ኃይል የሚተገብራቸውን የመከላከያ ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችን በተግባር ላይ እየዋሉ እንደሆነ ይከታተላል። የመከላከያ ሚኒስተር እና የመከላከያ ኃይል በህግ በተሰጣቸው ስልጣን ልክ ስራዎቻቸውን እንዲያከናውኑ ይደረጋል። የመከላከያ

ሚኒስተር የመከላከያ ኃይልን የመቆጣጠር (inspection) ሀላፊነቱን በሚገባ ይወጣል። በመከላከያ ሚኒስተር ስር የቁጥጥር (inspection) ዳይሮክቶሬት ያለ ሲሆን ይህ ዳይሮክቶሬት ስራውን በሚገባው ደረጃ እንዲያከናውን ይደረጋል።

በመከላከያ ሚኒስተር ስር ያለው የሕዝብ ግንኙነት ዳይሮክቶሬት የሚጠበቅበትን ሀላፊነት በሚገባ እንዲወጣ ይደረጋል። ይህ አካል መከላከያን አዎንታዊ ምስል (image) በማህበረሰቡ ዘንድ እንዲኖረው ከማድረግ ባሻገር ማንኛውም የተረጋገጠ እና ምናልባታዊ ጠላት በሃገር ላይ ጥቃት እንዳያደርስ በሕዝብ ግንኙነት በኩል የሚሰሩ የማስቀረት (deter) ስራዎችንም ያከናውናል። ይህን ሀላፊነቱን በተጠና እና ሙያዊ በሆነ መንገድ ይፈጽማል። በመሆኑም የህዝብ ዳይሮክቶሬቱ የመከላከያ ተለዕኮን ባገናዘበና ሙያዊነትን ባሰፈነ መልኩ በተለይ ከእራስን ማተለል (self-deception) ነጻ በሆነ መልኩ ይዋቀራል፤ በተጠና መንገድ ከጸረ መረጃ (counter Intelligence) ተቋማት ጋር በመናበብ ስራዎችን ያከናውናል።

ባጠቃላይ መከላከያ ሙያዊነትን ማእከል አድርጎ እንዲገነባ ይደረጋል። በመሆኑም የመከላከያ ኃይል ሙያዊነትን በሁሉም የመከላከያ መስኮች ላይ ተግባራዊ የሚደረግበትን መንገድ ቀይሶ የሃገር አሌንታ መሆኑን ያረጋግጣል። ዋና ዋና የሚባሉ ከመከላከያ ጋር በተያያዘ የሚተገበሩ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡- ከመከላከያ እሳቤዎች ጋር በተያያዘ የሚያስተምር የካዴት ትምርህር ቤት እንዲኖር ይደረጋል። በዚህ የካዴት ትምህርት ቤት ውስጥ በትምህርታቸው የላቁ ተማሪዎችን በመመልመል እንዲቀላቀሉ ይደረጋል።

ከብሄራዊ ደህንነት ካውንስል የሚመነጩ እና የመከላከያ ሃይል ካውንስል የሚያጸድቀው፤ ከብሄራዊ ደህንነት እና የስትራቴጂያዊ መረጃ ቅደም ተከተሎች አንጻር የመከላከያ ስትራቴጂያዊ የመረጃ ቅደም ተከተሎችን ማእከል አድርጎ የመከላከያ ኃይል እንዲንቀሳቀስና ግዳጁን በብቃት እንዲወጣ ይደረጋል።

በጠቅላይ መምሪያ ስራ ካሉ በርካታ ዋና መምሪያዎች ውስጥ የመከላከያ መረጃ ዋና መምሪያ አንዱ ነው። ይህ ተቋም የተጨባጭ እና ምናልባታዊ ስትራቴጂያዊ ስጋቶችን በመተንተን ሃገርን እና የወገን ኃይልን ከማንኛውን አይነት አደጋ የማስቀረትና የመከላከል ሀላፊነት ያለበት በመሆኑ ስራውን በአግባቡ መወጣት በሚችልበት ደረጃ እንዲዋቀር እና እንዲደራጅ ይደረጋል። ከስትራቴጂያዊ መረጃ ማሰባሰብ ጀምሮ እስከ የትንተና ውጤት አቅርቦቱ ድረስ በእውቀት ላይ የተመሰረተና ሙያዊነትን ባከበረ መልኩ እንዲንቀሳቀስ ይደረጋል። በመሆኑ የመከላከያ መረጃ ዋና መምሪያ መዋቅራዊ ማሻሻያ ያደርጋል።

የመከላከያ መረጃ ዋና መምሪያ እራሱን በተለያዩ የመከላከያ ሃይላት ስር የሚገኙ የመረጃ ተቋማትን ማዕከላዊነትን በጠበቀ መልኩ አስተባብሮ መምራት በሚችልበት ሁኔታ ይደራጃል። በተለይ ተጨባጭ እና ምናልባታዊ የስትራቴጂያዊ ስጋቶችን በመተንተን ለአዛዦች የስትራቴጂያዊ እና ስልታዊ (tactical) አፕሬሽኖችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፈጸም የሚያስችል የተነተነ የድርጊት (Actionable) መረጃዎችን ማቅረብ በሚችሉበት ሁኔታ ይደራጃሉ።

የመከላከያ ኃይል የተለያዩ ሃይሎቹን የሚያሰፍርበት (deployment)፣ መዋቅሩን ማዕከል የሚያደርግባቸውን ቦታዎች እና የኃይል ስምሪት አካባቢዎች በተጨባጭ እና ምናልባታዊ የስትራቴጂያዊ አደጋ እና ስጋት ትንተና ላይ ተመስርቶ የሚፈጸም ይሆናል። ይህ ስትራቴጂያዊ የመረጃ ትንታኔ ተጨባጭ እና የወደፊቱ የሃገሪቷን ብሄራዊ ጥቅም እና የህዝቡን ደህንነት ማዕከል አድርጎ የሚከናወን ነው። በዚህ ደረጃ በሚፈጸም የትንተና ውጤት ላይ ተመርኩዞ ነው የሰራዊቱ ስትራቴጂያዊ እንቅስቃሴዎች የሚተለሙት።

ከነፍስ ወከፍ እስከ ቀላል ተተኳሽ መሳሪያዎች ድረስ በሃገራቸን ሊመረት ሚችልበትን እና እራሳችንን ከመቻል አልፈን ለአካባቢ ሃገራት መሳሪያዎችን መሸጥ የሚያስችል አቅም ይገነባል። ለዘለቄታው እራሳችንን በመሳሪያ አቅርቦት እንድንችል የመሳሪያ ቴክኖሎጂ (weapon technology) ምርምር የሚደረግበትን የመሳሪያ የምርምር ማዕከለ መገንባት ዋነኛ የመከላከያ አትኩሮታችን ነው። በአጠቃላይ ብሩህ አእምሮ ያላቸውን ተማሪዎች እንደዚህ አይነት እውቀቶችን የሚያዳብሩባቸውን የመሳሪያ የምርመር ተቋም በመክፈት ከነፍስ ወከፍ እስከ ውስብስብ የሆኑ የመሳሪያ ቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለመስራት የሚያስችል ዝግጁነት ይፈጠራል።

3.2. ሲቪልሰርቪስ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ መሳተፍ ከፍተኛ ክብር የሚያስጥ የነበረ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት የሲቪል ሰርቪሱ ተመጣጣኝ ክፍያ ተከፍሎት ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ሳይሆን፤ ዜጎች ተገቢውን አገልግሎት ለማገኘት ሄደው ተማረው የሚመለሱበት፤ ሲቪል ሰርቫንቱም በቂ ክፍያ ስለማያገኝ የምልጃ ክፍያዎችን መጠየቅ ነውር መሆኑ የቀረበት ይልቁንም የስራው ባሕሪ ተደርጎ የሚሰድበት አስነዋሪ ደረጃ ላይ መድረሳችን በግልፅ የምንመለከተው የዕለት ከዕለት ገጠመኛችን ነው፡፡

የሲቪል ሰርቪሱ በሌሎች አገራት እንደሚደረገው፤ በችሎታቸው የላቁ ለሕዝብ ጥቅም የሚቆሙና የደረጃ ማስጠበቅና የመንግሥትን የቁጥጥርና ክትትል ሥራን የሚያሳልጡ መሆናቸው ቀርቶ፤ ለካድሬዎቸ እና ለፖለቲካ ታማኝነት ትኩረት የሚስጥ በመሆኑ ዜጎች አገልግሎት ሲሹም ይህን አድሎዋዊ አስራር እመነው እንዲቀበሉ ሲያደርግ የነበረ ነው፡፡

በሌሎች ሀገራት ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኛው መካከለኛ ገቢ ያለው ቢያንስ መኪና መንዳትና የመኖሪያ ቤት ብርቁ ያልሆነ ልጆቹን ያለምንም መሳቀቅ የሚያስተምር እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህም የሆነው የሲቨል ሰርቪስ ሰራተኞች በብቃት ብቻ የሚመደቡና፤ በብቃታቸው ልክ ስለሚከፈላቸው ነው፡፡ የሀገራችን የሲቪል ሰርቪስ በአብዛኛው ቁጥሩን የሚይበዙት በየገጠሩ የተሰማሩ ለገበሬው ድጋፍ እንዲሰጡ በሚል የተመደቡ የፖለቲካ አስፈፃሚዎች ናቸው፡፡ በወረዳ የሚመደቡ የግብርና ልማት ሰራተኛ በአብዛኛው ጊዜያቸውን በፖለቲካ የሚያጠፉ በመሆናቸው የተሻለ የግብርና ቴክኖሎጂ ይዘው ቢቀርቡም በሕብረተሰቡ ዘንድ ተዓማኒነታቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ በተመሳሳይ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች መከላከል መሰረት በማድረግ ለተቀረፀ ፖሊሲ ወሳኝ ግብዓት ተደርገው ቢታሰቡም የፖለቲካ ተስታፎዋቸው ዋናውን ተግባራቸውን በታማኝነት እንዳይሰሩ ደንቃራ እንደሆነባቸው ይታመናል፡፡

ለሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች በተለያየ ወቅት የደሞዝ ጭማሪ ተደረገ ቢባልም በማነኛውም መመዘኛ ሰራተኛው ኑሮውን ሊያሻሽል ቀርቶ በዚሁ መንስዔ የተከሰተውን የዋጋ ንረት ሊካክስ የሚችል አልነበረም፡፡ አሁንም በጥናት ላይ የተመሰረተ ተመጣጣኝ ክፍያ ለሰራተኛው መክፈል የመልካም አስተዳደርን ለመሻሻል አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው፡፡

ዘላቂው መፍትሔ አቅምና አቋም ያለው ሲቪል ሰርቪስ ሥርዓት ሲሆን ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችለው ከፖለቲካ ገለልተኛ የሆነ የሲቪል ሰርቪስ መገንባት ሲቻል ነው፡፡ ኢዜማ የሲቪል ሰርቢስን በወሳኝ መልኩ የሚለውጥ ሲሆን የማንኛውም ፓርቲ አባላት ቢሆኑም በስራቸው ብቃት እስካሳዩ ድረስ ምንም ጫና የማይኖርባቸው ሲሆን፤ የሚታይባቸውን የብቃት ችግር ለማሻሻል ተገቢውን ትኩረት ስጥቶ ይስራል፡፡ ኢዜማ ሙስናን እና ዜጎችን ማጉላላት በምንም ዓይነት ሰበብ ተቀባይነት የማይኖረው ሲሆን፤ለሕዝብ አስተማሪ በመሆኑ መልኩ እርምጃ ይወስዳል፡፡

ክፍል አራት

4.1. የፖለቲካ መሰረታዊ ችግሮች መፍቻ መንገዶች ለቀጣይ አምስት ዓመት

4.1.1. ሕገ መንግስታዊ ስርዓትን ማክበርና ማስከበር

ኢዜማ በሕዝበ ውሳኔ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ የሚያደርግ መሆኑን ያሳውቃል!

ኢዜማ ኢትዮጵያ ውስጥ መሰረታዊ የሆነ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ለውጥ ለማምጣት የህገ መንግስት መሻሻል አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል። የኢትዮጵያን ህገ መንግስት ህገ መንግስቱ ዉስጥ የተቀመጠውን አንቀጽ ተከትሎ ማሻሻል እንደማይቻል ለሁላችንም ግልፅ እየሆነ የመጣ ይመስላል፡፡ ሰለሆነም፤ ኢዜማ በ2013 ምርጫ አሸናፊ ከሆነ ቅድሚያ ሰጥቶ ከሚሰራቸው ስራዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው አሁን በሥራ ላይ ያለው ሕገ መንግሥት “መሻሻል አለበት? ወይስ የለበትም?” የሚል ሕዝበ ውሳኔ እንዲካሄድ ማድረግ ነው፡፡ የሕዝብ ውሣኔው ውጤት “መሻሻል አለበት” የሚል ከሆነ፤ ነፃና ገለልተኛ የሆነ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ኮሚሽን በማቋቋም፤ ሕገ መንግሥቱ ውስጥ ያሉትን መልካም ጅማሮች ላይ መሰረት በማድግ፤ ሕገ መንግሥቱ መሻሻል አለበት ከሚሉ ሀይሎች ጋር በጋር በሕጋዊ ሥርዓት ለሕዝብ ጥቅም ብቻ ሲባል እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡ ይህ ሕገ መንግሥት በሕዝብ ውሳኔ እስኪሻሻል ድረስ ግን በህገ መንግስት የተቀመጡት ድንጋጌዎች በስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

4.1.2. የሕዝብ የስልጣን ባለቤትነት ጥያቄ

ዛሬ በሁሉም መልኩ ሉዓላዊነታቸውን አስከብረው ከፍተኛ የሥልጣኔ ማማ ላይ የደረሱ ዘመናዊ አገሮች ለዚህ የበቁት የዜጎቻቸውን ሰብዓዊና ሌሎችም መብቶች ያከበረና የህዝብን የሥልጣን ባለቤትነት ያረጋገጠ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ማህበረሰብ መፍጠር መቻላቸው ነው። አገራችን ኢትዮጵያም አሁን ከምትገኝበት ድህነት፣ኋላቀርነት እና የፖለቲካ ምስቅልቅ ውስጥ ወጥታ የተረጋጋችና ሉአላዊነቷ የተከበረ ዘመናዊ ሀገር እንድትሆን፣ የሕዝብ የስልጣን ባለቤትነት የሚያረጋግጥ የፖለቲካ ሥርዓት ያስፈልጋታል። የኢዜማ እንዲህ አይነት የፖለቲካ ሥርዓት መፍጠር ቀላል እንዳልሆነና ብዙ ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል ይገነዘባል። ሆኖም በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጥረታችን ውስጥ በእያንዳንዱ ምዕራፍ የምንሰራቸው የፖለቲካ ሥራዎች በሂደት ወደዚህ ወዳሰብነው ሥርዓት የሚወስዱን መሆን አለባቸው ብሎ ያምናል። ዲሞክራሲ ህዝባዊ ተሳትፎን የሚፈልግ ሥርዓት ነውና፣በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደታችን ውስጥ ከምንሰራቸው ትልልቅ ስራዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ማህበረሰባችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ፋይዳን በደንብ ተረድቶ ለዚያ ሥርዓት መፈጠርም ሆነ ከተፈጠረም በኋላ ተጠናክሮ እንዲቀጥ መጫወት ያለበትን ሚና ያለማሰለስ ማስተማር ነው።

ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በአንድ በኩል ጠንካራና የተረጋጋ በህዝብ የተመረጠ መንግስት ይፈልጋል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በኩል ዲሞክራሲን ተሸክመውት መጓዝ የሚችሉ መንግስታዊ ተቋሞችና መንግስት የሥልጣን ገደቡን እንዳይለቀ መቆጣጠር የሚችሉ ጠንካራ የሜዲያና ህዝባዊ ተቋሞች ያስፈልጋሉ። ይህንን በተመለከተ ኢዜማ ስራቸውን በገለልተኝነት የሚሰሩ ምርጫ ቦርድን፣ ደህንነትን፣ መከላከያን፣ፍትህን እና ኡዲትና ቁጥጥርን የመሳሰሉ ተቋሞች እንዲኖሩ አጥብቆ ይታገላል። በዲሞክራሲ ውስጥ መንግስት ተጠያቂ ከሚሆንበት መንገድ አንዱ ምርጫ ነው፣ነገር ግን ዲሞክራሲ ከምርጫ በተጨማሪ መንግስትን ተጠያቂ ማድረግ የሚችሉ የሰራተኛ ማህበራት፣ የሙያ ማህበራት፤የሴቶች ማህበራትን የመሳለሉ ህዝባዊ ተቋሞችና ገለልተኛ ነጻ የሆኑ የሜዲያ ተቋሞች ያስፈልጋሉ።

4.1.3. የመድበለ ፓርቲ ስርዓት ግንባታ

ኢዜማ የአንድ ፓርቲ ሥርዓት አይቀበልም፤ ለመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ግንባታ ሁሉን ኣቀፍ ድጋፍ ያደርጋል!

የሐሣብ አማራጭ ማቅረብ መብት ቢሆንም ማንኛውም ሃሳብ በሀይል በህዝብ ላይ መጫን አይፈቀድም!

ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ከተቋም ግንባታ ጋር በቅርብ የተቆራኘና አብሮ የሚሄድ ስራ ነው፣ ጠንካራና ጤነኛ ዲሞክራሲ ጠንካራና ጤነኛ የሆኑ ተቋሞች ያስፈልጉታል። ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ከሚያስፈልጉት ተቋሞች ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች ግንባር ቀደሙን ቦታ ይይዛሉ። የኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ጅምር መሬት አልለቅ ብሎ ብልጭ ድርግም እያለ ከግማሽ ምዕተ አመት በላይ ከፍተኛ ዋጋ ያስከፈለን ዲሞክራሲን መሸከም የሚችሉ ጠንካራና ጤነኛ ፓርቲዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ባለመኖራቸው ነው። ይህ ችግር ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ችግር ነው። ዲሞክራሲ ያለ ፓለቲካ

ፓርቲዎችና ያለ ተቃውሞ ፖለቲካ ሊኖር የማይችል ሥርዓት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የተቃውሞ ፖለቲካ እንዲያብብ ጠንካራና ጤነኛ ፓለቲካ ፓርቲዎች ያስፈልጉናል፣ ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እንዲኖሩን ደግሞ፣ የተቃውሞ ፖለቲካን ማስተናገድ የሚችል መድበለ ፓርቲ ሥርዓት መኖር አለበት። እነዚህ ተደጋጋፊ ተቋሞች እንዲኖሩን ኢዜማ የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል።

ኢዜማ፣ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባትም ሆነ ባጠቃላይ በኤኮኖሚ የበለጸገች አገር እንድትሆን በሃሳብ በልጦ ለመገኘትና በምርጫ አሸናፊ ሆኖ አገር ለመምራት የተለያዩ ፓርቲዎች ከፍተኛ ውድድር የሚያደርጉበት የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ያስፈልጋታል የሚል ፅኑ እምነት አለው። በየርዕዮተ አለም፣ በፖለቲካና በኤኮኖሚ ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎች የሚለያዩ ፓርቲዎች እኔ እሻል እኔ እያሉ የሚያደርጉት ውድድር ለዕድገት ወሳኝ እንደሆነ በብዙ አገሮች ውስጥ ታይቷል።

ልዩነት የኦ እንደ ፓርቲ ኢትዮጵያዊያን ወደተሻለ የኤኮኖሚ የማህበራዊ እድገት ደረጃ ለማደግ የሚችሉት አማራጭ ማቅረብ የሚቻልበት የመድበለ ፓርቲ ስርዓት ሲኖር ብቻ እንደሆነ በፅኑ ያምናል። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የተለያዩ ብሔረሰቦች ሀይማኖቶች ባሉበት ሀገር ብቻ ሳይሆን ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ዝርያና ሃይማኖት ላላቸው ህዝቦችም ቢሆን፤ አማራጭ ሊያቀርብ የሚችል የመድበለ ፓርቲ ስርዓት ግንባታ የግድ በሆነበት ዓለም ውስጥ እንደምንገኝ እየታወቀ፤ ገዢው ፓርቲም ለስልጣን ካለው ከፍተኛ ግምት ብቻ በመነሳት በአንድ አውራ ፓርቲ መመራት አለባት የሚለውን እንዲሁም **“ብቸኛውም አማራጭ”** የሚል ፍልስፍና ኢዜማ በፅኑ ይቃወማል። የኢትዮጵያ ህዘብም ለመድበለ ፓርቲ ስርዓት የሚመጥን የእድገት ደረጃ ላይ ይገኛል ብሎ ኢዜማ ያምናል።

የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት መኖር የሃሳብ መንሸራሸርን ያበረታታል፣ድምፅ ሰጪው ማህበረሰብ የተሻሉ አማራጮችን አይቶ ይሻላል የሚለውን ሃሳብ እንዲመርጥ ያስችለዋል፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች በነጻነት ሃሳባቸውን መሸጥ መቻላቸው የፖላቲካ አላማን በኃይል ማስፈጸም አዝማሚያን ይከላከላል። ኢዜማ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓትና ነፃ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ የሚያመጣውን ማንኛውም ውጤት በፀጋ ለመቀበል ዝግጁ የሆነ ሲሆን፤ በዚህ ሥርዓት የሚፈጠር ስህተት ቢኖር እንኳን ስህተቱ መታረም ያለበት በዲሞክራሲያዊ ሂደቱ ዉስጥ ብቻ መሆን አለበት የሚል ፅኑ እምነት አለው። ከዲሞክራሲያዊ ሂደቱ ዉጭ ለሕዝብ ሲባል የፖለቲካ ኃይሎች የሚወስዱት ምንም አይነት እርምጃ አፍራሽ ነውና መኖር የለበትም። ኢዜማ ለሕዝብ ሃሳቡን አቅርቦ በምርጫ ለሚያሸንፍ ኃይል እውቅና ከመስጠት ጀምሮ አብሮ እስከመስረት የሚደርስ ሰምምነት ሊደርስ ይችላል። ይህ የሚወሰነው ፓርቲዎቹ ከኢዜማ ፕሮግራምና ፖሊሲዎች ያላቸውን ቅርበት መሰረት በማድረግ እንጂ በፍጹም ለሥልጣን መጋራት ሲባል የሚደረግ አይሆንም።

4.1.4. ፌዴራሊዝም

የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም አብሮነትን የማፅናት፤ አስተዳደርን ወደ ሕዝቡ የማውረድ ሥርዓት እንጂ በምንም መልኩ ጠንካራ የፈዴራል ሥርዓት እንዳይኖር የሚያደርግ መሆን የለበትም!

ኢዜማ እንደ ፓርቲ የመንግስት አደረጃጀት ፌዴራላዊ መሆኑን በግልፅ ያስቀመጠ ሲሆን ይህም አደረጃጀት የፌዴራል መንግስትና የአካባቢ አስተዳደሮች ይኖሩታል። ኢዜማ አብላጫ ድምፅ አግኝቶ ስልጣን ሲይዝ የህዝብን ፍላጎት መሰረት ባደረገ ሁኔታ የክልላዊ መንግስት አወቃቀር በሚከተሉት መርሆዎች እንዲሆን ለህዝብ ውይይትና ለህገ መንግስት ማሻሻያነት ያቀርባል፤በሕዝብ ይሁንታ ሲያገኝ፤

- መልከአ ምድራዊ አቀማመጥን፣ የሕዝብ አሰፋፈር ለአጠቃላይ አስተዳደራዊና ለልማት ሥራዎች አመቺነትን፤
- ቋንቃ፤ ባህልና ታሪክን፤
- የሃብት ስብጥርና ፍትሃዊነት
- ለብሔራዊ መግባባት አመቺ ሁኔታ መፍጠርን፤ መሠረት ባአደረገ ሁኔታ ይሆናል።

ኢዜማ ፌዴራላዊ አወቃቀሩ አንዴ ተሰርቶ የሚያበቃለት ሳይሆን የተቀመጡትን መርሆዎችን ጠብቆ ከኢኮኖምያዊ እና ፖለቲካዊ እድገታችን ጋራ በመግባባት መንፈስ እየዳበረ የሚሄድ እንደሚሆን እምነት አለው። በዚሁ መሰረት፤

- የፌዴራል መንግሥቱና እና የአካባቢ መስተዳድሮች ባለሥልጣናት በሕግ የተወሰነ የየራሳቸው የሥልጣን ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡ አንዱ በሌላው የውስጥ ጉዳይ እንዳይገባ ይደረጋል፡፡ የየራሳቸው ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈፃሚ እና ሕግ ተርጓሚ ይኖራቸዋል፡፡
- አማርኛ የፌዴራል መንግስቱ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ያገለግላል፡፡ አሮምኛና ሌሎች ተጨማሪ ቋንቋዎች በመላው ሀገሪቱ ቋንቋውን ለመማር ፈቃደኛ ለሆኑ ዜጎች እንዲሰጥ ከአካባቢ መስተዳድሮች ጋር በመመካከር ድጋፍ ያድርጋል፡፡ እንዲሁም በሕዝብ ውሳኔ ሲፀድቅ ከአማርኛ ሌላ በተጨማሪ ቋንቋ የፌደራሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ እንዲሆን ያደረጋል፡፡
- የክልል መንግስታት የሥራ ቋንቋ የክልሉ ሕዝብ በሚያደርገው ሕዝበ ውሳኔ መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

4.1.5. የመሬትባለቤትነት

መሬት በግል፤ በማህበረሰብ እና በመንግሥት ይዞታ የሚሆንበት ሥርዓት ይዘረጋል!

አርሶ አደሩና የከተማ ነዋሪ የመሬቱ ሙሉ ባለመብት ይሆናል!

በኢትዮጵያ የግዛት ክልል የሚገኝ ማንኛውም የተፈጥሮ ሀብት መሬትን ጨምሮ የሁሉም ዜጎች የጋራ ሀብት ነው ብሎ ኢዜማ ያምናል፡፡ አሁን ያለው የመሬት ፖሊሲ ለኢኮኖሚ እድገት ያለውን እንቅፋት በመረዳት የተለያዩ ዓይነት የመሬት አጠቃቀም እና ይዞታ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ የመሬት ይዞታም በመንግሰት፣ በማሕበረሰብ ወይም በግል ሊሆን ይችላል፡፡

- በኢትዮጵያ ግዛት ክልል ዜጎች ያልሰፈሩበትን ቦታ ጨምሮ ሌሎች ፓርኮችና ለመንግሥት አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ ቦታዎች በፌዴራሉ መንግሥት ይዞታነት ሊያዙ ይችላሉ፤ በመንግሥት ይዞታነት ያሉ ቦታዎች ግልፅ በሆነ መሰፈርት እና የገበያ ዋጋ ወደ ግል ሊዛወሩ ይችላሉ፤
- በአርብቶ አደር አካባቢ ለግጦሽ፣ በሌሎች አካባቢም ለልዩ ልዩ ማህበራዊ አገልግሎት የሚውሉ በማሕበረሰቡ የሚተዳደሩ የወል የመሬት ይዞታዎች ሊኖሩ ይችላሉ፤
- ዜጎች መሬትን በግል ይዞታነት በባለቤትነት መያዝ፣ ማከራየት፣ መግዛት መሸጥና መለወጥ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡
- ኢዜማ የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት ግልፅ የሆነ የአረንጓዴ ልማት ፖሊሲ ቀርፆ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

4.1.6. የሊዝ ፖሊሲ

የሊዝ ትግበራ የዜጎችን ንብረት የማፍራት መብት በማይሻማ መልኩ ይደረጋል!

በድንበር አካባቢ ያሉ ኩታገጠም ሰፋፊ ቦታዎች ለረጅም ጊዜ በሊዝ ለውጭ አገር ዜጎች መስጠት አይቻልም!

ኢዜማ ኢትዮጵያዊያን በይዞታነት ሊይዙት የሚችሉትን መሬት መግዛትና መለወጥ የሚችሉበት ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በመንግሥት ይዞታ የሚገኙ መሬቶች እንደ አስፈላጊነቱ በሊዝ ለአገር ውስጥና ለውጭ ኢንቨስተርስ ሊተላለፉ የሚችሉበት ሥርዓትም በተጓዳኝ የሚኖር ይሆናል፡፡ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በሊዝ የሚሰጡ ቦታዎችን ስፋትና አካባቢያዊ ሁኔታ መንግስት በጥናት የሚወስነው እና የአገር ሉዓላዊነትን በማይነካ መልኩ መሆኑን ማረጋገጥ ዋንኛ ሃላፊነቱ ይሆናል፡፡

ለምሳሌ በድንበር አካባቢ ያሉ ኩታገጠም ሰፋፊ ቦታዎች ለረጅም ጊዜ በሊዝ ለውጭ አገር ዜጎች መስጠት አይቻልም፡፡ በድንበር አካባቢ በግለሰብ ይሁን በመንግሥት እጅ የሚገኙ ቦታዎች በሊዝ ለውጭ አገር ዜጎች በሚተላለፍበት ወቅት መከተል የሚገባንን ዝርዝር ደንብ ከአገር ሉዓላዊነት አንፃር ታይቶ የሚወጣ ይሆናል፡፡

4.1.7. ባንዲራ

የኢትዮጵያ ባንዲራ አረንጓዴ፤ ቢጫ እና ቀይ ነው!

ዓርማው በሕዝብ የሚወሰን ይሆናል!

ክልሎች የራሳቸው አርማ ሊኖራቸው ይችላል!

ኢዜማ በህገ መንግስት በተደነገገው መሰረት የኢትዮጵያ ባንዲራ አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ መሆኑን ይቀበላል፡፡ አሁን ያለው አርማ በዘላቂነት የኢትዮጵያ መንግስት አርማ ሆኖ መቀጠል አለመቀጠሉን በህዝበ ውሳኔ በማስጠት እንዲወሰን መደረግ ያለበት ሲሆን፤ ይህ ተቀባይነት ካላገኘ ሌላ አማራጭ አርማ በጥናት ቀርቦ በሕዝብ ይሁንታ እንዲያገኝ የሚደረግ ይሆናል፡፡ በሕዝብ ውሳኔ ተቀባይነት ያገኘ አርማ በማዕከላዊውና በክልል መንግስት ተቋማትና በድርጅቶች፤ በትምህርት ቤቶች፤ በውጭ አገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላዎች ፅ/ቤቶች እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎችን በሚያደርጉት ሕዝባዊ ስብስባን ጨምሮ በፅ/ቤታቸው የማድረግ ግዴታ የሚኖርባቸው ሲሆን ዜጎች በእለት ከእለት እንቅስቃሴዎቻቸው አርማ ያለበት ሰንደቅ እንዲይዙ የሚገደዱበት ሆኔታ ይቀራል፡፡ በፈቃዱ ዓርማው ያለበትን የሚይዝ ዜጋም መብቱ የተከበረ ነው፡፡

በተጨማሪ ክልሎች/የአስተዳደር አካባቢዎች የራሳቸው ባንዲራ የመወሰን ስልጣን የሚኖራቸው ሲሆን በምንም ዓይነት በስልጣን ላይ ካለው ፓርቲ ዓርማና ሰንደቅ ጋር ግንኙነት እንዳይኖረው ይደረጋል፡፡ ሁሉም ክልሎ/የአስተዳደር አካባቢዎች የፌዴራሉን እና የክልሉን ባንዲራ ጎን ለጎን የማውለብለብ ግዴታ አለባቸው፡፡

4.1.8. የግልና የቡድን መብቶች

ኢዜማ ለቡድን መብቶች እውቅና ይሰጣል! ባህል እንዲዳብር የመንግሥት ድጋፍ ያደርጋል!

የግለሰብ መብቶች መከበር የሰብዓዊ መብት መከበር ምሶሶ ነው!

የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ሲሻሻል ከፍተኛ ትኩረት ከሚፈልጉ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የግለሰብ መብትና የቡድን መብትን የሚለው ሃሳብ ነው። የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ግልጽ በሆነ መንገድ ለቡድን መብት ቅድሚያ ይሰጣል፣ ይህ በመሆኑ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የብሔር “ማንነት” የብዙ ነገሮች መለኪያ ነው። የግለሰብና የቡድን መብት ጉዳይ ብዙ የፍልስፍና እና የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራንን ለረጂም ግዜ ያከራከረ ጉዳይ ነው። የፍልስፍናው ክርክር እንዳለ ሆኖ ወደ አገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመጣ፣ የግለሰብ መብት እስከተጠበቀ ድረስ የቡድን መብት ይጠበቃል፣ ወይም ቡድኖች በጋራ አለን የሚሉትን መብት ከግለሰብ መብት ውስጥ ፈልጉት በሚል ጥቅል መልስ ማለፍ የማንችለበት ግዜ ላይ ነን። የግለሰብ መብት የመብቶች ሁሉ መሰረት ቢሆንም አንዳንድ ሲጠየቁም በተግባር ሲሰጡም በቡድን ደረጃ ብቻ የሚሰጡ መብቶች እንዳሉ መገንዘቡ የአገራችንን ችግር ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት ያፋጥነዋል።

አገራችን ኢትዮጵያ አሁን ባለው ፖለቲካ ሁኔታ ወደድንም ጠላንም የቡድን መብት የሚባሉት በተለይ ደግሞ የብሔር ብሔረሰቦች መብት የሀገራችን ፖለቲካ መሰረት ሆኖ ላለፉት ሰላሳ አመታት ቆይቷል። ይህንን የፖለቲካ መሰረትነት ኢህአዴግ ለስልጣኑ ማስጠበቂያ ዋልታና ማገር አድርጎታል፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ባለው ተጨማጭ ሁኔታ የቡድን መብት ብሎ ነገር የለም የሚል አስተሳሰብ ማራመድ ከእውነት መራቅ ይሆናል፣ ነገር ግን የቡድን መብት የመብቶች ሁሉ መሰረት እንደሆነ አድርጎ ማቅረብና የአገርን ፖለቲካ በዚህ መሰረት ላይ ማቆም የማያዋጣ መሆኑን ማሳየት ብቻ ሳይሆን አማራጭ ሃሳብ ይዞ መቅረብ አስፈላጊ ነው ብሎ ኢዜማ ያምናል። የብሔር ፖለቲካ አራማጆች በብዛት የሚጠይቁት ጥያቄ ኢትዮጵያዊ ማን ነው? የሚል ሲሆን እኛ ደግሞ መጠየቅ ያለበት ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ማን ነው? ተብሎ መሆን አለበት ነው፡፡

ኢዜማ ቋንቋ፣ባህል፣ሃይማኖት፣ ታሪክ ወዘተ የመሳሰሉ ለቡድን መብት ጥያቄ መነሳት መሰረት የሆኑ ጉዳዮች “እራስን በራስ ማስተዳደር” የሚለው ዋናውና ትልቁ የቡድን መብት ጥያቄ መልስ ሲያገኝ አብረው መልስ ያገኛሉ የሚል ከፍተኛ እምነት አለው። አንድ ህዝብ እራሱን በራሱ ሲያስተዳድር ባህሉንና ቅርሱን ከመንከባከብ ባለፈ የራሱን የትምህርት ፖሊሲና የልማት ቅደም ተከተል የማውጣትም መብት ይኖረዋል። ስለዚህ ኢዜማ የመብቶች ሁሉ መሰረት የግለሰብ መብት መሆኑን እና የግለሰብ መብት ሳይከበር የቡድን መብት ሊከበር እንደማይችል በጽኑ የሚረዳ ቢሆንም፣ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለቱም መብቶች መከበር አለባቸው የሚል እምነት አለው።

4.1.9. ሰብዓዊና ዲሞክራሲ መብቶች

ኢዜማ የዜጎች ሰብዓዊ መብት በማይከበርበት አገር ውስጥ ቁሣዊ እድገት በራሱ ትርጉም አለው ብሎ አያምንም!

ለማንኛውም ዓይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተገቢው እርምጃ ይወሰዳል! በጊዜው ማስተካከያ ያደረጋል!

ኢዜማ በሕገ-መንግሥቱ እውቅና የተሰጣቸውን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ አገራችን የፈረመቻቸውን የሰው ልጆችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚደነግጉ ስምምነቶችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ የአገራችንን ልዩ ሁኔታ ባገናዘበ የቡድን (የብሔረሰብ፣ የሀይማኖት፣ ወዘተ) መብቶች ከግለሰብ መብቶች ጋር ግጭት በማይፈጥረበት መልኩ ጥበቃ የሚደረግለት ሲሆን፤ በጥናት ላይ የተመሰረተ የቡድን ፍላጎታቸውን ለማዳበር እንዲችሉ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ የሚዲያ ተቋማት እንዲሁም ሲቪል ማህበራት የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ለማዳበር በነፃነት እንዲደራጁ አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያደረግ ይሆናል፡፡

4.1.10. የሠራተኛና የሙያ ማኅበራት

ሠራተኞች እና የሙያ ማህበራት በነፃነት እንዲደራጁ ምቹ ሁኔታ መፍጠር!

የሙያ ማህበራት ተደራጅተው የአባላቶቻቸውን መብት ማስከበር እንዲችሉና በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂት ውስጥ የራሳቸውን አሻራ እንዲያሳርፉ ማስቻል!

ኢዜማ በነፃነት የመደራጀት መብትን የሚያከብር ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን፤ ሠራተኞች እና የሙያ ማህበራት ያለምንም ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት እንዲደራጁ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በሠራተኛና ሙያ ማኅበራት ፖሊሲው የሚከተሉትን ወሣኝ የዘርፉ ጉዳዮችን ተግባራዊ እንዲሆኑ የድርሻውን ይወጣል፡፡

- ሠራተኛው ለመሠረታዊ ፍጆታው የሚበቃ ክፍያ የሚያገኝበት የሥራ ዋስትናው የሚጠበቅበት በእውቀትና ክህሎት የዳበረ ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ የሰው ኃብት ልማት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
- ከማንኛውም ወገንተኝነት (ፖለቲካ፤ ጎሳ፤ሃይማኖት፤ ወዘተ) ነጻ የሆነና እውቀትንናሙያንመሠረትያደረገየሰውኃይልቅጥር፤ ምደባ እና እድገትተግባራዊያደርጋል፡፡
- ሠራተኛው ስለመብቶቹና ጥቅሞቹ ለመደራደር የሚያስችለው አቅም እንዲያገኝ በመሥሪያ ቤቶች ቦርድ ውስጥ እራሱ ያለጣልቃ ገብነት የሚመርጣቸው ተወካዮች እንዲኖሩት አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፡፡
- ከፍተኛየትምህርትተቋማትየሰውኃይልፍላጎትናአቅርቦትጥናትላይየተመሠረተሥልጠናእንዲሰጡ፤የትምህርት ተቋማትንና የአሠሪዎች/ቀጣሪዎች ምክክር በማበረታታት የተማረው ወጣት ያለ ሥራ እንዳይቀመጥ ተግባራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡
- የሠራተኛናየሙያማኅበራትበነጻነትእንዲደራጁድጋፍማድረግናማኅበራቱየአባሎቻቸውንሙያዊብቃትእንዲያድግየሚ ያስችልየሰርተፊኬሽንመርሐግብርእንዲተገብሩያበረታታል፡፡
- ጠንካራ የሥራ ባህል እንዲያድግ በትምህርት ካሪኩለም ውሥጥ የሥራ ባህልን የተመለከተ ትምህርት ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ በትምህርት ካሪኩለም ውስጥ እንዲካተት ያደርጋል፡፡
- የሠራተኛው ክህሎት እንዲያድግ አሠሪዎች ከትርፋቸው ለሥልጠና እና ሌሎች አቅም ግንባታዎች በጀት እንዲመድቡና፤ ለዚህ የሚውለውንም ከታክስ ነጻ ይደረጋል፡፡
- በኢመደበኛ ከፍለ ኢኮኖሚ የተሰማሩ ዜጎች የሚደራጁበትና ህጋዊ የሚሆኑበት የሕግ ማዕቀፍ ይዘጋጃል፡፡
- የግል ዘርፉ የሰው ኃይል ከመቅጠር አንጻር በሂደት የአንበሳውን ድርሻ እንዲወስድ ይደረጋል፡፡
- ጠንካራና ዲሞክራቲክ የሆኑ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነትን የሚያሳልጡ ተቋማትን በመገንባት የኢንዱስትሪ ሰላም የሰፈነበት፤ ምርታማነት የጎለበተበት ከባቢ እውን እናደርጋለን፡፡
- የሠራተኞች እና የሙያ ማኅበራት በአገራቸው ሁለንተናዊ፤ ማለትም ፖለቲካዊ፤ማኅበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ በንቃት ተደራጅተው የሚሳተፉበት፤ ተወካዮቻቸውን በነጻነት የሚመርጡበት፤ ከጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው፤ ትርጉም ያለው አስተዋጽዎ ማበርከት እንዲችሉ ሁለንተናዊ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

ክፍል አምስት

5.1. ግብርናንገጠርልማት

ኢዜማ በምግብእህልራስንመቻል (self-sufficiency) ከሚለውአስተሳሰብበላይየምግብሉዓላዊነት ያረጋግጣል!

ለአገር ውስጥ ፋብሪካዎች በቂ ምርት ማምረት!

ደራጃውን የጠበቀ ዋጋቸው ከፍተኛ የሆኑ ምርቶችን ለውጭ ገበያ ማምረት!

ኢዜማ አንኳርየዘርፉንችግሮችለመፍታትየሚከተሉትንየፖሊሲእናእስትራቴጂክአቅጣጫዎችይከተላል፡፡

- ገበያ መር፣ የተቀናጀ፣ሁሉን አቀፍ የሆነና ሥነ ምህዳርን ናየተፈጥሮ ሀብት ጥበቃን እና መስኖን መሠረት አድርጉ ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ የሚጨምር የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲን ያራምዳል፡፡ ይህንም ለመፈፀም ይቻል ዘንድ እስካሁን የወጡ ሊሲዎችና እስትራቴጂዎችን ወቅቱን ባገናዘበ መልኩ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ እና የምርምር ግኝቶችን በግብዓትነት በመጠቀም በየጊዜው ከለሳ ይደርጋል፡፡

- መሬትን ፖሊሲን በተመለከተ፡-በሕዝብ ውይይትና ፈቃደኝነት ላይ በመመስረትየ ግል፣የመንግሥትና የማህበረሰብ የመሬት ባለቤትነት እንዲኖር ይደረጋል፡፡ መሬት ከአንድ የመሬት ባለቤት ወደሌላ ሦስተኛ ወገንበ ሽያጭ፣ በኪራይ፣ ወዘተ እንዲተላለፍ ይደረጋል፡፡መሬት ለሃገር ልማት ቁልፍ ሀብት በመሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃየ መሬት ፖሊሲ በማውጣት የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በመንደፍ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ሴክተሩም ከተበታተነ መስሪያቤቶች ሀላፊነትተ ሰብስቦበ አንድ መ/ቤት እንዲመራ ይደረጋል፡፡

- በሀገሪቱ የማምረት አቅም ያላቸውን አካባቢዎች በመለየት በተመረጡ የግብርና ምርቶች (ሰብሎች፣ተፈጥሮ ሀብት እና የእንስሳት ሀብት) ላይ በማተኮር ከፍተኛ ግብዓቶችን (መስኖ፤ የተሻሻሉ ዝርያዎች፣ ባዬቴክኖሎጂ፤ መካናይዜሽን፣ ወዘተ) እና የአሠራር ዘዴዎች በመጠቀም በዓመት ከሁለት ጊዜ በላይ በማምረት ምርት እና ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ በመጨመር በምግብ ራስን መቻልና ከውጭ የሚገባውን ምግብ በሀገር ውስጥ ምርት መተካት እንዲቻል ይደረጋል፡፡ (food security & Import substitutions)

- በዘርፉ የግል ሴክተሩ ሚና የማይተካ በመሆኑ የሥራው ባለቤት የሚሆንበትን ሁኔታ እንዲመቻች ይደረጋል፡፡ በዚህ ምመሠረት የግል ሴክተሩ የተለያዩ የግብርና ግብዓትና ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብ፣የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት፣ የእንስሳት ጤና አገልግሎት በመስጠት በግብርና ምርትማ ምረትና ግብይት ላይ ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ከዚህ አኳያ የመንግሥት ሚና በተመለከተ ለግሉ ሴክተር አስቻይ ሁኔታዎችን በመፍጠር፣ ደረጃዎችን በማውጣትና ቁጥጥር ማድረግና የግሉ ዘርፍ ለጊዜው ሊገባባቸው በማይችሉ ተግባራት ላይ ብቻ አተኩሮ እንዲሠራ ይደረጋል፡፡

- ግብርናን መሠረት ያደረጉ የገጠር ከተሞች እንዲፈጠሩ በማድረግና የከተማ ግብርናን እና ደን ልማትን በማስፋፋት፣ ትናንሽና መካከለኛ አግሮ ኢንዱስትሪዎች እና ሌሎች ቀላል ኢንዱስትሪዎችን እንዲስፋፉ አስቻይ ሁኔታዎችን በመፍጠር የወጣት ኃይሉን ሥራ በማስያዝ ለክፍለ ኢኮኖሚው አስተዋጽኦ እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

- ገበሬዎችና አርብቶ አደሮች ችግሮቻቸውን ፈትተው ፍላጐቶቻቸውን በጋራ ለማሳካት ይችሉ ዘንድ በነፃ ፍላጐት ላይ የተመሠረቱ የተለያዩ ማህበራት ከማንኛውም ያልተገባ ተፅዕኖው በሆነ መንገድ እንዲደራጁ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡

- የግብርና ምርምሩን ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት አሳታፊ እና ችግር ፈቺ የሆነ ምርምር እንዲስፋፋ ማድረግና የግብርና ምርምርና ውጤቶችን ከግል ሴክተሩ እና ከግብርና ኤክስቴንሽን እንዲሁም ትምህርት ተቋማት ጋር ተሳስረው እንዲሄዱ ከማድረግ አኳያ አጠቃላይ አሰራራቸው እና አደረጃጀታቸው ተፈትሾ እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

- ተፈጥሮ ሀብታችንን (ውኃ፣ ደን፣ ዱር እንስሳት፣ አፈር ብዝ ሀሕይወት ወዘተ) ለሀገራችን ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ዝርዝር እስትራቴጂ እና የድርጊት መርሀ ግብር እንዲወጣላቸው ይደረጋል፡፡በመነሻነት:

  - ✓ አሁን ያለውን ከፍተኛ የሆነ የአፈር ክለትና ለምነት መታጣት ለመቀነስ እስካሁን ይካሄዱ የነበረው የዘመቻ ሥራ በመለወጥ በሙያ በታገዘና ጥራቱን በጠበቀ ቴክኖሎጂዎች ሥነምህዳርንና ተፋሰስን መሠረት ያደረገ የአፈር ጥበቃ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲከናወን ይደረጋል፡፡

  - ✓ የውኃ ሀብታችንን (ከርሰም ድርና ገፀ ምድር) በአግባቡ መሰብሰብ፣ በመጠበቅና በመጠቀም የግብርናና ገጠር ልማቱ እንዲሳለጥ ይደረጋል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ከዚህ ቀደም የወጡ ፖሊሲዎችንና እስትራቴጂዎችን በመገምገም እንዲከለሱ ይደረጋል፡፡

  - ✓ በደን ሀብታችን ላይ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት በማካሄድ የሀገሪቱን የደን ሽፋን በማሳደግ ንዑስ ሴክተሩ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ያለውን ጉልህ ሚና እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ይህንንም ለማስፈፀም ራሱን የቻለ ተቋም እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

  - ✓ የዱር እንስሳት ሀብታችንን እና መጠለያ ቦታዎቻቸውን ሕብረተሰቡ ባሳተፈ እና ተጠቃሚ ባደረገ ሁኔታ በተገቢው መንገድ በመጠበቅ በመንከባከብና ጥቅም ላይ በማዋል ከፍተኛ መዋዕ ለነዋይ በመመደብ እና አግባብነት ያለው ተቋም በማቋቋም ከዘርፉ የሚገኘውን የቱሪዝም እና ሌሎች ገቢዎች ከፍ እንዲሉ ይደረጋል፡ ፡

- ሴቶች በግብርና ዘርፍ አስተዋጽአቸው የጐላ ቢሆንም ተጠቃሚነታቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ይህን ለማሻሻል ሥነ-ፆታን ታሳቢ የሚያደርጉ እስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞችን በመንደፍ ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

- በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ውስጥ ሥነምግብ ችግሮችን የሚፈታ አደረጃጀትና የቴክኖሎጂ ፓኬጅ እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

- የግብርናው ዘርፍ እድገት ለማፍጠን የገጠር መሠረተ ልማቶችን ማለትም የገጠር መንገድ፣ ቴሌኮሙኒኮሽን፣ መብራት፣ የመጠጥ ውኃ እና የመረጃ መረብ ስርዓት (ICT) ወዘተ በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡

- ለዝናብ አጠር እና አርብቶ አደር አካባቢዎች ካሉባቸው የተለዩ ችግሮች አኳያ ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችና የተቀናጁ የልማት ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ተቀርፀው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

የግብርና ዘርፍን የሚመራው መዋቅር የታለመውን የግብርና ፖሊሲ ሊያሳካ በሚችል መልኩ እንደገና በጥናት ተመስርቶ ይደራጃል፣ ብቃት ባለው ባለሙያ እንዲመራ ይደረጋል፡፡ እንዲሁ ምምርምር፣ የግብርና ኤክስቴንሽንና ገበሬዎች እና ሌሎች አጋር አካላትን አቀናጅቶ የሚያስተባብር ጠንካራ ተቋማዊ ሥርዓት እንዲፈጠር የምግብ ዋስትና እና ሥርአተ መብል ዋስትና

በምርትና በክምችት ወቅት የሚፈጠሩ ብክነቶችን በመቆጣጠር አፋጣኝ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ!

ምግብ በተመጣጣኝ ዋጋ ለዜጎች የሚቀርብበት ሥርዓት ማበጀት!

ሕፃናትና ታዳጊ ልጆች የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ማድረግ!

ኢዜማ የዜጎችን በምግብ ዋስትና እና ሥርአተ-መብል ዋስትና የፖሊሲ ግቦች ልዩልዩ የፖሊሲው የትግበራ አቅጣጫዎችን በመከተል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ያሳካል፡፡

- በመጀመሪያው አምስት አመት የመንግስትነት ጊዜው ዜጎች ያለሁኔታዎች ገደብ ጥራቱና ጤናማነቱ የተረጋገጠ ምግብ ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡
- የዜጎች የምግብ ተደራሽነት በይዘቱ ማእዳዊ ንጥረ-ምግብን ያሟላ እንዲሆን አስቻይ ሁኔታዎችን በመፍጠር በጊዜ ሂደት እንዲሟሉ ይደረጋል፤ ሕፃናት ተመጣጣኝ ምግብ የሚያገኙበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

- ምግብ ለዜጎች የእለት ከእለት እንቅስቃሴ እንዲሁም ተፈጥሮአዊ ብርታት ሰጪ እና ተፈጥሮአዊ የማሰላሰል ብቃታቸውን አበርች የሆነ እንዲሆን አስቻይ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡
- የህጻናትና ታዳጊዎችን የምግብ አቅርቦት በተመለከተ በቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ ሊያጋጥም የሚችልን የምግብ ዋስትና ጉድለት ማስቀረት/ከለላ ይሰጣል፡፡
- በምግብ አመራረት፣ አቅርቦትና ክምችት ችግር ሊመጡ የሚችሉ የምግብ ዋስትና ተግዳሮቶችን ከሚመለከተው ባለድርሻ አካል ጋረ በመሆን ቅድመ መከላከል እንዲሰራ ያደርጋል፡፡
- ዜጎች በሰው ሰራሽ እንዲሁም ተፍጥሮአዊ ችግሮች ምክንያት የሚያጋጥም የምግብ እጥረትን በአጭር ጊዜ መፍታት እንዲሁም በምግብ እጥረት ሊመጡ የሚችሉ የጤና እክሎችን መቆጣጠርና መቋቋም አስቻይ ሁኔታን የፈጥራል፡፡
- ዜጎች የምግብን አይነተ ብዙነት ከምግቡ ከሚገኝ ንጥረ ምግብ ይዘቶች አንጻር እንዲገመግሙና የአሰፈላጊነት ቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ እውቀትን መሰረት ያደረገ የአስቻይነት ትምህርት ይሰጣል፡፡
- የምግብ ደህንነትና ጥራት ተቆጣጣሪ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የምግብን እንዲሁም የምግብ ግብአቶችን ጥራትና ደህንነት እንዲያስጠብቅ የደረጋል፡፡
- በንግዱ ማህበረሰብ በምግብና ምግብ ግብአቶች ላይ የሚሰሩ ተገቢ ያልሆኑ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ይከላከላል፤ ተፈጽሞ ሲገኝ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡
- በምግብ ዝግጂት ጊዜ የሚባክን የምግብ ንጥረ ነገሮችን ማስቀረት የሚያስችል ትምህርት ለዜጎች ያቀርባል፡፡

5.2. ማዕድን

የማዕድን ዘርፉን ማጠናከር የውጭ ምንዛሪን ከማምጣት፤ ሥራ ከመፍጠርና የ አካባቢውን ማኅበረሰብ ከመጥቀም አኳያ ትልቅ ጠቀሜታ ስለሚኖረው፤ ኢዜማ ዘርፉን ለማሻሻል በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የሚከተሉትን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

- የማዕድን ሥራዎች በሚከናወኑበት አካባቢ ሁሉ ጸጥታና ደህንነትን ለማስከበር አስፈልጊውን ይፈጽማል
- አሁን ያለው የህግ ማዕቀፍ ለኢንቬስትሜንት በምያመች መልኩ እንዲቀረጽ ይደረጋል፡፡
- የማዕድን ኢንቬስትሜንት የአካባቢ ጥበቃን ባገናዘበ መልኩ እንዲሠራ ይደረጋል፤ የአካባቢው ኅብረተሰብ ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል፤
- የማዕድን ሥራ ባለሞያዎችን ቴክኒካል ሥልጠና በመስጠትና በማዕድን ሥራ ከፍትኛ ልምድ ካላቸው ሀገሮች ባለሞያዎች ጋር በማቀናጀት በጥራትም በቁጥርም እንዲጨምሩ ይደረጋል፤
- በማዕድን ሥራ ላይ የተሠማሩ ኢንስቲቱሽኖች አቅም እንዲዳብር ይደረጋል፤
- የመሠረተልማት አቅርቦትና የጸጥታ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ አስፈልጊው ሁሉ ይደረጋል፡፡

5.3. ኢንዱስትሪ

ከውጭ እየገቡ ያሉ ነገር ግን በአገር ውስጥ ሊመረቱ ለሚችሉ የፍጆታ እቃዎች ቅድሚያ ይሰጣል!

የኢንዱስትሪ ልማት ከኢኒፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጋር በማቀናጀት ተወዳዳሪ እንዲሆን ይደረጋል!

የግል ዘርፍ በዋነኝነት እንዲሳተፍ በማድረግ የሥራ እድሎች እንዲፈጠሩ ይደረጋል!

መሰረቱ የአገር ውስጥ ግብዓት ለሆነ ኢንዱስትሪና ማንፋክቸሪንግ ዘርፍ ቅድሚያ የሚሰጥ!

የአጎራባች አገራትን ፍላጎት ከአገር ውስጥ ፍላጎት ጋር በመደመር አዋጭነትን ያረጋግጣል!

ኢዜማ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡት አብዛኞቹ የፍጆታ እቃዎች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ፍጆታችንን ወደ ሌሎች ወሳኝ የካፒታል እቃዎች ከማዋል ባሻገር፤ ከፍተኛ የሥራ እድል እንዲፈጠርያደርጋል፤ በጊዜ ሂደትም የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ሰለዚህ በአገር ውስጥ የማምረት

አቅምን በመገንባት፤ የአገር ውስጥ የግል ኢንዱስትሪ በመሪ ተዋናይነት ዘላቂ እድገት እንዲያመጣ እና በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለመሆን እንድንችል አልመን እንሰራለን፡፡ፓርቲያችን በፖሊሲው የሚከተሉትን ዋና ዋና ውጤቶችን ያሳካል፤

- ኢንዱስትሪው የሀገር ውስጥ እምቅ ሀብት አጠቃቀምንና የሃገር ውስጥ ፍልጎቶችን መሰረት ያደርጋል፤
- የምርት ዓይነት ብዝሀነትና ከፍተኛ የገበያ ተደራሽነትን እና እሴት በመጨመርና ምርታማነትና ውጤታማነት ያላቸው ዘርፎች ላይ ትኩረት ያደርጋል፤
- በከፍተኛ ጥራት፣ በዋጋና በብዛት የማቅረብ ተወዳዳሪ የሆኑ ኢንዱስትሪዎች ይገነባሉ፤ ምርቶቻቸውን በዓለም ገበያ የማስተዋወቅ ጠንካራ ሥራ ይሠራል፤
- ከብልሹ አሰራርና ስር ከሰደና ሙስና ነፃ የሆነ የኢንዱስትሪ ስርዓት ይገነባል፤ወቅታዊነቱን የጠበቀና ጠንካራ የስራ ፈጠራ ተወዳዳሪነትና ክህሎት እንዲኖር ትኩረት ይደረጋል
- ለሀገራችን ተገቢነት ያለውና ዘመናዊ የቴክኖሎጂ አጠቃቀሞችን ትግባራዊ ይደረጋሉ፤
- ለኢንዱስትሪ ግንባታ ልዩ የፋይናንስ አቅርቦትና የመሬት አቅርቦት ስርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፤
- የተሳለጠ መሰረተ-ልማት፣ ሀይል አቅርቦት፣ ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሲስተም ይዘረጋል፤
- ኢንዱስትሪን ከግብርናው ዘርፍ ጋር በማቀናጀት አስተማማኝና ጥራት ያለው የግብዓት አቅርቦት እንዲፈጠር ስርዓት ይዘረጋል፤
- በአነስተኛ፣ መካከለኛና ግዙፍ ኢንዱስትሪዎች መካከል ያለው ትስስር በመዋቅራዊ ስልት (ኢኮኖሚስ አፍ ስኬልስ) የተገነባ ስርዓት ይፈጠራል፤
- የግሉ ዘርፍ የኢንዱስትሪ ክ/ኢኮኖሚው ዋና ተዋናይ እንዲሆን የደረጋል፤ሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ከውጭ በሚመጣ ተመሳሳይ ሸቀጥ እንዳይዳከሙ የታሪፍ እገዳ ፖሊሲ ይቀረጻል፤ የገቢ ንግድን የሚተኩ ኢንዱስትሪዎች (Import Substitution Industries) በስፋት ይገነባሉ፤
- በኢንዱስትሪ ውስጥ የሚቀጠሩ ዜጎች ደህንነት በዓለም አቀፍ መስፈርት መሰረት ይሆናል፤ ይህን ለማስፈጸም ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል፡፡

5.4. ንግድ

ዓላማችን ሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ፤ በተረጋጋ ሁኔታዎች መሰረታዊ ዕቃዎች እንዲያገኝ ማድረግ ነው!

ያልተዛባ ተጠያቂነት ያለበት የገበያ ሥርዓት መገንባት!

የግል ባለሀብቶች ሚና ለአገር ልማት ያለውን ሚና ከተጠያቂነት ጋር እንዲኖር እናደርጋለን!

ኢዜማ አምራቹንከተጠቃሚውጋርበቀላሉእንዲገናኙ የሚያደርግ ያልተንዛዛ የንግድ ሰንሰለትን በመፍጠር ለሁሉም ተወዳዳሪዎች እኩል እድል የሚሰጥና የንግድ ውድድር ላይ መሰረት ያደረገ፤ የንግድ ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ ዋነኛ ግቡ ነው፡፡ በሌላ በኩል የወጭንግድንበማስፋፋትና የተዛባውንንግድ ሚዘን ለማስተካከል፤ መሰረታዊየሀገርውስጥየፍጆታእቃፍላጎቶችንበሀገርውስጥእንዲሸፈኑ ለማደረግ ቀዳሚትኩረቱአድርጎ ይሰራል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ይህ ፖሊሲ የንግድ ባህላችንን በዘላቂነት ለመቀየር በሚረዱ የትግበራ መርሆዎች ላይ የተመሰረተ ሲሆን ከላይ የጠቀስነውን ግብ ለማሳካት የሚከተሉትን ዝርዝር ስራዎች ያከናውናል፡፡

- የንግድ ሚኒስትርንና የንግድ ቢሮዎችን በቴክኖሎጅ በማዘመን እያንዳንዱ ግብይት በመንግስት የታወቀ እና በኤሌክትሮኒክስ የግብይት ውስጥ የሚያልፍ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
- በተደጋጋሚ የሚታዩ የንግድ ማዛባት፤ የተጋነነ ዋጋ የመጨመር፤ የንግድ ማጭበርበር እንዲሁም እንደ ኮንትሮባንድ ያሉ ተግባሮችን ለመከላከል ጠንካራ የቁጥጥር ተቋም እንዲኖር ይደረጋል፡፡
- ጠንካራና ዓላማውን የተረዳ የሸማቾችን ጥቅም የሚያስጠብቅ ተቋም እንዲኖር ያደርጋል፤
- ለኤክስፖረት የሚዉሉ ምርቶችን ግብይት ለማሳለጥ የምርት ገበያ እንደገና እንዲዋቀር ይደረጋል፤ ላኪ ለመሆን የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሻሻል ገበያ የሚያበላሹ ላኪዎችን እንዳይኖሩ ያደርጋል፡፡

- በአትክልትና ፍራፍሬ ግብይት ላይ የሚታየውን ችግር ለመፍታትና አምራቹ ምርቱን ለተጠቃሚው እንዲያቀርብ፤ አምራች ብቻ የሚሳተፍበት የመገበያያ ቦታ በአዲስ አበባ፤ በክልልና በዞን ከተሞች እንዲቋቋም ይደረጋል፤ በየአካባቢውም የህብረት ስራ ማህበራት እንዲደራጁ ይበረታታሉ፡፡
- የቁም እንስሳት አክሽን ገበያ በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች እንዲቋቋም ይደረጋል፤ አምራቾችን ከተጠቃሚው ጋር በቀጥታ የሚየገናኝ ሰንሰለት ይዘረጋል፡፡
- ስትራቴጅክ ኤክስፖርት ምርቶቸን በመለየትና የተለየ ትኩረት እንዲሁም ድጋፍ በማደረግ የሀገራችን የወጭ ንግድ ለማሳደግ በትኩረት ይሰራል፡፡
- የውጭባለሃብቶችንእንደዋነኛየኢኮኖሚአንቀሳቃሽናላኪአድርጎዘላቂለውጥማምጣትከባድ በመሆኑ፤ ጠንካራ የሃገርውስጥባለሃብቶችን ለመፍጠር የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
- ለላኪዎች የገበያ ትስስር ለመፍጠር ኢምባሲዎች ገበያ ማፈላለግ አንዱና ዋነኛ ስራቸው እንዲሆን ይደረጋል፤
- በጎረቤት ሃገራትና በአፍሪካ ያለንን የንግድ መዳረሻ ለማስፋት የኢትየጵያ አየር መንገድና የውጭ ንግዱን የሚመሩ ባለስልጣናት የሚያገናኝ ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡
- በሀገር ውስጥ መመረት የሚችሉ ምርቶችን በመለየት በየአመቱ የኢምፖርት መጠናቸው እንዲቀንስና በሂደትም ዜሮ እንዲሆን ለማድረግ በእቅድ ይሰራል፡፡

5.5. ቱሪዝም

ኢዜማ ቱሪዝምለሀገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት ያምናል፤ ስለሆነም ዘርፉ እንዲያድግ አጥብቆ ይሠራል፤ በሚቀትሉት አምስት ዓመታት የሚከትሉትን ዝርዝር ተግባራት ያከናውናል፡፡

- የቱሪስት መዳረሻዎችን ዓለም አቀፍ ደርጃን የጠበቁ እንዲሆኑ የመሠረት ልማት ግንባታ ያካሂዳል፤ ዘመናዊ የቱሪዝም ማስተዋወቅ እና የገበያ ሥርዓት እንዲኖር ይድረጋል፤
- በቱሪስት መዳረሻ አካባቢ የሚገኙ ዜጎች በአግባቡ ተጠቃሚ የሚሆኑበትና ከድህነት ወጥተው እራሳቸውን እንዲችሉ የሚያደርግ ሥርዓት ይበጃል፤ በቱሪስት አካባቢዎች ባጠቃላይ በአገራችን የቱሪስትን እንቅስቃሴ የሚገቱ የፀጥታና የደህንነት ችግሮች ማስወገድ ቀዳሚ ስራችን ይሆናል፣
- ለቱሪዝም ልማት የሚያስፈልጉ ቱሪስት ጋይዶች/ በፕሮፌሽናል ደረጃ እንዲሰለጥኑ ይደረጋል፤ የተለያየ የቋንቋ የትርጉም ሥራዎች በቦታው እንዲገኝ ይደረጋል፤
- በዓለም አቀፍ የቱሪዝም መድረኮች ከፍተኛ የማስተዋወቅ ሥራዎች እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤
- ለኮንፈረንስ ቱሪዝም ከአዲስ አበባ በተጨማሪ ሌሎች አካባቢዎችን ተለይተው እንዲለሙ ይደረጋሉ፤
- ከኤርትራ ጋር እየተፈጠረ ያለውን ሠላም ወደ ኤኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማሳደግ የተቀናጀ የቱሪዝም ልማት በምፅዋ እና አዲስ አበባ/ባህር ዳር/አክሱም/ጎንደር የአየር በረራዎችን ጨምሮ የጉዞ መስመር እንዲከፈቱ ይደረጋል

5.6. መሠረተ ልማት

5.6.1. መንገድ

የገጠር መንገዶች ሥራ በሕብረተሰብ ተሳትፎ በመስራት ለወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠሪያ እንዲውል ይደረጋል፡፡

የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮ ከአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች ጋር በጋራ የሚሰሩበት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚረጋገጥበጥ ሥርዓት ይበጃል!

በዘርፉ የተንሰራፋው ሙስና እና ብልሹ አሰራር በመሰረታዊነት እንለውጣለን!

ለቱሪዝም ዘርፍ ልማት ቅድሚያ ተሰጥቶ የመንገድ ሥራዎች ይሰራሉ!

የመንገድ ዘርፍ እድገት ለህገራችን የኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ በመሆኑ ኢዜማ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ዘርፉን ለማሳደግ የሚከትሉትን ያደርጋል፡፡

- ለመንገድ ዘርፍ አሁን እየተሰጠ ያለውን የበጀት ምደባ የሚደግፍና የሚያጠናክር ሲሆን፤መንግድ ግንባታዎች የኢኮኖሚ አዋጭነት በደንብ የሚጠና ሲሆን፤ በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያ በቱሪዝም ሴክተር ያላትን የተፈጥሮና የታሪክ ሀብት ለጥቅም ልታውል በምትችልበት መንገድ ታቅዶ ይሰራል፡፡
- ለውጭ አገር የሚሰጡ ኮንትራቶች ከአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች ጋር በጋራ እንዲሆን በማድረግ የቴክኖሎጂ ሽግግር በተለይ የመንገድ ግንባታ አስተዳደር ልምድ እንዲቀሰምበት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡
- በዘርፉ የሚታየውን ሥር የሰደደ ሙስና እና የሥራ መጓተት በማስወገድ መንገድ ለኤኮኖሚ እድገት ያለውን ወሳኝ ሚና በአጭር ጊዜ እንዲያሳይ ያደርጋል፡፡ በዘርፉ የሚታየውን ብልሹ አሰራር በማስወገድ ለወጪና ገቢ ንግድ ዋጋ ንረት መንስዔ እንዳይሆን ይደረጋል፡፡
- የአገር ውስጥ አቅምን በማጎልበት በወጣቶች የሚመራ የክረምት ከቢጋ መንገድ በሁሉም አካባቢ እንዲተገበር በማድረግ ዋንኛ የሥራ እድል መስክ ይደረጋል፡፡

5.6.2. ባቡር

የባቡር መስመር ግንባታዎች ወጤታማ በሆነ መንገድ እንዲተገበሩ ያደርጋል!

የኢትዮጵያዊያን ባለሀብቶች በከፍተኛ ደረጃ በባለቤትነት በተለይ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ተደራጅተው በባለቤትነት እንዲገንቡት ይደረጋል!

የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ይደረጋል!

ኢዜማ የባቡር ትራንስፖርት ከሎጂስትክስ አንጻር ኢኮኖሚውን ከማነቃነቅ አኳያ ከፈተኛ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ በሚቀትሉት አምስት ዓመታት የሚከተለውን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

- አሁን በዕቅድ ያሉትን የባቡር መስመር ግንባታዎች ወጤታማ በሆነ መንገድ እንዲተገበሩ ከማድረግ ጎን ለጎን ሀገራዊ የባቡር ኔትወርኩ ፍትሃዊ እንዲሆን በማድረግ እና የኢትዮጵያዊያን ባለሀብቶች በከፍተኛ ደረጃ በባለቤትነት ጭምር እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡
- አሁን ባለው ሁኔታ የባቡር መስመር ዝርጋት የሚፈልገውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከግምት ውስጥ በማስገባት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በአክሲዮን ተደራጅተው በባለቤትነት እንዲገነቡት፣ ለቴክኖሎጅ ሽግግር የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ሁሉን አቀፍ የፖሊሲ አማራጮች አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

5.6.3. ኃይል አቅርቦት

በገጠር የሶላር ኢነርጂን በማስፋፋት የሀይል ብክነት የመቀነስ ሥራዎች ይሰራሉ! ከከተማ ርቀው የሚገኙ ዜጎች አማራጭ የሀይል ምንጭ ሆኖ ያገለግላል!

የህዳሴ ግድብን ማጠናቀቅ ወሳኝ ተግባር ተደርጎ ይወሳዳል፤ ሕዝቡ ለሕዳሴ ግድቡ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ እንዲያደርግ ይደረጋል!

ኢዜማ የኃይል ፍላጎት መሟላት ለኢኮኖሚ ዕድገታችን ወሳኝ በመሆኑ በሚቀጡት አምስት ዓመታት የሚከተሉትን ዋናዋና ተግባሮች ያከናውናል፡፡

- በአጭር ጊዜ በጅምር ያሉትን የህዳሴ ግድቡን ጨምሮ ሌሎች የሀይል ማመንጫዎች በከፍተኛ የህዝብ ተሳትፎ እና ብቃት ያለው አመራር በመስጠት እንዲጠናቀቁ በማድረግ፤ የሀይል ፍላጎት እንዲሟላ ያደርጋል፡፡
- በቀጣይ አገራችን ያላትን የተፈጥሮ ፀጋዎች በመጠቀም አሟጠን የምንጠቀም ሲሆን፤ ዘላቂ የሆነ የሀይል ልማት ለማረጋገጥ ሠላማዊ የኒዎክለር ሀይል እንደ ወሳኝ አማራጭ የሚወስደው ይሆናል፡፡
- የገጠር እና ርቀት ባላቸው አካባቢዎች ተገቢው ድጋፍ የሚደረግለት የሶላር ኢነርጂ አጠቃቀም ስትራቴጂ በመቀየስ የሀይል ብክነትን የምንከላከል ሲሆን፤ በግላቸው የሀይል ፍላጎት ለማሟላት ለሚፈልጉ ኢንዱስትሪዎችም ሆነ ሌሎች የግል ባለሀብቶች ተገቢው ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል፡፡

5.6.4. የውሃ አቅርቦት

የውሃ ሀብታችንን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ቅድሚያ የኢንቨስትመንት አቅጣጫ በማድራግ፤ በምግብ እህል ራስን ለመቻል ባለን ራዕይ እና ዜጎችን በንፁ የመጠጥ ውሃ ማቅረብ፤ ለአርብቶ አደሩ የውሃ ተደራሽነት ለማረጋገጥ በሙሉ ሀይላችን የምንሰራ ሲሆን

- የተትረፈረፈ የውሃ ሀብቷን፤ የዉሃ ሀብቶቹ ከሚገኙበት ጂኦግራፊካል ቦታዎች፤ ወደየአቅጣጫው በተደራጀ የፐምፒንግ ሲስተም በማጓጓዝ፤ከዝናብ ሌላ የውሃ ምንጭ የሌላቸውን ደረቅ መሬቶች በተለያየ የኢሪጌሽን አይነቶች፤ ለምሳሌ የሜዳ (ፒቮት) ኢሪጌሽን፤ የጠብታ ኢሪጌሽን ወዘተ በመተግበር፤ የገበሬ መሬቶችን ከዝናብ ጥገኛነት እና በአመት አንዴ ወይም ቢበዛ ሁለቴ አምራችነታቸው ተላቀው፤ እስከ ሶስት አራት ግዜ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን (ስቴፕል እና ካሽክሮፕ የሆኑ እንዲሁም አትክልት እና ፍራፍሬዎችን) እንዲያመርቱ እናደርጋለን፤ የግል ሴክተሩ ጉልህ ሚና እንዲጫወት እናደርጋለን፤

- በበጋ ወራት ኢሪጌሽን በመጠቀም የእንስሳት መኖዎችን በደጋው አካባቢ የሚገኙት የገበሬ መሬቶች ላይ በማምረት፤ ኢትዮያውያን ገበሬዎች መስራት የሚወዱትን የእንስሳት እርባታ ውጤት በብዙ እጥፍ ማሳደግ፤ የአገሪቱን የእንስሳት እርባታና የእንስሳት ውጤቶች ምርትን በብዙ እጥፍ በማምረት፤ ሃብታም ገበሬዎችን መፍጠር፤ በምግብ ራስን የመቻል ራዕይን ማሳካት እንሰራለን፤

- በበረሃ አካባቢ የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን አርብቶ አደር በመሆናቸው፤ እንስሳት በሚሰማሩበት ቦታዎች ላይ ውሃ በማድረስ እና የበረሀ ቡሾች እና ግራሮች የመሳሰሉትን እጽዋት ቅጠል እንዲያፈሩ በማድረግ ፤ የተለያየ ቦታ ግጦሽ በመፈለግ የሚባዝነውን የኢትዮጵያ አርብቶ አደር፤ በመረጠው ቦታ ሰፍሮ ከብቶቹን እንዲያግድ ማስቻል፤ በግጦሽ ቦታ ሽሚያ ምክንያት የሚፈጠረውን አርብቶ አደር ህዝብ ግጭቶች ሙሉ በሙሉ መቅረፍ፤ ከከብት ስምሪት ውጭ የሆነውን ሰፊ የበረሃ መሬት ለሰፋፊ (ሜጋ) እርሻዎች)እንዲዉሉ በማድረግ ውጤታማ የመሬት አጠቃቀም እናረጋግጣለን፤

- ሥር ነቀል የሆነ የመስኖ እና የውሃ አጠቃቀም ሥርዓት በመዘርጋት፤ ኢትዮጵያን አመት ሙሉ አምራች አገር ማድረግ፤ ቢያንስ ለምስራቅ አፍሪካ በቂ እህል ማቅረብ የሚያስችል አቅም እንፈጥራለን፡፡

5.6.5. ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ

ኢዜማ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን ለኤኮኖሚው የጀርባ አጥንት፤ መንግስትን ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥበት እንዲሆን እንሰራለን!!

ኢትዮጵያ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቀዳሚ እንጂ ተከታይ እንዳትሆን እንሰራልን!!

ኢዜማ አገራችን ኢትዮጵያ ከሌሎች ዓለማት ጋር በኢኒፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ዓለም በደረሰበት ደረጃ ለመድረስ ትችላለች ብሎ ያምናል፡፡ ይህን እምነት ተግባራዊ ለማድረግ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የሚከተሉትን ዓላማዎች ያሳካል፡፡

- ከአይሲቲ በየዓመቱ 1% የጂዲፒ እድገት በማስመዝገብ፤ ቀጥታ ተጠቃሚ ለሆኑ 500,000 ዜጎችና ቀጥተኛ ተተቃሚ ላልሆነ 1.5 ሚሊዮን ተጨማሪ ዜጎች የሥራ ዕድልን ይፈጥራል፤
- በአምስት ዓመቱማጠናቀቂያ ላይ የመንግስት አገልግሎቶች መቶ በመቶ በአስተማማኝነት በበይነመረብ አማካኝነት የማቅረብና የቴሌኮም ተደራሽነት 80% እና የበይነመረብ ተደራሽነት 60% ለማድረስ በአይሲቲ ልማት ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ከ1 እስከ 3ኛ ደረጃ ለማድረስ ይሠራል፤
- በበይነመረብ አማካኝነት የሚሰራጩ ሃሰተኛ መረጃዎች የኢትዮጵያ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ህይወት ላይ ተጽዕኖ የማያሳድሩ እንዳይሆኑይሰራል።
- በቴሌኮም ዘርፍ ተወዳዳሪ አካባቢን በመፍጠር አቅምን ያገናዘበ የብሮድባንድ መሰረተ ልማት በማቅረብ ተደራሽነትንና የአገልግሎት ጥራትን ይጨምራል፤

- ኢንዱስትሪዎችን ለመደገፍ የፖሊሲ እና ደንብ ማዕቀፍ ያዘጋጃል። ይህም ለአውታረ መረብ ማስፋፊያ ምቹ ሁኔታን መፍጠር፣ ለግል ዘርፉ ድጋፍ ማድረግና ፈጠራን ያበረታታል፤
- ዲያስፖራው እና ወዳጅ ሃገሮች ለአይሲቲው ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጾ እንዲያደርጉ ያመቻቻል።ይህም ትልቅ እውቀትና ልምድ ያዳበሩ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የዲያስፖራ አባላትንና የሌሎች አገሮችን የላቀ የሰው ሃይል በመጠቀም ክፍተቶቻችንን እንዲሞላ ይደረጋል፤
- ግልጽ (open) እና ዲጂታል መንግስት በመፍጠር ሙስናን ለመዋጋት ምቹ ሁኔታ እንፈጥራለን፤
- የሥራ ዕድሎች እና ሃገራዊ የአይሲቲ ዘርፍ እንፈጥራለን፤ ለዚህም ስራ ፈጣሪነት እና ፈጠራን (innovation) የሚያበረታታ ሃገራዊ የአይሲቲ ስርዓት ይዘረጋል፤
- በመደበኛ ትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ለሆኑ ዜጎችን የአይሲቲ አቅም ግንበታ ሥርኣት ይበጃል፤
- ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት እና የግለሰብ መረጃ ጥበቃ መዋቅር ይገናባል በአግባቡ በሥራ ላይ ይውላል፤በሃገር ውስጥ እና ከሃገር ውጪ ያሉ ምሁራንን ያካተተ የብሔራዊ አማካሪ ኮሚሽን ይቋቋማል፡፡

5.7. ፋይናንስ

ለሴቶች ለወጣቶችና አዲስ ሃሳብ አመንጪዎች የፋይናንስ ተቋማት በተለየ ሁኔታ የብድር አገልግሎት እንዲያዘጋጁ ይደረጋል!

የመንግሥት ብድር በሕዝብ ወኪሎች ቁጥጥር የሚደረግበት ይሆናል!

የኢትዮጵያብሄራዊባንክየሃገሪቱማዕከላዊባንክእንደመሆኑየሃገሪቱንየገንዘብፖሊሲናየገንዘብተቋማትንየሚቆጣጠርተቋምነው፡፡ የዚህባንክጠንካራመሆንበሃገሪቱየፋይናንስተቋማትጤናማናጠንካራመሆንብቻሳይሆንበአጠቃላይኢኮኖሚውላይያለውእንደም ታእጅግከፍተኛስለሆነ ኢዜማ በሚቀትሉት አምስት ዓመታት የሚከተሉትን ያከናውናል፡፡

- ብሄራዊባንኩበብቁባለሙያዎችእንዲደራጅናጊዜውየሚጠይቀውንአመራርእንዲሰጥያደርጋል፡፡
- የፋይናንስ ክፍለ ኢኮኖሚው በየጊዜው በርካታ ለውጦችን እያስተናገደ በመሆኑ፤ አሁን በስራ ላይ ያሉ ባንኮችን ያህል አዳዲስ ባንኮች እየተቋቋሙ በመሆኑ፤ የብር የመግዛት አቅም በየጊዜው በፍጥነት እየቀነሰ በመምጣቱ፤ የአክሲዮን ገበያ ሊጀመር እንቅስቃሴ በመኖሩ፤ ሌሎችእነዚህና መሰል ለውጦች በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ ያለውን እንደምታ የሚያጠናና አፋጣኝ እርምጃዎችን በየወቅቱ የሚወስድ ባለድርሻዎችን የሚያሳትፍ የመማከርት ጉቤ ያቋቁማል፤
- የመንግስት ብድር በጣም ከፍተኛ በመሆኑ፤ ከመክፈል አቅሙ ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን፣ የብድሩንም መጠን ለህዝብ ተወካዮች ምክርቤትና ለኢትዮጵያ ህዝብ በየሩብ ዓመቱ እንዲገልፅ የሚያደርግ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
- ባንኮቻችን ከዋስትና ማቅረብ ጋር ብቻ የተያያዘውን የብድር አሰጣጥ በመለውት አዋጭ የሆነ ሃሳቦችን መዝነው ብድር የሚያቀርቡበትን አሰራር ይዘረጋል፤ አዳዲስ ሃሳቦች የብድር ዋስትና ማቅረብ ባለመቻሉ መክነው እንዳይቀሩ በመንግሥት ዋስትና ብድሮች እንዲሰጡ ሥርዓት ይበጅለታል፡፡ በዚህም በርካታ አዳዲስ ድርጅቶች እንዲቋቋሙና ብዙ ሃብት እንዲፈራ፤ ብዙ የስራ እድል እንዲፈጠር እናደርጋለን፡፡
- ኢዜማ በቁጠባ ከሚገኘው ውስን ሃብት ለሃገራችን የኢኮኖሚ እድገት ላይ ወሳኝ ሚና ለሚጫወቱት ለግብርናና ለወጪ ንግዱ፣ እንዲሁም በርካታ የስራ እድል ለሚፈጥሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የተሸለ የብድር አቅርቦት እንዲያገኙ እናደርጋለን፡፡ ይህን ለማድረግ እንዲያግዝ የአነስተኛ ብድር ተቋሞቻችን ለብድር የሚያቀርቡት ገንዘብ እንዲያድግ፣ የሰለጠነ የሰው ሀይል እንዲኖር፣ የፋይናንስ መሰረተ ልማት በበቂ እንዲዘረጋ፣ በማድረግ እነዚህ የፋይናንስ ተቋማት ተገቢው ድጋፍ ይሰጣቸዋል በተሸለ አቅም እንዲሰሩ በማድረግ ማህበረሰቡን እንዲያግዙ ያደርጋል፡፡

5.8. ከተማ ልማት

በአግባቡ የሚመራ የታቀደ የከተማ ልማት!

ለኑሮ ምቹ አረንጓዴ ከተሞችን በመመስረት ከተሜነትን እናበረታታለን!

ኢዜማ የከተማ ልማትን ሂደቱም ሆነ ውጤቱ ያሉብንን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች እንዲያሻግረን እና በሁለንተናዊ እድገት የነለበተች ሀገርን እንድንገባ በማለም በከተማ ልማት ዘርፍ የሚከተለውን እቅድ ይተገብራል።በዚህ እቅድ የከተሜነት ምጣኔን በአምስት አመት ጊዜ ውስጥ ከአርባ በመቶ በላይ ለማድረስ እና ከተሞቹም ለኑሮ የሚመቹ፣ ሁሉን አቀፍ፣ አሳታፊ፣ ስራና ገቢን የሚፈጥሩ፣ መሬት እና ሀብት ቆጣቢ እንዲሁም አካባቢን የሚጠብቁ እንዲሆኑ እንሰራለን።

- ከተሞች የራሳቸውን ከንቲባ እና አስተዳደር በቀጥታ የሚመርጡበትን ስርአት ያመቻቻል።
- ነዋሪዎች በከተማ ምክር ቤት የሚወሰኑ ውሳኔዎችን እንዲያውቁ በሲቪክ ማህበራት በመገኘት እንዲሞግቱ ክፍት ይሆናል።
- የከተማ ልማት ሂደት፣ ልማቱ የሚነካቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ከጽንሰ ሃሳብ ጀምሮ በተለያየ ደረጃ በማሳተፍ እንዲካሄዱ ያደርጋል።
- የከተማ ልማት ተቋማት፤ መሰረተ ልማቶች፣ የቤት እና የትራንስፖርት አገልግሎት ማቀናጀት እና ማናበብ እንዲችሉ ስልጣን ተሰጥቷቸው ይዋቀራሉ።
- የከተማ ፕላን መመሪያዎች ደንቦች እና ህጎች ጥቅጥቅ እድገትን ማምጣት እንዲያስችሉ ተደርገው ይከለሳሉ።
- ነዋሪዎች መሬት አዋጥተው እና ከአልሚ ጋር በመተባበር የበለጠ ጥግግት በሚፈጥር መልኩ አልምተው የልማቱ ባለድርሻ የሚሆኑባቸውን የሽርክና እና የአጋርነት መመሪያዎችን ያወጣል፣ ይከልሳል።
- የአዳዲስ ከተሞች ግንባታ እንጀምራለን
  - ✓ በየወረዳው በአማካይ ሁለት ማለትም አንድ ሺህ አነስተኛ የገጠር ከተሞችን ከግል አልሚዎች ጋር በመሆን ማደጊያ ፕላን አዘጋጅተን፣ ቀይሰን እና ማስጀመሪያ ፈንድ አዘጋጅተን ልማታቸውን እናስጀምራለን። የገጠር ቤቶች ልማትን ከነዚህ ከተሞች ግንባታ ጋር በማያያዝ እንመልሳለን።
  - ✓ ስድስት ክልል አጣማሪ ከተሞችን ክልሎች በሚዋሰኑባቸው ቦታዎች ላይ፣ በክልሎች ስምምነት ቦታ ለይ ተን በሜትሮ ፖሊስ ደረጃ የሚያድጉ ከተሞችን ጥናት እናስጠናለን ከነኚህ መሃል የሁለቱ ንግንባታ እናስጀምራለን።
  - ✓ ጅምር ከተሜነት ባለባቸውና ምንም ባልተጀመረባቸው ቦታዎች የቦታዎቹን አካባቢያዊ ጸጋ በማጥናት እና በብሔራዊ ስፓሻል ፕላን በመወን የልዩ ትኩረት ከተሞችን በአይሲቲ፣ በኢንዱስትሪ፣ በቱሪዝም፣ በባህል፣ በከፍተኛ ትምህርት እና በመሳሰሉት ሳቢ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የተመሰረቱ ከተሞችን ፕላናቸውን እናቅየሳቸውን አጠናቀን ግንባታቸውን እናስጀምራለን።
- የቤቶች ልማትን በአምስት አማራጮች እናካሂዳለን። በሁሉም አማራጮች አረንጓዴ ልማት የምር ተግባራዊ ይሆናል፤ነ) የቤቶች ልማት በግልና በመንግስት አጋርነት፤ 2) የቤቶች ልማት በግልና በነዋሪዎች ሽርክና፤ 3) የቤቶች ልማት በአልሚዎች፤ 4) ገቢን ያማከሉ እና ደረጃቸውን የጠበቁ የኪራይ ቤቶች፤ እና 5) ለማህበር ገንቢዎች የድጋፍ ማእቀፍ ናቸው።:
- ሁሉም የቤት ልማት አማራጮች በዋናነት በግል አልሚዎች የሚለሙ ሲሆኑ መንግስት የቤትን ዋጋ ለማውረድ፣ በመሬት በፋይናንስ እና በግብር ላይ ያሉ ማነቆዎችን በማንሳትና በማመቻቸት ይሰራል።
- ከዚህ በፊት በጋራ መኖሪያ ቤቶች ተመዝግበው የሚገኙ ነዋሪዎችን ከተዘረዘሩት ውስጥ በምርጫቸው በተለይ ደግሞ ወደ መጀመሪያው አማራጭ በማሻገር ተመዝጋቢዎች የቤት ግንባታቸው ወደሚቀጥለው የምርጫ ዘመን እንዳይሻገር ለማድረግ ይሰራል።
- ይህ ከፍተኛ የሆነ የቤት ግንባታ የሚፈልገውን ግብአት የሚያቀርቡ ኢንደስትሪዎችን በመሳብ የአቅርቦት፣ የውጭ ምንዛሬን እና የስራ እድል ችግሮችን ለመፍታት ይሰራል።

- የትራንስፖርትአገልግሎትንተደራሽእናየሚተነበዩእንዲሆኑያደርጋል።

  ✓ የመሬትአጠቃቀምንበማሻሻልየሞተርነክተሽከርካሪንአስፈላጊነትለመቀነስይሰራል።

  ✓ ከግል አልሚዎች ጋር በመሆን እስከ ፈርጅ ሁለት ባሉ ከተሞች ዘመናዊ የከተማ አውቶብስ ስርአት ይዘረጋል።

- የከተማ አገልግሎቶች ማለትም ውሃ፣ ፍሳሽ፤ ሃይል፣ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር፣ የእሳት አደጋ፣ አምቡላንስ፣ የምግብ እና ደህንነት ቁጥጥር፣ ጤና እና ትምህርት፣ ደህንነት እና ትራንስፖርት ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ይሰራል።

  ✓ ሀላፊነት በተረከበባቸው ከተሞች ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ አገልግሎቶቹ ያሉበትን ትክክለኛ የአቅርቦት እና የፍላጎት ክፍተት ለህዝብ ይፋ ያደርጋል።

  ✓ ከግል አልሚዎች እና አለምአቀፍ አጥኚዎች ጋር በመተባበር፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፈንድ በማሰባሰብ አገልግሎቶቹን አጥጋቢ በሚባል ደረጃ ላይ ያደርሳል።

  ✓ የደንበኞች አገልግሎት ማሻሻያ ማእቀፍ በሁሉም አስተዳደራዊና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ይተገብራል፤ በዚህም መረጃን ለህዝብ ግልጽ ከማድረግ ጀምሮ ዜጎች ሲስተናገዱ ክብራቸውን በጠበቀ እና ተገቢ ግልጋሎት የሚያገኙበትን አሰራር ይዘረጋል።

- የማይቆራረጥአካታችየእንቅስቃሴስርአትመርሃግብርበመንደፍይተገብራል። በዚህምከዋናመንገዶችበተዋረድእስከህንጻዎችውስጥእናመፀዳጃክፍሎችድረስለአካልጉዳተኞችየተመቹእንዲሆኑይሠራል።
- የከተሞች የባህል፣ የመገናኛ ብዙሃን እና የማንነት ማበልጸግያ ማእቀፍ፤ ከተሞች ልዩ መገለጫቸውን አጥንተው ለነዋሪዎቻቸውና ለጎብኚዎች የሚያስተዋውቁበትን እንዲሁም በከተማ ፕላኖቻቸው ላይ የሚተገብሩበትን ሂደት ይይዛል።

5.9. ኢንቨስትመንት

እምቅ ሀብት ለመጠቀም በሚያስችሉ መስኮች የኢንቨስትመንት ማበረታቻ እናደርጋለን!

ዓለም ትርፍን መሰረት ባደረጉ ኢንቨስተሮች የምትመራ ቢሆንም፤

ከልባቸው ለኢትዮጵያ ጥቅም ኢንቨስት ለሚያደርጉ በተለየ ሁኔታ ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል!

የውጭም ሆነ የአገር ውስጥ ኢንቬስትመንት ለሀገር ዕድገት ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ስለሆነ ኢዜማ ይህን ለማኘት ኢዜማ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የሚከተሉትን ያደርጋል፡፡

- ለኢንቨስትመንት አመቺ የሆነ የጸጥታ ሁኔታ እንዲኖር ትኩረት ተሰጥቶትይሰራል፣
- ኢትዮጵያውያን መሠረታዊ የፍጆታ እቃ ፍላጎታቸውን በሦስት አመት ውስጥ ማሟላት እንዲችሉ የሚያግዙ የውጭም ሆነ የውስጥ ባለሃብቶችን ኢንቬስትሜንቶችን ያበረታታል፣
- የግብርና ምርት ለሀገር ውስጥ ኢንቬስትምሜንት ግብዓት እንዲሆን በማድረግ ገበሬው የልፋቱን ዋጋ እንዲያገኝ ይደረጋል፣
- በሀገሪቱ ውስጥ የሚደረጉ የኢንቨስትመንት ሥራውዎች ሁሉ ሥራው በሚሰራበት አካባቢ የሚኖር ህዝብ ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል፣
- የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች አቅማቸውን አሳድገው በውጭ ሀገሮችም ኢንቨስት ማድረግ የሚችሉበትን አቅም እንዲገነቡ አስፈላጊው ሁሉ ይደረጋል፡፡
- በኢንቨስትመንት ስም የሚወሰደው ቦታና ገንዘብ ተገቢ በሆነ ቁጥጥር የህዝብን ጥቅም ባስጠበቀ ሁኔታ ተግባርዊ እንዲሆን ቁጥጥር ይደረጋል፣
- በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ከትልቅ ኢንቨስትመንቶች ጋር ተሳስረው እንዲሰሩ ይደረጋል፣
- ለኢንቨስትመንት የሚቀርብ ፋይናንስ መሬትን እንደ ማስያዣያ አድርጎ የሚቀበል የመሬት ፖሊሲን እንከተላለን፣
- ኢንቨስትመንት ኢትዮጵያዊያንን የበለጠ እንዲጋመዱ ማድረግ እንዲችል አተኩሮ ይሰራል፣

- ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ፤ በርካታ የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ (primary market) ን እንዲፈጠር የሚያደርግ የሁለተኛ ደረጃ ገበያን (secondar market) ን እናደራጃለን፣

ክፍል ስድስት

6.1.የማህበራዊመሰረታዊችግሮችመፍቻመንገዶችለቀጣይአምስትዓመት

6.1.1. ትምህርት

የመንግሥት ትምህርት ተቋማት ጥራት ማሳደግ፤ ጥራታቸው ከፍተኛ ከሆኑ ከግል ትምህርት ቤቶች ተቀራራቢ ማድረግ!

ተማሪዎች ለሥርዓት የሚገዙበት ጥብቅ ሥርዓት ማበጀት!

ወላጆች ለትምህርት ጥራት ያላቸውን ጉልዕ ሚና ተረድቶ ማሳተፍ!

በትምህርት ቤቶች የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን ማረጋገጥ

- የትምህርት ዘርፍን አመራርና አደረጃጀት ከመንግሥት ጠልቃገብነት (ከመንግሥት ፖለቲካ አመለካከት) በማላቀቅ ኃላፊነቱንና ተጠያቂነትን ለትምህርት ማህበረሰቡ የሚሰጥ ሥርዓትና ተቋማት መገንባት፤
- የትምህርት ተቋማት አመራሮች (በሹመት ሳይሆን) በብቃት፣ ልምድና የአመራር ብስለት ባላቸው ባለሙያዎች በትምህርት ማህበረሰቡ ተሳትፎ መልካም አስተዳደር እንዲኖር ማስቻል፤ የወላጆች ተሳትፎ ማጎልበት፡፡
- የአንደኛ ደረጃ ማስተማሪያ ቋንቋ በአፍ መፍቻ (በእናት) ቋንቋ ሆኖ በደንብ በተጠናና በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲሰጥ በማድረግ፤ የአማርኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ በሁሉም ትምህርት ቤቶች እንዲሰጡ ማድረግ፤አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋ በሆነባቸው አካባቢዎች ሌሎች አገርኛ ቋንቋዎች ከእንግሊዘኛ ጋር ከ3ኛ ጀምሮ ይሰጣሉ፡፡
- ትምህርት የጀመሩ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ችግሩን ለመቅረፍ የሚረዳ ሥርዓት በተለይም ለሴት ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ በመስጠት፡ የጾት አለመመጣጠን በአጭር ጊዜ እንዲጠፋ ማስቻል፤
- ጥራቱ የወደቀውን ትምህርት ለማሻሻል ግብዓቶችን በማሟላት፤ የተቋማትን አቅም በማበልጸግ የትምህርትን ይዘት (ከሪኩለም) በየደረጃው የሚከልስ ግብረ ኃይል ማቋቋም፤የትምህርት ጥራት የወላጆችን ሚና ከግምት በማስገባት ግብዓቶች ለሚሟለት በሚደረገው ጥረት እገዛ እንዲያደርጉ ማሳተፍ፤
- የሀገር አቀፍ ብሔራዊ ፈተና አሰጣጥን የሚያሻሽልና የትምህርትን ጥራትና አግባብነት ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ማበጀት፤ተቋማትን ማጠናከር፤
- የትምህርት ሥርዓቱ መምህራንን ማዕከል የሚያድረግና ተማሪ ተኮር በማድረግ የዜጎችን ሥራ ፈጠራ፣ተባብሮ መሥራትና የሙያ ሥነ-ምግባር እንዲሰፍን ማስቻል፤ተማሪዎች ሕግና ሥርዓትን ማክበር በተግባር እንዲማሩ ማድረግ፤
- ለግል ትምህርት ተቋማት (ከመዋዕለ ህጻናት እስከ ዩኒቨርሲቲዎች) የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የግል ትምህርት ሥርዓት እንዲስፋፋ ለባህበቶች ሁኔታዎችን አመች ማድረግ፤ከመንግሥት ትምህርት ተቋማት ጋር በጋራ የሚሰሩበት ሁኔታዎች መፍጠር፤
- የልዩ ፍላጎት (ድጋፍ) ትምህርት ፕሮግራሞችና የጎልማሶች የተቀናጀ ትምህርት ዘርፍ በአገሪቱ እንዲስፋፉ ሥርዓት ማበጀት፤ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት በበጎ ፈቃደኞችና በወጣት የብሔራዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፤
- የፈጠራ ችሎታ እንዲስፋፋና ልዩና ከፍተኛ ውጤት ለሚያመጡ ተማሪዎችና መምህራን ምርምርን የሚበረታታ ሥርዓት ማበጀት ሴቶች በዚህ እድል በተሻለ የሚጠቀሙበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤

6.1.2. ጤና

የተቀናጀ የጤና አስተዳደር ጤናማና አምራች ዜጋ ለማፍራት!

መሠረታዊ የእናቶችና ሕፃናት ጤና ሙሉ ለሙሉ በነፃ ይሆናል!

ጥራት ያለው ጤና ለማዳረስ አገር አቀፍ የጤና ሽፋን ኢንሹራንሽ ይዘረጋል!

ከመከላከል በተቀናጀ ሁኔታ የፈውስ ህክምና ተገቢ ትኩረት ይሰጠዋል!

በሁሉም ወረዳዎች ደረጃውን የጠበቀ የሰፖርት ማዘውተሪያ ሰፍራዎች ይደራጃሉ!

በግል ባለሃብቶች የሚደራጁ የህክምና ተቋማትና የሚሰጡት የጤና አገልግሎቶች እና በመንግስት ተቋማት የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች ተመሳሳይ ደረጃ እና ጥራት እንዲኖራቸው ይሰራል!

- የጤናውን ዘርፍ **ማህበራዊ ፍትህን ከማስፈን** አንጻር በማየት ለሁሉም ዜጋ ቤተሰብና ማህበረሰብ ጤናማ የመሆንን መብት ለማረጋገጥ እንዲቻል በማለም **የተቀናጀ የጤና አስተዳደርን** የፖሊሲያችን ዋና ክፍልና አይነተኛ አቅጣጫችን አድርገን እንሰራለን::
- ኢዜማ**በማህበረሰቡ ፤ በመንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች** እና **በግል ባለሀብቶች** መካከል በከፍተኛ ደረጃ የትብበር፣ መደጋገፍ እና በጋራ አቅዶ በጋራ የመተግበር ባህል እንዲዳብር የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል::
- **የአገልግሎቶች** ጥራትና ዘመናዊነትን ለመጠበቅ እንዲቻል የአገልግሎት አሰጣጥ **ደረጃዎች ፣ ደንቦችና መመሪያዎች** በየእርከኑ ይዘጋጃሉ፤ አደረጃጀቶቹ **መንግስታዊ የግል እንዲሁም መንግሰታዊ ያልሆኑ** በማለት የሚዋቀሩ ይሆናሉ::
- የአደረጃጀት እና መዋቅራዊ ለውጦችን የምንተገብር ሲሆን ይህም በዋነኝነት **የማህበረሰብ ጤና አገልግሎትንና የፈውስ ጤና አገልግሎትን** ጥራቱን የጠበቀ ሚዛናዊና ፍትሃዊ የሚያደርግ ይሆናል::
- **ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች** ላይ ተገቢው ትኩረት እንዲሰጥ የሚደረግ ሲሆን **የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር** ላይ ያሉ የብቃትና የተቋማት እንከኖችን በመቅረፍ የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል::
- የጤናውን ዘርፍ አደረጃጀት እና አስተዳደር **ከፖለቲካ ወገንተኝነት** በማጽዳት ሙያዊ ብቻ እንዲሆን የሚደረግ ይሆናል::
- በተለይ **በግል ባለሃብቶች የሚደራጁ** የህክምና ተቋማትና የሚሰጡት የጤና አገልግሎቶች እና **በመንግስት ተቋማት** የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች ተመሳሳይ **ደረጃ እና ጥራት** እንዲኖራቸው ይሰራል፤ ልዩ የሆኑ አስፈላጊ እና አንገብጋቢ ህክምናዎች በግል ተቋማት የሚሰጡ ሆነው **በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ** መሆን የሚችሉበትን መንገድ መንግስት **ድጋፍና እገዛ** በማድረግ በማህበረሰብ መር **የጤና መድህን** አገልግሎቶች እንዲሸፈን በማድረግ ለማህበረሰቡ ያመቻቻል::
- **የጤናው ዘርፍ የሰው ኃይል ልማት ዕቅድ** በማዘጋጀት ባለሙያው ህይወቱን ትርጉም ባለው መልክ መምራት የሚያስችል **ደመወዝና ጥቅማጥቅሞችን** እንዲሁም **ልዩ ልዩ ትምህርቶችን** ማግኘትን በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲሆን ይደረጋል::
- **በመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች** አከፋፋይ መደብሮች ባለሙያዎችን በማህበር በማደራጀት፣ በማቋቋምና የብድር አቅርቦትን በማመቻቸት ሙያዊ፣ ስነምግባራዊና ፍትሃዊ የሆነ በዋጋውም የተመጣጠነ አገልግሎት ለህብረተሰቡ እንዲያዳርሱ የሚያበረታታ ስርዓት ይዘረጋል::
- ሃገር አቀፍ **የሙያ ማረጋገጫ ፈቃድ** ሰጭና የስነምግባር ቦርድ አንዲሁም በየጤና ተቋማት ደረጃ **የህክምናና ስነምግባር ቦርዶች** ይመሰረታሉ፤ የሙያና ስነምግባር ጉድለቶች ማረሚያና መቀጣጫ ሊሆኑ የሚችሉ እርምጃዎችን ሃላፊነት **የጤና ዘርፍ ሙያ ማህበራት** እንዲወስዱ ይደረጋል፤ ከመንግስትም **ድጋፍ እና ክትትል** የሚያገኙ ይሆናል::
- **በጤና ዋስትና መድህን ስርዓትን** በማዋቀር ከኪስ ቀጥተኛ ወጪ የሚሆኑ ክፍያዎችን ለመቀነስ ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል ሆኖም በጤና ዋስትና ያልታቀፉ ዜጎች ከመንግስት ጤና ተቋማት የጤና አገልግሎቶችን ለማግኘት ሲፈልጉ የጤና ተቋማቱን ወጪዎች ለመሸፈን አላማ ያደረገ የአገልግሎት ክፍያ በቀጥታ የሚፈጽሙ ይሆናል::
- በዕውቀት ላይ የተመሰረተ **መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀት፣ አቀማመር** እና **ትርጉም አሰጣጥን** ተግባራዊ የሚያደርግና የመረጃ ስርጭትና አጠቃቀምን በአግባቡ ተደራሽ የሚያደርግ **"የመረጃ አስተዳደር ስርዓት"** በተግባር ላይ ያውላል::

6.1.3. ሰደት

ኢዜማ ኢትዮጵያዊያን በየትም ዓለም ተወዳድረው የሚሰሩ ዜጎች እንዲሆኑ ተገቢው ድጋፍ ያደርጋል!

ኢትዮጵያዊያን ስደትን እንደ ዋና የሕይወት አማራጭ እንዳይመለከቱት የሚያደርግ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሥራዎች!

ኢዜማ በውጭ አገር የሚደረግ የሥራ ሰምሪትን በተገቢው መንገድ እንዲመራ የሚያደርግ ሲሆን፤ ማንኛውም ዜጋ በፖለቲካ አመለካከቱ ከአገር የሚሰደድበት ሁኔታዎች እንዳይኖሩ ይሰራል፡፡ አገራችን አሁን ባለው ሁኔታ በቂ የሥራ እድል መፍጠር በማትችልባው ፤ በውጭ አገራት የሠው ሀይል እጥረት በሚታይባቸው የሥራ መስኮች ተገቢውን የሠው ሀይል በማስልጠን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳድረን ለመስራት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

- ለሥራ ሥምሪት የሚሄዱ ዜጎች ተጨማሪ የውጭ ቋንቋዎች በማወቅ ተገቢው የግንኙነት ክዕሎት እንዲኖራቸው ማድረግ፤
- በአረብ አገራት ለሥራ የሚሄዱ ዜጎች ከቋንቋ በተጨማሪ መሰረታዊ የቤት አያያዝና አስተዳደር፤ የውጭ ምግቦች ዝግጅትና ሌሎች መሰረታዊ ክዕሎቶች እንዲኖራቸው ይደረጋል፤
- ዜጎች በሚኖሩባቸው አገራት ክብራቸው ተጠብቆ እንዲኖሩ፤ ተገቢው ምዝገባና ጥበቃ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
-

6.1.4. ባህል

ኢትዮጵያ የዓለም አንድ ክፍል ብትሆንም፤
ኢትዮጵያዊነት ከህብረ ብሔራዊነት ጋር ያዋሃደ ማንነት ያላት አገር እንደሆነች ለዓለም እናሳያለን!
ትምህርት ቤቶች የበጎ ባህል ማስረጫ እና በልዩነት የመተባበር መሰረት መጣያ ማዕከል ይደረጋሉ!

የኢዜማየባህልፖሊሲዋናዓላማየሀገራችንንነባርናአኩሪባህሎቻችንንእናታሪካዊእሴቶቻችንንበመጠበቅእናከአፍራሽናጎጂልምዶ ችበመከላከልእንዲሁምትውልዱንበሚያንፁእናየነገውንህገርገንቢወጣትአእምሮበሚገነቡባህሎችልማትእናስርፀትላይመስራትነ ው::

የባህልእሴቶቻችንንየመጠበቅእናየመንከባከብ ፤
በክብርሊጠበቁእናወደፊትምሊቀጥሉከሚገባቸውታላላቅየሀገራችንአኩሪባህሎችመካከልኢዜማልዩእንክብካቤማድረግየሚጠበ ቅበትበብሄረሰቦችምሆነበሃይማኖቶችመካከልለረጅምዘመናትየነበረውመቻቻልናመከባበር;
ለእንግዳየሚሰጠውክብርናመስተንግዶ; ግጭትንበሰላማዊመንገድመፍታት; አቅመደካማንምሆነአካልጉዳተኞንመርዳት; በደቦየማልማትእናየመደጋገፍ; በጋራሀገርንየመከላከልእናየመሳሰሉትአኩሪ ባህሎችን የመጠበቅና የመንከባከብ ስራ ይሰራል፡፡ ይህን ዓለም እንዲያውቀው ለማድረግ ይሰራል!

የዳበረባህልእንዲለማየማነልበት፤
እኒህከላይየተጠቀሱትአኩሪባህሎችየሚገባቸውእውቅናእናእንክብካቤእንዲደረግላቸውሆኖአፈፃፀማቸውንበተመለከተዘመኑንበ ሚመጥንመልኩእንዲጎለብቱለማድረግኢዜማከዚህየሚከተሉትንየማልማትተግባራትንይፈፅማል።በማህበራዊሚድያመልካምስ ብዕርንአመላካችመልእክቶችንየመለዋወጥ፤እንደግጭቱስፋትናዓይነትዘመናዊየግጭትማስወገጃስርዓትማነልበት፤
የሃይማኖትአባቶችየጋራየምክክርመድረክመፍጠር፤የፖለቲካፓርቲመሪዎችየጋራጉባዔመፍጠር፤
መልካምባህልንበኢንፎርሜሽንቴክኖሎጂማነልበት፤
አርሶአደሩበዘመናዊአስተራረስየሚረዳበትንመንገድየማነልበትእናየመሳሰሉትተግባራት ይከወናሉ::

ወራሪባህሎችንእናአሉታዊተፅዕኖአቸውንየመከላከል፤ አዜማ የዜጎችን ግላዊ ነፃነት ያከብራል፡፡ የሉላዊነትአላስፈላጊ ተፅዕኖለመከላከልብሎምለመግታት በቂ መረጃ የመስጠት ስራዎችን ይሰራሉ፡፡ ጊዚያዊ ድህነታችንን በመጠቀም የእኛ ያልሆኑ፤ በማህበረሰቡ ተቀባይነት የሌላቸው፤ ድርጊቶች ለማስፋፋት ምቹ ሁኔታ አይፈጠርም፡፡ ኢዜማከዚህበሚከተሉትችግሮችላይትኩረትበመስጠትየመከላከልተግባሩንይፈፅማል፣ያስፈፅማል። የተመሳሳይፆታጋብቻ፤ ፍቺዎች፤ሱሰኝነት፤ ግጭት/ነውጠኝነት፤ ወዘተ ...

ጎጂአስተሳሰቦችንናልምዶችንየማስወገድ፤በተለያየ ጊዜ ያዳበርናቸው፤ባለሀብትንበጥላቻመመልከትእናተገቢድጋፍአለመስጠት፤ የፓርቲእናየመንግስትስራመደበላለቅ፤ምሁሩንበጥርጣሬበማየትበእውቀቱአለመጠቀም፤ የባለስልጣናትበመርህእናስርዓትአለመገዛት፤ፖለቲካንመራቅእናበሀገርጉዳይአለመሳተፍ፤ፅንፈኝነትንመላመድ፤ ኢምክንያታዊመሆን፤ሃይማኖትንናብሄርተኝነትንለፖለቲካጉዳይመጠቀም፤ሙስና፤ሐሰተኛእናየጥላቻወሬንማስፋፋት፤ ሴቶችን ጨምሮ ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችላይ አእምሮአዊምሆነአካላዊጉዳትየሚያደርሱጎጂልምዶችየማስወገድ ሥራ ይሰራል፡፡

ስርፀትእናስትራቴጂው፤

በጋራየጠበቅናቸውንናበስርዓትያነለበትናቸውንምጡቅባህሎቻችንንበህብረተሰባችንዘንድበተለይምበወጣቱእናበታዳጊዎቸዘንድ በሰለጠነመንገድእንዲሰርፁጥረትለማድረግኢዜማ**በመደበኛትምህርትቤቶችበኩል**ራእይያለውትውልድእንዲፈጠርተገቢውየባህ ልካሪኩለምእንዲቀረፅበማድረግ፤

ተማሪዎችበአፍመፍቻቋንቋቸውእንዲማሩእናበየደረጃውእናእንደየእድሜያቸውእያደገየሚሄድየባህልትምህርትስርዓትእንዲቀረ ፅያደርጋል፡፡ከዚህም

ባሻገርማህበረሰቡለዚህግብየበኩሉንአስተዋፅኦእንዲያደርግ**በመገናኛብዙሃንበኩልበእምነትተቋማትበኩልበስፖርት**እናበ**አርትመ ስክ**በተጨማሪምርምሮችእንዲታገዝኢዜማእጅግከፍተኛጥረትያደርጋል፡፡

6.1.5. የስርዓተ-ፆታ

ትምህርት የሥርዓተ ፆታ እኩልነት ማረጋገጫ ወሣኝ መሳሪያ በመሆኑ፤

ሴቶች/ልጃገረዶች የትምህርት ተሳትፎ የሚቀንሰባቸውን ቦታዎች ለይተን ማስተካከያዎች እናደርጋለን!

የሴቶች ተሣትፎ በቁጥር ሳይሆን በወሣኝ መልኩ ለአገር ግንባታ አስፈላጊ መሆኑን በማመን ነው!

- በሁሉም መስኮች የሴቶች ተሳትፎ እንዲረጋገጥ የሚሰራ ሲሆን፤ በመሰረታዊነት የልጃገረዶች የትምህርት ተሳትፎ በመሰረታዊነት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ድጋፍ ይደረግለታል፡፡
- የወንዶችን ተሣትፎ ያረጋገጥ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ የሲቪል ማህበራት በተቀናጀ አግባብ አንዲሰሩ ሥርዓት ይበጃል፡፡
- ለሴቶች በተለየ ነፃ የትምህርት እድሎች ይመቻቻል፡፡ በገጠርም ሆነ በከተማ ያሉወላጆች ልጆቻቸውን ወደትምህርትቤትእንዲልኩማበረታታት፣ ሴቶችን ልጆችን ለይቶ ከትምህርት ቤት ማስቀረት በሕግ የሚጠየቁበት ስርዓት ይበጃል፡፡
- በሁሉምትምህርትደረጃዎችላይሴቶችንበብዛትበመምህርነትእናአመራርስራዎችማካተትላይያተኩራል፡፡
- የሥርዓተፆታ-
  እኩልነትመርሆዎችእናየእኩልነትእናየፍትህመልዕክቶችበአንደኛእናበሁለተኛደረጃትምህርትቤቶችሥርዓተ-ትምህርትውስጥእንዲካተቱያደርጋል፡፡
- ወንዶችና ሴቶች በአንደኛ ደረጃ ጀምሮ የምግብ ዝግጅትና የቤት አያያዝ ትምህርት እንዲያገኙ በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ይካተታል፡፡
- የሴቶች እና ሕፃናት የንፅሕና መጠበቂያዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ለሁሉም እንዲዳረስ ይደረጋል፡፡ በዚህ ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው የሚስተጓጎሉ ልጃገረዶች እንዳይኖሩ ይደረጋል፡፡ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ተገቢው የስነ ተዋልዶ ትምህርት እንዲያገኙ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ይካተታል፡፡
- በሴቶችባለቤትነትየተያዙየንግድተቋማትንየተለየየብድርእናየታክስቅነሳማዕቀፍበጥናትአስደግፎተግባራዊያደርጋል፡፡
- የሴቶችን የወሲብ ጥቃት ለመቀነስ እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ተቋማትን የማጠናከር ሥራዎች ይሰራሉ፤ ጥቃት ፈፃሚዎች ላይ የሚወሰዱ ሕጋዊ እርምጃዎች አስተማሪ በሚሆን መልኩ ለሕዝብ የሚገለፁ ይሆናሉ፡፡
- ገለልተኛየሴቶችየመብትቡድኖችለሴትነትእንቅስቃሴዎች እንዲስፋፉያበረታታል፤ ከፖለቲካ ፓርቲ ገለልተኛ በመሆን በነፃነት በመደራጀት መብት ጋር በተጣጣመ መልኩ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

6.1.6. የወጣቶች

በቂ መረጃ ያለው፤ በመረጃ ላይ ተመስርቶ እንዲወስን ማስቻል!

የብሔራዊ አገልግሎቶች ኢትዮጵያዊ ሕብርን በሚያሳይ መልኩ መተግበር!

በገጠር የሚገኘውን ወጣት ሀይል አማራጭ የሥራ ሰምሪት የሚፈጥር ሥርዓት ይበጃል!

ወጣቶች የአገራችን ኢትዮጵያ ማዕከል እንደመሆናቸው በአገር አቀፍ ደረጃ የመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ዘርፎች ትርጉም ባለው መልኩ ሊሳተፉ ይገባል። እነዚህን ምክንያቶች ማዕከል በማድረግ ኢዜማ ለወጣቶች በዚህ የቃልኪዳን ሰነድ ወጣቱ ኃላፊነት በተሞላበት መንፈስ የአገር አንድነት እና ሉዓላዊነትን እንዲያስከበር፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እንዲያሰፍን ከዚያም ባሻገር ከራሱ አልፎ ለሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች መብት መከበር እንዲቆም ፣ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነቱን አረጋግጦ ዕድገትን እንዲያፋጥን ፣ ማህበራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት መሪውን ድርሻ እንዲወስድ ታቅዶ የተቃኘ ነው።

- በቴክኖሎጅ የታገዘ ፣ ለሥራው ዓለም አስፈላጊ የሆኑ ክህሎቶችን ለወጣቶች የሚያስጨብጥ የትምህርት ሥርዓትን መዘርጋት እና ተደራሽ ማድረግ፤
- የወጣቶች ለልዩ ልዩ አላስፈላጊ ድርጊቶች ተጋላጭነት የሚቀንሱ ተግባራትን ለምሣሌ በሁሉም አካባቢዎች በቂ የስፖርት ማዘወተሪያ ሥፍራዎች ይዘጋጃሉ፤ ተጋላጭ የሆኑ ወጣቶች ወደ መደበኛ ሕይወት እንዲመለሱ ድጋፍ ይደረጋል::
- የግል ዘርፉን በስፋት በማሳተፍ ጥራት እና ተደራሽነት ባለው መልኩ ወጣቶች የስፖርት፣ መዝናኛ እና የባህል እንቅስቃሴዎች ተጠቃሚ ማድረግ
- የወጣቶችን የአገር ፍቅር ስሜት እና የበጎ- አድራጎት አገልግሎት ለማሳደግ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ብሔራዊ አገልግሎትን በአገር አቀፍ ደረጃ ማስጀመር እንዲሁም የተቀናጀ ብሔራዊ የበጎ-ፍቃደኞች የመረጃ ቋት እንዲቋቋም ማድረግ፤
- የገንዘብ አቅርቦትን በማረጋገጥ፣ የመሰረተ-ልማት ማነቆዎችን በመፍታት፣ የብድር ሥርዓቱን በማዘመን እንዲሁም የሕግ-ማዕቀፎችን በማሻሻል ወጣቱ በአዳዲስ የፈጠራ ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል፤
- ወጣቱ መረጃ እንዲኖረው፤ ቴክኖሎጂን ተደራሽ በማድረግ፣ የበይነ-መረብ ጥራት እና ደህንነትን በማረጋገጥ፣ የማሕበራዊ ሚዲያ አጠቃቀምን በማዘመን ሰርነቀል ማሻሻያ ይደረጋል:: ወጣቱ መረጃን መሰረት አድርጎ ነሮዉን ያሻሽልበታል::
- በገጠር በአርሶ አደርና አርብቶ አደር አካባቢ ያሉ ወጣቶች አማራጭ የሥራ መስክ የሚያስገኙ እድሎች በመፍጠር፤ የግብርናውን ምርታማነት የሚጨምሩ ሥራዎች ይስራሉ::

6.1.7. አካልጉዳተኝነት

አካል ጉዳተኞች በተለየ ሁኔታ ይችላሉ ብለን እናምናለን!

አካል ጉዳተኞች ተረጂዎች ሳይሆኑ፤ ለአገር ግንባታ የሚሰጡት እሴት እንዳላቸው እናምናለን!

ኢዜማ አካል ጉደተኞች በተረጅነት ሳይሆን ለአገር ካላቸው ጠቀሜታ አንፃር ተገቢውን ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያስችል ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል:: የአካል ጉዳተኞች በተለየ የሚችሉ እንጂ የማይችሉ አደርጎ መመልከትን ህሣቤ ከመሰረቱ ለመቀየር እንሰራለን::

በዚህም በቀጣይ ዓመታት ለአካል ጉዳተኞች ለመከወን ቃል ከምንገባቸው መሀከል ቀዳሚዎቹ፡-

- ብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ጠንካራ ሆነው እንዲመሰረቱ፤ ያሉትም እንዲጠናከሩ እናደርጋለን::

- አግላይ የሆኑ ህጎችን በማስወገድ እንዲሁም ህጎችና ደንቦች የአካል ጉዳተኞችን መብትና ግዴታን እንዲያካትቱ እንዲሁም የአካል ጉዳተኞችን የሲቪልና የፖለቲካ ተሳትፎን በማላቅ እንዲሰሩ እናደርጋለን፡፡
- በትምህርት መስክ አካል ጉዳተኞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እናደርጋለን፤ በዚህም የልዩ ፍላጎት ትምህርት በስፋት እና በጥራት እንዲሰራ እናደርጋለን፡፡
- ምቹ ስራ ቦታ ለአካል ጉዳተኞች እና አገልግሎት ቅድሚያ የማግኘት መብት ሆነው ይወጣሉ፡፡ መንግስት በሁሉም መስክ የእኩል እድል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር፤ በኮንስትራክሽን ስራዎች፣ በመገናኛና በመረጃ ስራዎች፣ በመንገድ ስራዎች፣ በህዝብ መገልገያዎች ህግና መመሪያዎችን በማዘጋጀት የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነት እናረጋግጣለን፡፡
- የማህበራዊ አገልግሎቶች ማለትም የማህበራዊ ዋስትና፣ የህክምና፣ የትምህርት፣ የመሰረታዊ ፍጆታዎች አቅርቦት በመጠንም ሆነ በጥራት ለአካል ጉዳተኞች መቅረባቸውንና ፍትሀዊ ክፍፍል መደረጉን እናረጋግጣለን፡፡
- በአገራቀፍ ደረጃ የተለያዩ የልዩ ፍላጎት አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን በጥራት እና በተደራሽነታቸው የላቁ አድርገን እንገነባለን፡፡ በዚህም አካል ጉዳተኞች ከቴክኖሎጂ ጋር እንዲተዋወቁ፣ በፈጠራ ስራ ቀዳሚ እንዲሆኑ እና የመሰረታዊ ፍላጎት አቅርቦት ተሟልቶላቸው እንዲማሩ እና እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡
- አካል ጉዳተኞች ላይ የሚሰሩ ሰፋፊ መርሀ ግብሮችን እናስጀምራን፤ እነዚህም እኩል ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ፣ ተቋማዊ ድጋፍ እና እንክብካቤ እንዲሁም የተሳትፎ ማላቅ እና የበሁሉም መዋቅር የማካተት መርሀግብሮች ናቸው፡፡
- ትምህርትና ስልጠና በመስጠት የአካል ጉዳት መከሰቻ የሆኑ ምንጮችን በመቀነስ እንዲደርቁ እንሰራለን፤
- የመንግስት እና የግሉን ዘርፍ በማስተባበርና የባህላዊ መንገዶችን በመገልገል ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የማህበራዊ ከለላ ስራዎችን እንሰራለን፡፡
- የአካል ድጋፍ ሰጪ ቁሳቁሶችንና የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ ስርአትን መዘርጋት ላይ በስፋት እንሰራለን፡፡

6.1.8. በማህበራዊከለላ

ስንፍናን የሚጠየፍ ጠንካራ ትውልድ ለመስራት ኤዜማ ይሰራል!

ለማህበራዊ ቀውስ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን ከለላ እንዲያገኙ ያደርጋል!

ደጋፊ የሌላቸው አረጋዊያን በማዕከል እንክብካቤ ይደረግላቸዋል!

ማኅበራዊ ከለላ ስንል የፖሊሲዎች እና የመርሀግብሮች ጥቅል የሆነ በቁጥር ላቅ ያለውን ማህበረሰብ ከድህነት እና ከተጋላጭነት የማውጣት ውጥን ነው፤ ይህንንም ለማድረግ በፖሊሲዎች እና መርሀግብሮች ጥምረት ህዝብን ከአደጋ ተጋላጭነት መቀነስ፣ እራሳቸውን የሚከላከሉበትን የስራ ገበያ በማመቻቸት አቅማቸውን ማሳደግ እና በቂ ገቢ እንዲያገኙ ማስቻል እና መሰረታዊ የማህበራዊ አገልግሎትን ማድረስ ነው፡፡

በዚህ መሰረት በማኅበራዊ ከለላ ረገድ የሚከተሉትን ለመከወን ቃል እንገነባለን፡፡

- የተቀናጀ የማህራዊ ከለላን ወደ ህብረተሰቡ ለማድረስ በአገራቀፍ ደረጃ የሚመራ ተቋምን አዋቅሮ መዋቅሩን እስከ ወረዳ ድረስ እንዲዘረጋ እናደርጋለን
- የማህበራዊ ከለላ አገልግሎት መሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች አካል እንዲሆን በማድረግ በተቋማት እና በመላው ህዝብ ዘንድ እንዲታወቅ እናደርጋለን፡፡ በሕፃናት መለመን በህግ ይከለከላል፡፡ ህፃናቱ ተገቢው እንክብካቤ ወደሚያገኙበት ማዕከል ይገባሉ፡፡ በተመሳሳይ ደጋፊ የሌላቸው አረጋዊያን መጦሪያ ማዕከል ይኖራቸዋል፡፡
- ዜጎች ለተለያዩ ችግሮች እንዳይጋለጡ ለመከላከል ዘርፈ ብዙ የማህበራዊ ዋስትና ስርዓትን የመዘርጋት፣ የዜጎችን ሰርቶ የማግኘትና ጥሪት የመያዝ አቅምን ማጎልበት፣ ለጥቃትና በደል ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የህግ ጥበቃና ድጋፍ እንዲያገኙ እናደርጋለን፡፡
- የማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎችን የማህበረሰብ ተቋማት እንዲመሯቸው እናደርጋለን፡፡

- ማህበራዊ ከለላ ለድህነት ቅነሳ እና ለፍትሀዊ እድገት ወሳኝ ሚና ስለሚጫወት በድህነት ለሚማቅቁ ለመኖር በቂ የሆነው ዝቅተኛው አቅርቦት እንዲደርሳቸው በማድረግ ከለላ በመስጠት ስራ እንሰራለን፡፡
- አደጋዎች እየጨመሩ ሲመጡ ህበረተሰቡ ከማይወጣው ማጥ እንዳይገባ አቅርቦትን በማመቻቸት አስቀድሞ በመከላከል ላይ አተኩረን እንሰራለን
- የተጋለጡ እና የተገለሉ ማኅበረሰቦችን ምርታማነትን በማሳደግ እና ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙባቸውን አማራጮች የማሳደግ ስራ ላይ ትኩረት እንሰጣለን፡፡
- ከድህነት ወለል በታች ለሚገኙ ወገኖች መሰረታዊ ሽቀጦችን እና አገልግሎቶች ማድረስ ላይ እንዲሁም ተግባራዊ ጥበቃ (Proactive security) በማድረግ ብቃትን እና ዕድልን ማሳደግ ትኩረታችን ይሆናል፡፡
- የዜጎችንየሰብዓዊመብትመከበርላይትኩረትሰጥቶየምግብእናየገንዘብድጋፍንለሚገባውሰው ብቻ በማድረስ እንሰራለን፡፡ ይህም ምቹየአየርንብረት፣ንጹህአከባቢእናመራቆትንየሚያስቀርመርህግብርእንዲሆንአድርጎ ከመቅረጽእናመከታተል ጋር ይከወናል፡፡
- ህብረተሰብንማስተማር፣ግንዛቤማሳቅእናመልካምተሞክሮዎችንበሁሉምስፍራማስተዋወቅ በተቀናጀ መልኩ ይከወናል፡፡
- የቴክኒክእናሙያእንዲሁምየሳይንስእናቴክኖሎጂስልጠናዎችን እና የግብርናእናየአነስተኛንግድስራዎችንከማህበራዊከለላየመውጫመንገድእንዲሆኑማድረግ ላይ እንሰራለን፡፡

ክፍል ሰባት

7.1. የውጭግንኙነት መሰረታዊ ችግሮች

እኛ ኢትዮጵያዊያን ከዓለም የምንወስደው የምንሰጠውም እንዳለ እንረዳለን፡፡ ኢትዮጵያ በዓለም ሶስተኛ ደረጃ የዲፕሎማቲክ ከተማ ያለባት አገር ነች፡፡ ከአፍሪካ አገሮች ከፍተኛ የዲፕሎማቲክ ስምሪትም የምታደርግ አገር ነች፡፡ ይህ ሁሉ የውጭ ግንኙነት ተግባር የሚከወንበት አገር ብትሆንም፤ በዚሁ መጠን ከውጭ ግንኙነት ለዜጎች ይህ ነው የሚባል ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የቻለች አገር አይደለችም፡፡

የምዕራብ አገራት ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸው ግንኙነት በንግድ፣ በኢንቨስትምት ይሁን በደህንነት ጉዳዮች የሚል ቢሆንም ዋናው ጉዳይ ግን ሽብርተኝነትን የመከላከል ትብብር አካል እያደረጉት አንዳንዶች እንደሚሉት እኛ ኢትዮጵያዊያን የውጭ ሀይሎች “ተላላኪ” እና ጥቅም አስጠባቂ ተደርገን እየተፈረጅን ነው፡፡ ሽብርተኝነትን መከላከል የሁሉም ሠላም ወዳድ አገራት ግዴታ ቢሆንም ከሌሎቹ ግንኙነት ጋር ተቆራኝቶ መቅረቡ፤ አገራችን የሌሎች አገራትን ውኂያ በግንባር የምትጋፈጥበት ሁኔታ መፍጠሩ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ ገዢው መንግሥት የውስጥ ዴሞክራሲን ማስፋት ያለመቻሉን መሸፈኛ፤ በሽብር መከላከል ሥም የውጭ ድጋፍ ማግኛ ማድረጉ ተገቢ ስትራቴጂ እንዳልሆነ ኢዜማ ያምናል፡፡ የዜጎች ሕይወት እየገበሩ የሌሎችን ፍላጎት ለማሟላት መንቀሳቀስ ተገቢ አይደለም፡፡

እነኚህ የምዕራብ አገራት አገራችን በሽብር መከላከል ግንባር ቀደም ተሳታፊ እንድትሆን የመፈለጋቸውን ያህል፤ ተፈጥሯዊ የሆነውን የተፈጥሮ ሀብታችንን ለመጠቀም በምናደርገው እንቅስቃሴ፤ ለብቻቻው ጥቅም ማጋበስ ከሚፈልጉ የጎረቤት አገሮች ጋር በሚኖረን ግንኙነት አዎንታዊ ሚና ለመጫወት ዳተኞች ይሆናሉ፡፡ ቢችሉ በእጅ ጥምዘዛ የሌሎችን ጥቅም ሊያስጠብቁ እንደሚችሉ ምልክቶች ይታያሉ፡፡ ከጎረቤት አገሮች ጋር ያለን ግንኙነት፤ በበዙ መልኩ በደንብ መፈተሽ እንዳለበት የሚታመን ነው፡፡ ለመቶ ዓመታት የዘለቁ የድንበር ማካለል ጉዳዮች መፍትሔ ሊሰጣቸው እና ወደ የጋራ ልማትና ትብብር ልንገባ የምንችልበት አቅጣጫ እየተከተልን አይደለም፡፡

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በግልፅ የተቀመጠ ፖሊሲ ያልነበረ ቢሆንም በተለያየ ጊዜ የሚወጡ ፅሁፎችና መግለጫዎች የሚያሳዩት ነገር ቢኖር በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ትኩረት የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ/ዶላር እንዲሰጡ ብቻ ነው፡፡ በተቀናጀ ሁኔታ በአገራቸው ፖለቲካ፣ ኤኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ጉልፅ ሚና እንዲጫወቱ የሚያደርግ አሰራር የተዘረጋበት ሁኔታ የለም፡፡ በዓለም ዙሪያ በሚሊዮን የሚቆጠሩ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በሚገኙበት ሁኔታ፤ አውነት ይዘን በሀሰት ፕሮፓጋንዳ በተፃራሪ የቆሙ ሀይሎች ብልጫ ሲወሰዱብን እንመለከታለን፡፡ ኤኮኖሚያዊ ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉበትን ብዙ መስኮች መጠቀም ያለመቻላችን ብዙ ማሳያ ቢሆንም አንድ በውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ በዓመት ሁለት ቱሪስት ወደ አገር ቤት መላክ ቢችል በብዝ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ቱሪስቶች መምጣት ምን ያህል ኤኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ መንግሥት ሲከተለው በነበረው የብሔር ፖለቲካ መነሻ በሰው አገር በማንነት ተቧድኖ የሀይማኖት ተቋማትን ጭምር ለመከፋፈል ደርሰናል፤ ማህበራዊ ግንኙነታችንንም በዚያው ልክ በጥርጣሪ እንዲሞላ በማድረግ በጋራ እንዳንቆም ደንቃራ ሆኖብናል፡፡

የአገራችን የዲፕሎማቲክ ምደባ ለአገር ከሚሰጡት ጥቅም አንፃር ሳይሆን፤ በዋነኝነት ለግለሰቦች ተጠቃሚነት ሲሆን ሌላኛው ግለሰቦችን ከአገር ውስጥ ፖለቲካ የማራቅ ስምሪት ነው፡፡ ይህ በፍፁም ተቀባይነት የሌለው አሰራር አሁን “ለውጥ” በሚባለው ጊዜም ተጠናክሮ መቀጠሉ እጅግ አሳሳቢ እንደሆነ ልንረዳ ይገባል፡፡

በውጭ ግንኙነት ያሉብን መሰረታዊ ችግሮች ሲጠቃለሉ፤

- የውስጥ ችግሮቻችንን በዴሞክራሲያዊ አግባብ የመፍታት ባዕል ያለማዳበር፡፡ ችግሮቻችንን በውጭ ሀይሎች የዴፕሎማሲ ጫና ለመፍታት ሲከፋም የውጭ ሀይሎችና የጎረቤት አገራት በውስጥ ጉዳያችን ገብተው የአገራቸውን ጥቅም የሚያስጠብቁበት ምቹ ሁኔታዎችን ለሌች መፍጠራችን፤
- ሀገራችን ያላትን የተፈጥሮ ሀብት ሚዛን በጠበቀ ሁኔታ መጠቀም እንዳለባት እና ዜጎች ይህ ባለመደረጉ የሚኖሩበትን የደህነት ደረጃ በሚገባ ተርድቶ በጋራ አብሮ ያለመቆመ፤ ሜጋ ፕሮጀክቶችን ለፖለቲካ ፍጆታ መጠቀምና የህዝብን የተሟላ ተሳትፎ እና ባለቤትነት ያለማረጋገጥ፤

- በሚሊዮን የሚቆጠሩ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ለአገራቸው ሊያበረክቱ የሚችለውን በጎ ተጽዕኖ በሚገባ ያለመጠቀም፡፡ በተቃራኒው ቀላል የማይባሉት በዝምታ፤ ጥቂቶች ደግሞ ፅንፈ በረገጠ የገዢ ፓርቲ ጥላቻ በመገፋት የአገር ጥቅም አደጋ ላይ እስከ መጣል ጥግ መሄድ፤/ዳውን ዳውን ..../
- ከጎረቤት አገሮች ጋር ያለን ግንኙነት በአስተማማኝ መልኩ በኤኮኖሚና ማህበራዊ ግንኙነቶች እንዲተሳሰር ባለመደረጉ፤ በተለይ ደግሞ ቁርጥ ውሣኔ ያላገኙ የድንበር ማካለል ሥራዎች ከፍተኛ የፀጥታ ሥጋት እየፈጠሩ መሆኑ፤
- ከምዕራብ አገራት ያላን ግንኙነት በአመዛኙ የፀረ ሽብር በመከላከል ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ካላት መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ እና በአፍሪካ ቀንድ ሊኖራት በሚገባው ተፅዕኖ ፈጣሪነት ደረጃ ያለመሆኑ፤ ይህን በመንግስትም የሁለትዮሽ ግንኙነት፣ በኤምባሲና ቆንስላ ፅ/ቤቶችም ሆነ በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ተገቢውን መረጃ ለዓለም በማድረስ በኩል ችግር ያለብን መሆኑን፤

7.2. የመፍትሔ አቅጣጫዎች

ኢዜማ የኢትዮጵያ መሰረታዊ የደህንነትና የጥቅም አደጋዎች የሚመነጩት ከውጭ ይልቅ በውስጥ በተሸከምናቸው በሁሉም ዘርፎች ከሚታዩ ችግሮቿ ጋር የተሳሰሩ መሆናቸውን የተረዳ፣ እነዚህ ችግሮች በአለም አቀፍ መድረክ መጫወት ይገባን የነበረውን ትልቅ ሚና ያቀጨጩት መሆኑን የተገነዘበ፣ እነዚህን ችግሮቻችን በማባባስ ትልቅ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችሉ የጎረቤት ሃገሮች እንዳሉን የሚያውቅ፣ ከምንም በላይ ቅድሚያ ለኢትዮጵያ እና ለዜጎቿ ጥቅሞች የሰጠ፣ ኢትዮጵያ በፖለቲካ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ዘርፎች ለገጠሟት ውስብስብ ችግሮችና ለምትገኝበት አሳሳቢ ሁኔታ መፍትሄ በመስጠት እገዛ ማድረግ የሚችልና በሂደትም ሃገሪቱ በአካባቢዋ ይሁን በአፍሪካ ከዛም አልፎ በአለም መድረኮች ተደማጭነት የሚያሰጣት፣ በሂደትም ከፍተኛ የእድገትና የስልጣኔ ማማ ላይ እንድትቀመጥ የሚረዳ መሆን አለበት ብሎ ያምናል፡፡

ይህንንም ለማድረግ ኢዜማ የፕሮፌሽናል ዲፕሎማት ማስልጠኛ ተቋም ይመሰረታል፡፡ ከዚህ ተቋም የሚወጡ ዲፕሎማታቸው ስለ አገራቸው እና በአጠቃላይ ስለ ዓለም ሁኔታ በቂ እውቀት እንዲኖራቸው እና በእውቀት ላይ ተመሰርተው የአገራቸውን ጥቅም በሚያስጠብቅ ደረጃ እንዲያገለግሉ ይደረጋል፡፡ ይህ ተቋም በምልመላ ወቅት ፍላጎት ያላቸው ሁሉም ኢትዮጵያዊያን የሚሳተፉበት እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በተለይ ድጋፍ ለሚሹ አካባቢዎች ጥራትን ሳያጎድል አዎንታዊ ድጋፎች በማድረግ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ የዶታ ተሳትፎም እንዲሁ ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኝ በማድረግ እውቀትን መሰረት ያደረገ የውጭ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

7.3. በአጠቃላይ

- በከፍተኛጥንቃቄና ጥናት ላይ በመመስረት ሃገራችን ጥቅሟንና ደህንነቷን የበለጠ ማስከበር ያስችላሉ ብላ ከምታምናቸው የአለም ሃገራት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ትመሰርታለች፣ በተመሳሳይም መሰረታዊ ጥቅሟን ሊጻረሩ የሚችሉትን በጥናት በመለየት ራሷን በሁሉምመልኩ ለመከላከል የሚያስችል ዝግጅት ታደርጋለች፣
- ለሰው ልጆች ሰላም፣ መብት መከበር፣ ብልጽግና፣ የአካባቢ ጥበቃና ሌሎችንም በጎ አስተዋፅኦ ለአለማችን ከሚያበረክቱ ተቋማትና ድርጅቶች ጋር በቅርበት ትሰራለች፣ ተልእኳቸውም እንዲሳካ የምትችለውን ድጋፍ ታደረጋለች፣
- መንግስታት በስምምነትያጸደቋቸው አለም አቀፍ ህጎችና ስምምነቶች በሁሉም ሃገራት እንዲፈጸሙ፣ የሃገራችን ሉዓላዊነት እንዳይገሰስ፣ ደካማው በጠንካራው እንዳይጠቃ፣ የተባበሩት መንግስታት ፍትሃዊ የውሳኔ መስጫ አግባብ እንዲኖረውና እንዲጠናከር፣ የአፍሪካ ሕብረት ድርጅት በሁሉም መስኩ ጎልብቶ ዋንኛው የአፍሪካ ችግር ፈቺ ወሳኝ ሃይል ሆኖ እንዲወጣ የሚያደርግን እንቅስቃሴ በሙሉ ትደግፋለች፣
- ማንኛውንም ሃገራችን የፈረመቻቸውን አለምቀፍ ድንጋጌዎችና ህጎች ታከብራለች፣ ጥቅሟን ለማስከበር የምትወስዳቸው ማናቸውም እርምጃዎች በእነዚህ ህጎችና ድንጋጌዎች ማእቀፍ ውስጥ እየተፈጸሙ መሆኑን እያረጋገጠች ተግባራዊ ታደርጋለች፣
- የአለምን ሰላምና ደህንነት የሰው ልጆችን ነጻነት ለመግፈፍ በአለም ላይ ሽብርና ሁካታ ለመፍጠር የሚፈልጉ ሃይሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አለም አቀፍ ማህበረሰቡ በጋራ የሚያደርገውን ጥረት በተቻላት አቅም ትደግፋለች፣
- ሀገራችን ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች እና መንግስታት ጋር የምታደርገው ግንኙነት የራሷን ደህንነትና ጥቅም ለማስቀደም ቅድሚያ እየሰጠች በረጅም ጊዜ በጋራ ጥቅም፣ በእኩልነት፣ በመከባበር እና በእርስ በርስ የውስጥ ጉዳዮች ጣልቃ ባለመግባት መርሆች ላይ የተመሰረተ ይሆናል፤

7.4. ጎረቤት ሃገሮችን በተመለከተ

- ኢዜማ ከጎረቤት አጋራት ጋር የሚኖረን ግንኙነት በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን፣ ከጥርጣሬና ካአላስፈላጊ ውድድር ነፃ ሆኖ በጋራ መልማትና የቀጠናውን ሰላምን ማረጋገጥ ላይ ያተኮረ እንዲሆን ይሰራል፡፡
- የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያችን በአካባቢያችን እየተደቀኑብን ያሉትን ስጋቶች በሚገባ የተገነዘበ፤ ከዚሁ አንጻርም የአገራችንን የረጅም ጊዜ ጥቅምን በሚገባ ለማስጠበቅ የሚያስችል ይሆናል፡፡
- ከዓለም አቀፍ ሕግጋትና ከታሪክ አንጻር አገራችን ራስዋ ባለቤት ሆና የምታስተዳድረው (sovereign ownership) የባህር በር እና መተላለፍያ (ኮሪዶር) የማግኘት መብት ሊኖረን እንደሚገባ ኢዜማ ያምናል፡፡ ከአካባብያችን እና ከሃገራችን ልዩ ሁኔታ አንጻር ሲታይ ደግሞ ይህን መብት የማስከበር ጉዳይ የኢኮኖሚ እድገት ብቻ ሳይሆን የሃገር ደህንነት እና የሃገር ህልውና ጉዳይ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ይህን በሥላማዊ፣ ህጋዊና እናዲፕሎማሲያዊ መስመር ብቻ ተግባራዊ ለማድረግ ይሰራል፡፡
- ኢዜማ ሀገራችን ያሏትን የተፈጥሮ ሀብቶችን በተለይ ደግሞ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችን የመጠቀም ተፈጥሯዊ መብት እንዳላት ያምናል፤ ይህንንም ከአገሮች ጋር በስምምነት ለመፈፀም እና የትብብር እንጂ የግጭት መንስዔ እንዳይሆኑ አበክሮ ይሰራል፡፡
- ከጎረቤት ሃገራት ጋር የሚደረግ ግንኙነት የሚመራው ከሌሎች ሃገሮች ጋር በሚደረጉ መሰረታዊ መርሆዎች ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ ግን የጎረቤት ሃገሮች በራሳቸውም ይሁን የሌሎች ሃይሎች መሳሪያ በመሆን በሃገራችን ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ አሳዳሪ መሆን ስለሚችሉ በሚገባ የታሰበበት በጥናትና ምርምር ላይ የተደገፈ በጥንቃቄ የሚያዝ የተናጠል ፕሮግራም ይቀረጻል፣
- ከጎረቤት ሃገሮች ጋር የሚኖር ግንኙነት የየሃገራቱን ማንነትና ምንነት በሚገባ ያጠና፣ በቀላሉ ለጋራ ጥቅም መቆም የሚችሉትን፣ ለጋራ ጥቅም በጋራ ለመስራት የተለያዩ ችግሮች ያለባቸውን ሃገራት በመለየት ለእያንዳዳቸው የሚሆን የተናጠል ስትራተጂ ተግባራዊ ይደርጋል፤
- ኢዜማ በአካባቢው መልካም ጉርብትናን በመፍጠርና በማቀራረብ በሁሉም ሃገራት የነበሩ የፖለቲካ ስርአቶች የፈጠሩትን የቁርሾ፣ የመጠራጠር ስሜት በማጥፋት፣ ለመልካም ጉርብትናው ዋስትና መሆን የሚችሉ የፖለቲካ የማህበራዊና የኢኮኖሚ እሴቶች የሚጋሩ በነዚህ እሴቶች ዙሪያ ሃገሮቻቸውንና ህዝቦቻቸውን በሁሉም መንገድ የሚያስተሳሰሩ፣ ከጋራ ኢኮኖሚ ግንባታ እስከ ጋር መከላካያ ለማቆም የሚዘልቅ የጋራ ጥቅም ማስከበሪያ ስትራተጂ ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

7.5. በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን

- በተለምዶ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ተብሎ የሚጠራው፣ ከኢትዮጵያ ውጭ በሌላው አለም ተበትኖ የሚኖረው በአንድ ወቅት ምንጩ ኢትዮጵያ የሆነው ሁሉ በዚህ ፕሮግራም ትውለደ ኢትዮጵያ ተብሎ የሚጠራው ነው። ከሃገሩ የወጣበት ምክንያት የፈለገው ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌላም ይሁን፣ በፈለገው የተለያዩ ማህበረሰቦች፣ ቋንቋን ሃይማኖትን የሙያ ዘርፍ፤ ወዘተ ለይቶ በተከፋፋፈለ ሁኔታ በወጭ ሃገራት እየተሰባሰብ ወይም ተበትኖ ይኑር፣ በአንድ ወቅት ምንጩ ኢትዮጵያ እስከሆነ ድረስየአገራችንን ችግር ለማቃለልና ወደ ተሻላ ሁኔታ ላይ ለማድረስ በሚደረገው ጥረት ሁለንተናዊ ተሳትፎ ለማድረግ ትልቅ ሀይል ነው ብሎ ኢዜማ ያምናል።

- የፖለቲካ ፍልስፍናውን ማህበራዊ ፍትህ አድርጎ የሚንቀሳቀስ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ፤ የፓርቲውን ፕሮግራም በሚገባ ለማስፈጸም ዝግጁ የሆነ ፓርቲ በአገር ውስጥ ከተፈጠረ፤ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ትልቅ ድጋፍ ሊሰጥ የሚችሉ በመሆናቸው ተገቢው ትኩረት ሊሰጣቸው እና ግልፅ ፖሊሲ ሊወጣላቸው እንደሚገባ ያምናል። ኢዜማ፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊያንን የሚመለከት ግልፅ ፖሊሲ ሊኖረው የግድ የሚያደርገው በውጭ ያሉት አባላቱና ደጋፊዎቹ የሚመኙትን፤ ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊና የበለጸገች ሃገር ለማድረግ በብዙ ዘርፎች ወሳኝ ሚና መጫወት እንደሚችሉ ሰለሚያውቅ ነው።

- ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በአብዛኛው እንደሚታሰበው ተንደላቀው እና በምቾት የሚኖሩ አድርጎ መሳል ሰህተት ነው፡፡ እጅግ ብዙ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በአስከፊ ሁኔታ በሰው አገር እንደሚኖሩ ይታወቃል፡፡ አብዛኞቹ የሚኖሩት

ዴሞክራሲ በዳበረባቸው ሃገሮች ነው። በነዚህ ሃገሮች በመኖር ብቻ ሰብአዊ መብት፣ የሚድያና የግለሰቦች ነጻነት፣ የህግ የበላይነትና የፍትህ ሚዛናዊነትን ለመረዳት፣ በዚህ መንገድ በሰለጠነ ሁኔታ፣ የተረጋጋና የበለጸገ ሃገር ፈጥረው በሚኖሩ ሕዝቦች እንዲቀኑ ተደርጓል። "ምነው ኢትዮጵያም እንዲህ የሞላላት ሃገር ብትሆን" ብሎ የማይቀና ትውልደ ኢትዮጵያዊአይኖርም። ይህ ማለት የተሳትፎው ጉዳይ ቢለያያም በውጭ የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ሃገራችን ነጻነት፣ ፍትህ፣ ዴሞክራሲ የሰፈነበት ሃገር እንድትሆን እስካሁን ያደረጉት ትግልና የከፈሉት መስዋእትነት ወደፊትም የሚኖራቸው አስተዋጸኦ ቀላል አይሆንም።

- ሰለዚህ በሚኖሩበት አገራት ያካበቱትን ልምድ፣ እውቀትና ሀብት ከአገራቸው ጋር እንዲያስተሳስሩ፣ ድጋፋችን ለሚሹ በችግር ላይ ላሉትም ተስፋ የሚሰጥና የሚደግፍ፤ ሁሉን አቀፍ የሆነ ምቹ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚ እና ማህበራዊ ተሳትፎ ሊያደርጉ የሚችሉበት ፖሊሲ ኢዜማ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ክፍል ስምንት

8.1. የቃልኪዳንሠነድመተግበሪያሥልቶች

8.1.1. ስትራቴጂ

ይህ የቃል ኪዳን ሠነድ የሚተገበረው፤ አሁን አገራችን የገባችበትን ከፍተኛ

- የሕዝብ አገልጋይ ለመሆን የተቀጠሩ ሠራተኞች በሙሉ ጊዚያቸውና እውቀታቸው የተመደቡበት የህዝብ ሥራ ብቻ እንዲሰሩ ማድረግ፤
- በአቅም ማነስና እንዝላልነት የሚባክኑ ጊዜዎችና ሀብቶች በአግባቡ ሥራ ላይ የሚውሉበት አስራር በመዘርጋት፤
- የፖለቲካ አመራሮች በሚሰጧቸው አመራሮች ምስጋና እንዳለ ሁሉ፤ ተጠያቂነት ያለበት ውሣኔ መወሰን እንዳለባቸው፡፡ ከሁሉም በላይ ያለመወሰን እና ያለመስራት በእንዝላልነት በመስራት ከሚመጣው ጥፋት እኩል ተጠያቂነት እንዳለው በማሳወቅ፤
- ሹመት የሕዝብ ማገልገያ ቦታ እንጂ፤ የሹም መጠቀሚያ እንዳልሆኑ የተረዱ ብቻ ወደ ሃላፊነት መመደብ ለሥራቸው ተገቢውን ሥልጣን መስጠት፤

8.1.2. ፋይናንስ

ይህ የቃል ኪዳን ሠነድ ሲዘጋጅ አገራችን በአሁኑ ጊዜ ምንም የተለየ የፋይናንስ ምንጭ በተለየ ሁኔታ ይገኛል ከሚል ታሣቢ አይደለም፡፡ የፖለቲካ ሪፎርሞች እስከ አሁን በሚመደብላቸው በጀትና የሰው ሀይል በተሻለ ውጤታማ ማድረግ ይቻላል የሚል እምነት አል፡፡

በኤኮኖሚ ዘርፍ ከፍተኛ በጀት የሚመደብ ሲሆን ይህን በጀት በዋነኝነት በጊዜ ማርዘም እና በፕሮጀክት አፈፃፀም ድክመት ሲከፉም በሌብነት የሚባክን እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህን ስርዓት በማስያዝ ረገድ የሚወሰደው ቁርጠኛ አቋም በፋይናንስ ረገድ ወሳኝ ቦታ አለው፡፡ በተጨማሪ ለፖለቲካ ጠቀሜታ ሲባል ኤኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው ያልታዩ ፕሮጀክቶች በማጠፍ አፋጣኝ ለውጥ ሊያመጡ ለሚችሉ ትኩረት ለሚሰጣቸው ዘርፉች እንዲውል ይደረጋል፡፡

የማህበራዊ ዘርፍ ኢትዮጵያዊያን ያለን የበጎ አድራጎት ባህል በመጠቀም በሕዝብ ተሳትፎ እንዲሁም መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በማቀናጀት ወሳኝ የሚባሉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡ ለምሣሌ በከተማዋ የሚገኙትን የጎዳና ልጆችና በጎዳና ላይ በልመና የተሰማሩ እናቶችና ሕፃናትን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት እንዲቻል ኢዜማ የነደፈውን ፕሮግራም በአጭር ጊዜ በመተግባር ኢትዮጵያዊያን ያለንን በጎ ተሞክሮ ለዓለም የምናሳይበት ይሆናል፡፡

8.2. መራጩ ሕዝብ ኢዜማን ለምን ይመርጣል

8.2.1. የደህንነት ጉዳዮች

- ✓ የመንግስት የቅድሚያ ተግባርና ሃላፊነት የዜጎችን ደህንነትና ሰላምን መጠበቅ መሆኑን እናረጋግጣለን፤
- ✓ የዘውግ ማንነትን መሰረት ያደረገውን መንግስታዊ የፖለቲካ ስርአት፤ ሁሉም ዜጎች በእኩል ወደ የሚስተናገዱበት መንግስታዊ የፖለቲካ ስርአት እንዲቀየር እናደርጋለን፤
- ✓ ለተቋም ግንባታ ከፍተኛ ዋጋ በመስጠት በከፍተኛ ደረጃ በሰለጠኑ ባለሞያዎች የሚመሩ የደህንነት ማህበረሰብ፣ የመከላያ ሃይልና የዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ከፖለቲካ ወገንተኛነት በጸዳ መልኩ እንገነባለን፤ በእነዚህ ተቋማት ውስጥ የሃገር እና የህዝብ ደህንነት እና ጥቅምን የሚያስጠብቁ ባለሙያዎች ተገቢውን ክብር እንዲያገኙ እናደርጋለን፤ ሽልማቶች እንሰጣለን፤
- ✓ ዘለቄታ ያለው የተረጋጋ ሃገር እንዲኖረን ለማስቻል ተጨባጭ እና ምናልባታዊ የብሄራዊ የደህንነት ስጋት እና አደጋ ጋር የተያያዙ ስትራቴጂያዊ የመረጃ ትንተና ውጤቶች ላይ የተመረኮዘ የህግ ማስከበር፣ የመረጃ እና የደህንነት ስራዎች እንዲሁም የመከላከያ ሃይል እንቅስቃሴዎች ሙያሚነትን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወኑ እናደርጋለን፤

- ✓ የደህንነት ማህበረሰብ እና የመከላከያ ሃይል ለሚያከናውኑት ሃገራዊ ተለዕኮ ውጤታማ ለመሆን የሚያስችላቸውን የመስኩ የምርምር ስራዎች የሚተገበሩበት የምርመር ተቋማት ይደራጃሉ፤ እራሳችንን የመረጃ፣ የደህንነት እና የመከላከያ ሃይል መሳሪያዎች ለመቻል የሚያስችለንን ዝግጁነት እንፈጥራለን፤
- ✓ በሃገር ውስጥ ሆነ ከውጪ በሃገር ሉአላዊነት፣ አንድነት፣ በህዝብ ደህንነትና ብሄራዊ ጥቅም ላይ ሊቃጣ የሚችል ተጨባጭ እና ምናልባታዊ ስጋት ወይም አደጋ የማስቀረት ካልሆነም የመከላከል ተግባራትን በማንኛውም ሰአት ለመወጣት የሚያስችል ዝግጁነት በደህንነት ማህበረሰቡ እና መከላከያ ሃይል እንዲፈጠር እናደርጋለን፤ የሰብአዊ ደህንነት የተጠበቀባት ሃገር እንዲኖረን እናስችላለን።

8.2.2. የፖለቲካ ጉዳዮች

- ✓ የዜጎችን ሰብዓዊ፣ ዴሞክራሲያውና የኢኮኖሚ መብቶች ሙሉ ለሙሉ እናረጋግጣለን፣
- ✓ ኢትዮጵያን አንድነቷ የተረጋገጠ የሰላምና መረጋጋት አገር ለማድረግ የኢትዮጵያን ጥቅም ለድርድር አያቀርብም፤
- ✓ ሁሉኑንም ዜጎች በእኩልነት የሚያስተናግድ የፖለቲካ ሥርዓት እንዲገነባ አስፈላጊውን ጥረት እንደረጋለን፣
- ✓ ብዝሀነትን መሰረት ያደረገ ዴሞክራሲያዊ ፌድራሊዝም መንግስታዊ መዋቅርና አስራር እንከተላለን፣
- ✓ የዜግችን በፈለጉበት ቦታ የመኖር፣ንብት የማፍራት፣ የማሰብ፣የመሰብሰብ፣ የመደራጀት፣ፈለጉትን የፖለቲካ ሃሳብ የመደገፍና የመቃወም መብት እናከብራለን እናስከብራለን፤
- ✓ የአገርን ልዓላዊነት እናስጠብቃልን፣ ለህዝብ ሉዓላዊነት እንገዛለን የህዝብን ውሣኔ እናከብራለን፤
- ✓ የመንግስትና የፓርቲ ጉዳዮችን የአስራራር ሥርዓት ተግባራዊ እናደረጋለን፣
- ✓ የመንግስትም ሆነ የግል መገናኛ ብዙሃን፣ ለዜጎች መብት መከበርና ደህነታቸው መጠበቅ፣ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ተጨባጭ አስተዋጾ የሚያደርጉበትን ሁኔታ እናመቻቻለን እናረጋግጣለን፣

8.2.3. የኤኮኖ ሚጉዳዮች

- ✓ የግብርና ዘርፉን በማዘመን ኢትዮጵያ በቂ ምርት አምርታ በምግብ ራሷን እንድትችል ይደረጋል:: የተዛባ የንግድ ሰንሰለቱን በማዘመን ሸማቹ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል
- ✓ በግብርናና በኢንዱስትሪ የሚደረገው ኢንቬስትሜንት በቂ የሥራ ዕድል እንዲፈጥር ይደረጋል፤ የሃገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት እንዲያሟላ ይደረጋል
- ✓ መንግሥት ዜጎች በእኩል የኤኮኖሚ ምዕዳር እንዲወዳደሩ እና ሀብት እንዲያፈሩ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤
- ✓ መንግሥት ከዜጎች ጋር በኤኮኖሚው ውስጥ ውድድር ውስጥ አይገባም፤ ውድድሩ ጤናማ እንዲሆን ሕገ ወጥጭ ያለአግባብ የሚበለፅጉበት መንገድን ሥርዓት ያስይዛል፤
- ✓ በአነስተኛ ደረጃ ለሚንቀሳቀሱ ዜጎች ምቹ የሥራ ቦታ እንፈጥራለን፤ ዜጎች በኤኮኖሚ ሲያድጉ ወደ ግብር ከፋይነት እንደሚያድጉ ሰለምናም በአነስተኛ የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ የግብር ጫና እንቀንሳለን፤ ሴቶች በልዩ ሁኔታ ሥራ ፈጠራ እንዲሳፉ ማበረታቻ ይደረጋል::
- ✓ የግል ዘርፉ በስራ ፈጠራ ያለውን ጉልዕ ሚና በመረዳት ይህን አገራዊ ሚናውን በታማኝነት እንዲወጣ ድጋፍ ይደረግለታል:: ከመንግሥት ጋር ተጠግቶ የሚደረግ ሀብት ማጋበስን በፍፁም እናስቀራለን፤ የመሠረተ ልማት ግምባታዎች የሀገር ውስጥ ባለሃብቶችን በማሳትፍና ለወጣቱ ሥራ በመፍጠር የሚተግበር ይሆናል፤
- ✓ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመስፋፋት ኢኮኖሚው እንዲዘምን ይደረጋል፤ ሥራ እንዲፈጥር ይደረጋል፤ ብልሹ አሠራርን እንዲያስቀር ይደረጋል፤
- ✓ የፋይናንስ ሴክተር ብቁ ባለሞያዎችን በማፍራትና የአሠራር ሥራዓቱን በማዘመን ኢኮኖሚውን የሚደግፍ ይደረጋል
- ✓ የቱሪዝም መሠረተ ልማትና የገበያ ሥራዓቱን በማዳበር ሊኮኖሚ የሚያደርገውን አስተዋጾ ማሳደግ፤
- ✓ ለአጠቃላይ እድገታችን ማነቆ የሆነውን የመሬት ገጠር መሬት ባለቤትነት ፍትሃዊነትና ልማትን በአረጋገጠ መልኩ እንዲሻሻል እናደረጋለን፣

8.2.4. የማህበራዊ ጉዳዮች

- ✓ በየጊዜው በመቦርበር እየመነመነ የሄደውን ማህበራዊ ወረታችንን (Social Capital) እንገነባለን፣

- ✓ ዜጎች በችሎታቸውና በመልካም ባህሪያቸው የሚከበሩበት ማህበራዊ እሴት እንገነባለን፣
- ✓ በተሳሳተ የመንግሥት ፖሊሲና የገበያ ሕግ የተፈጠሩ ማህበራዊ ቀውሶችን ለመሻሻል ዙሪያ መለስ ጥረት እናደርጋለን፤ ስንፍና በምንም መመዘኛ በማህበራዊ ከለላ ሥር እንዳይበረታታ እናደርጋለን፤
- ✓ የማህበራዊ ፍትህ መሰረት የሆኑትን፤ ጤና የትምህርት አገልግሎቶች ጥረት እናሻሽላለን፤ የዜጎች ተሳትፎን በማረጋገጥ በአጭር ጊዜ ለውጥ እንዲመዘገብ እናደርጋለን፤
- ✓ ሕፃናት በጎዳና ላይ መለመኛ እንዳይሆኑ፤ ዜጎች ከጎዳና ሕይወት እንዲላቀቁ እንሰራለን፤ አረጋዊያን ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያገኙ፤ አካል ጉዳተኞች በአገር ግንባታ ያላቸው ሚና ከፍ እንዲል ድጋፍ ይደረግላቸዋል፤
- ✓
- ✓

8.2.5. የውጭ ግንኙነት ጉዳዮች

- ✓ የውሰጥ ችግሮቻችን በዴሞክራሲያዊ አግባብ በመፍታት የተከበረች አገርን ለልጅ ልጆቻችን ለማስረከብ ቁርጠኞች ነን፤
- ✓ ከተባበርን የተፈጥሮ ሀብቶቻችን ለመጠቀም የሚያግደን ሀይል እንደሌለ እናምናለን፤ ለዚህ የሚከፈለውን ሁሉ ዋጋ ከፍለን ኢትዮጵያን ከፍ እናደርጋለን፤
- ✓ ከጎረቤት አገሮች ጋር የሚኖረን ግንኙነት በጋራ ደህንነትና ጥቅም ባደረግበፍፁም መተባበር ላይ እንዲሆን እናደርጋለን፤ የኤኮኖሚ ትስስር በማጠናከር ከፍ ያለ የፖለቲካ ትብብር እንዲኖር እንሰራለን፤
- ✓ ለዓለም ሠላማ ያለን ቁርጠኝነት እናረጋግጣለን፤ ፀረ ሽብር ትብብሮች የአገራቸንን ጥቅም በመያዣነት እንዲሆን አንፈቀድም፤
- ✓ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ክብር እንዲጠበቅ እንሰራለን፤ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ለአገር ግንባታ ያላቸውን ከፍተኛ ሚና ከግምት አስገብተን ውጤታማ ተሳትፎ የሚያደርጉበትን ሁኔታ እናመቻቻለን፡፡